# የኢዴፓ የፖለቲካ ፕሮግራም ትንታኔ

## ክፍል ሁለት (Volume - 2)

## የመንግስት አደረጃጀትን በተመለከተ ኢዴፓ የሚያራምደው አቋም

(ረቂቅ - ፩)

ሰኔ 1995 ዓ.ም

## ብርቱ ማሳሰቢያ፣

ይህ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሕዝብ ይፋ የተደረገው በሰኔ ወር 1995 ዓ.ም ነው። ፖለቲካ በባህሪው የተለዋዋጭ ሂደቶች (Political Dynamism) ውጤት ነው። በዚህም ምክንያት ሰነዱ ከተዘጋጀ ወዲህ ባሉት ጊዜአት በሀገሪቱ በርካታ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። እንደ ፖለቲካ ኃይል፤ ኢ.ዴ.ፓም የዚሁ ዳይናሚዝም ውጤት ነው። ስለሆነም፣ ፓርቲው ይህንን ሰነድ አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ የመጨረሻውን Version እስከሚያወጣ ድረስ፤ ይህንን ሰነድ የሚያነቡ ሁሉ የተጻፈበትን ወቅት የቋንቋ አጠቃቀምና ስነልቡና ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ በአክብሮት እናሳስባለን።

**(የኢ.ዴ.ፓ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ)**

# ክፍል 2

# *የመንግስት አደረጃጀትን በተመለከተ ኢዴፓ የሚያራምደው አቋም*

## 1. *ፌዴራላዊ አደረጃጀት በዴሞክራሲያዊ ስርዓት*

*ፌዴራሊዝም ከመነሻው የተለያዩ መንግስታት ለተወሰነ ዓላማ የሚፈጥሩት ልል የሆነ ትብብርና ሕብረት ተደርጎ የሚታይ ስለነበር ፌዴራሊዝምን ከኮንፌዴሬሽን ለይቶ ለማየት የሚያስቸግር ሆኖ ቆይቷል። ይሁን እንጂ በ18ኛው ክፍለ ዘመን ከቅኝ አገዛዝ ራሳቸውን ነፃ በማድረግ በአዲስ መልክ የተፈጠሩትን የአሜሪካ ግዛቶች ተከትሎ ጠንካራ ሚና ያለው ማዕከላዊ ሥልጣንና በተወሰነ ደረጃ ራሳቸውን የማስተዳደር ስልጣን የተሰጣቸውን ግዛቶች በአንድ ላይ ያቀናጀ የፌዴራል መንግስት ሞዴል ከፈጠሩ በኋላ ትርጉሙ እየጠራ መጥቷል።*

*ፌዴራሊዝም አሁን ያለው ትርጉም ሕገመንግስታዊ በሆነ ስርዓት ውስጥ ስልጣን በተለያዩ አካላት መካከል የተከፋፈለበትን፣ እያንዳንዱ የስልጣን አካል በተሰጠው ክልል ውስጥ የራሱን ኃላፊነት ተግባራዊ የሚያደርግበትን፣ እነዚህን ተግባራት ለመፈፀም የሚያስችሉ የራሱ ተቋማት የሚያደራጅበትን ሁኔታ የሚያጠቃልል ነው። በመሆኑም በፌዴራል ስርዓት እያንዳንዱ የስልጣን አካል በሕግ በተሰጠው የኃላፊነት ክልል ውስጥ የራሱ ሉዓላዊነት አለው ማለት ነው። ይህም ሁኔታ እያንዳንዱ የስልጣን አካል የሚገለገልበትን ሕጋዊ ስልጣን የሚያገኘው ከበላዩ ያለ የስልጣን አካል በሚሰጠው ውክልና ላይ ተመስርቶ እንዳልሆነ የሚያሳይ ነው። በሌላ አገላለፅ ማዕከላዊ የሥልጣን አካል ከራሱ ሥልጣን እየቀረሰ ለአካባቢ አካላት በውክልና ከሚሰጥበት አሰራር በእጅጉ የተለየ ነው ማለት ነው። ምክንያቱም እንዲህ ዓይነቱ የሥልጣን ውክልና ከማዕከላዊው ስልጣን አካል በታች ያሉትን አካላት ሉዓላዊነት የማያከብር ብቻ ሳይሆን የተሰጣቸውን ውክልና መልሶ ለመንጠቅም እድል የሚሰጥ በመሆኑ ነው።*

*በመጀመሪያ ደረጃ ፌዴራሊዝም አካባቢያዊ አስተዳደሮች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ የሚያስችላቸው ከፍ ያለ ስልጣን እንዲኖራቸው ማድረግ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውል አደረጃጀትና አሰራር ነው። በዚህ ረገድ ስዊዘርላንድ፣ ቤልጅየምና ናይጀሪያ የመሳሰሉ ሀገሮችን እንደምሳሌ ማየት ይቻላል።*

*በሁለተኛ ደረጃ የፌደራል አደረጃጀትና አሰራር መኖርን አስፈላጊ ከሚደርጉት ነጥቦች መካከል የሀገሮች የቆዳ የቆዳ ስፋት አንዱ ነው። ሰፊ የሆነ አገርን ክልልን ከአንድ ማዕከል በሚሰጥ ፖለቲካዊ አመራር በብቃት ለማስተዳደር እንደሚስያቸግር ግልፅ ነው። እዚህ ላይ መገንዘብ የሚያስፈልገን ጉዳይ ቢኖር በፌዴራል ስርዓት ውስጥ ባሉት የማዕከልና የአካባቢ ስልጣን እርከኖች መካከል ያለው ሚዛን ከሀገር ሀገር የተለያየ መሆኑን ነው። እያንዳንዱ ልዩነት በጊዜ ሂደት የሚፈጠር ቢሆንም ዋናው ልዩነት ግን የየሀገሩ ታሪካዊና ነባራዊ ሁኔታ ተመሳሳይ አለመሆኑ ነው።*

*በአብዛኞቹ የፌዴራል ስርዓቶች ሁለት መሰረታዊ ሕገመንግስታዊ ባህርያት ጎልተው ይንፀባረቃሉ። እነዚህም አንደኛው ባለሁለት ሕግ አውጭ ምክር ቤቶች* (Bicameral legislature) *መኖር ነው። ይኸውም የመጀመሪያው ሕዝቡ እንደ ብዛቱ መጠን ተወካዮቹን በመላክ የሚያቋቁመው ሕግ አውጭ ምክር ቤት (የታችኛው ምክር ቤት የሚባለው) ወይም የተወካዮች ምክር ቤት የሚባለው ሲሆን ሌላኛው ደግሞ የአካባቢ መንግስታት የራሳቸውን ጥቅም ማስጠበቅ የሚችሉበት ወይም በብዙ ሀገሮች ሴኔት እየተባለ የሚጠራው ምክር ቤት (የላይኛው ምክር ቤት) ነው። ሁለተኛው ሕገ መንግስታዊ ገጽታ ደግሞ በማዕከልና በአካባቢ አስተዳደር መንግስታት መካከል አለመግባባት ሲፈጠር ዳኝነት (ብይን) የሚሰጠው የፍትህ አካል በመሆኑ የፍርድ ቤቶች ሚና ጠንካራ እንዲሆን መደረጉ ነው።*

ፌዴራሊዝም ማለት በማዕከላዊ መንግስትና የአካባቢ መንግስታት መካከል ያለው ስልጣን በተፃፈ ሕገ መንግስት አማካይነት የተከፋፈለበት የመንግስት አደረጃጀትና አሰራር ማለት ነው:: በፌዴራል ስርዓት ውስጥ በአንድ በኩል በብሔራዊና (ማዕከላዊ) በአካባቢ መንግስታት መካከል፣ በሌላ በኩል ደግሞ በአካባቢ መንግስታት መካከል ያለውን የእርስ በርስ ግንኙነትና ልዩነት ለማሳየት ሲባል የመጀመሪያው ዓይነት ግንኙነት (በማዕከላዊና በአካባቢ መንግስታት መካከል ያለው) ተዋረዳዊ ፌዴራሊዝም (Vertical federalism) ይባላል:: በሁለተኛው ዓይነት ግንኙነት (በተለያዩ አካባቢ መንግስታት መካከል ያለው) ደግሞ የጎንዮሽ ፌዴራሊዝም (Horizontal Federalism) ይባላል:: በዚህ አይነት መንገድ የተዘረጉ ግንኙነቶች ተግባራዊ ሊሆኑ በሚችሉ የሕግ ስርዓቶች የሚደገፉ ናቸው:: ለምሳሌ አንዱ አካል ለሌላው ሕጎች፣ የፍርድ ቤት ውሳኔዎችና መረጃዎች ታማኝ እንዲሆን፣ በአንዱ ክልል መንግስት ስር ያሉ ዜጎቹ የሚያገኙትን ጥቅምና ጥበቃ የሌሎቹ ክልል መንግስታት ዜጎች እንዲያገኙ፣ ከፍርድ የሸሹ ጥፋተኞችን ወደመጡበት እንዲመልሱ የሚሉና የመሳሰሉ በሕግ የተደገፉ ግንኙነቶችን ይፈጥራሉ:: ከዚህ በተጨማሪ በመካከላቸው በሚደረጉ ድርድሮች፣ በሚፈፀሙ ስምምነቶችና በሚካሄዱ ምክክሮች በፈቃዳቸው የሚፈጥሯቸው ግንኙነቶችም አሉ::

ፌዴራላዊ ስርዓትን የሚመለከት ትንታኔ በሚቀርብበት ጊዜ በጥንቃቄ መረዳት የሚያስፈልገው ለዚህ ስርዓት መፈጠር መነሻ የሆኑትንና ቀደም ሲል የተጠቀሱትን ሁለት መሰረታዊ ጉዳዮች ነው:: እነዚህም አንደኛው የተደበላለቀ ባህል፣ አመለካከት፣ ኃይማኖት፣ አሰፋፈርና የመሳሰሉት ገጽታዎች የሚታዩበት ሕብረተሰብ (Heterogeneous societies) መኖርና ሌላው ደግሞ ሰፊ የሆነ ጆኦግራፊያዊ ግዛት መኖር የሚሉት ናቸው:: ሁለቱም ጉዳዮች ከዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ጋር ተሳስረው ሊታዩ የሚችሉ ናቸው:: የተደበላለቀ መልክ ያለውን ሕብረተሰብ ፌዴራላዊ በሆነ ስርዓት ስር ማደራጀት ማለት የተለያዩ ባህሎች፣ አመለካከቶች፣ ኃይማኖት፣ ጂኦግራፊያዊ አካባቢዎች ወዘተ... በመንግስት ስልጣን ውስጥ ተመጣጣኝና ተገቢ ውክልና የሚያገኙበትን ሰፊ እድል ከማመቻቸት ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው:: ዜጎች በአመለካከት፣ በኃይማኖት፣ በባህልና በሌላም ልዩነት ምክንያት ተፅዕኖ ሳይደረግባቸው ወይም አድሎ ሳይፈፀምባቸው ነፃነታቸውና በእኩልነት የመታየት መብታቸው በተከበረበት መንገድ ለመኖር የተሻለ ዋስትና የሚያገኙበት ስርዓት ነው:: ከዚህም ሌላ ሰፊ በሆነ የጆኦግራፊ ክልል ውስጥ የሚገኙ ዜጎች ሰላማቸው እንዲጠበቅ፣ ልማታቸው እንዲፋጠንና ቀልጣፋ የሆነ አስተዳደራዊ አገልግሎት እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው:: ዜጎች የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው ለመወሰን የሚያስችላቸውን አስተዳደር በየአካባቢያቸው እንዲመሰርቱ፣ በመንግስት ስልጣን አካላት መካከል ያለው ግንኙነትና የስልጣን ክፍፍል የተመጣጠነ እንዲሆን፣ በተለያዩ የስልጣን አካላት መካከል የእርስ በርስ ቁጥጥር እንዲኖር ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት ነው:: ዜጎች በመንግስት ተግባር ውስጥ ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖራቸው፣ የመንግስት ስልጣን ያልተማከለ እንዲሆንና የዜጎችን የመወሰን ከሥልጣን በሚያሰፋ ደረጃ ወደሕዝቡ የቀረበ እንዲሆን የሚያስችል ስርዓት ነው:: በአጭሩ ፌዴራላዊ ስርዓት ሲባል ዜጎች የፖለቲካና የሲቪል ነፃነቶቻቸውን በሚገባ እንዲጠቀሙ፣ የመንግስት ስልጣን ምንጭና ባለቤት መሆናቸውን በተግባር እንዲያረጋግጡና በተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ በሆነ መንገድ የሚያገኙትን ሪሶርስ በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲያውሉ የሚያስችል አደረጃጀት ማለት ነው::

ሌላው ነጥብ የፌዴራል ስርዓት የሚመሰርቱ የአካባቢ መንግስታት የማዕከላዊው አካል እየመጠነ በሚሰጣቸው የሥልጣን ውክልና ላይ የሚንጠለጠሉ ሳይሆኑ በሕግ የተፈቀደ የራሳቸው ከፍተኛ ስልጣን ያላቸው መሆኑ ነው:: ይኽንን ስልጣን ማዕከላዊው የመንግስት አካል የማይነጥቃቸው መሆኑ እንዳለ ሆኖ አባል የሆኑበትንና በጋራ ያፀደቁትን ፌዴራላዊ ሕገ መንግስት በማይቃረን መንገድ በሚያወጡት የራሳቸው ሕገ መንግስት አማካይነት ስራ ላይ ያውሉታል:: የፌዴራላዝምን ስርዓት መከተል ዋነኛ ጥቅምም ይኸው ነው:: የመንግስት ስልጣን በአንድ ማዕከል ብቻ ተከማችቶ እንዳይቀር ወይም በአንድ ብቸኛ ሉዓላዊነት ስር እንዳይወድቅ ማድረግ ነው::

በፌዴራል አደረጃጀት የማዕከላዊው ስልጣን የሚመሰረተው የአካባቢ መንግስታት ከራሳቸው ሉዓላዊነት የተወሰነ ቀንሰው ለመስጠት ባላቸው ፈቃደኝነትና ስምምነት ላይ ነው:: በተጨማሪም በፈቃዳቸው ለሚፈጥሩትና ሁሉም በእኩልነት ለሚሳተፉበት የጋራ ሉዓላዊነት መገለጫ ሆኖ ለሚያገለግለው ፌዴላራዊ መንግስት መተሳሰሪያ የሚሆን ሕገ መንግስት ያበጁለታል:: በመጨረሻም በዚህ የፌዴራል ሕገ መንግስት ላይ ተመስርተው የራሳቸውን ሕገመንግስት በማውጣትና ስራ ላይ በማዋል ሉዓላዊ ስልጣን እንዳላቸው ያረጋግጣሉ:: የፌዴራል ስርዓት እንደዚህ ባለው ስምምነትና

ፈቃደኝነት ላይ እስከተመሰረተና በሕጋዊ መንገድ እስከተደራጀ ድረስ የትርምስና ፍጥጫ ምንጭ በመሆን ፋንታ የትብብርና የጋራ ጥቅም ማስከበሪያ መንገድ ሆኖ ያገለግላል፡፡ ዜጎች ፈቅደውና ተስማምተው ያልመሰረቱት ወይንም ራሳቸውን የሕዝብ ጥቅም ጠባቂ አድርገው የሚቀርቡ ጥቂት የፖለቲካ ቡድኖች እንደመሰላቸው ቀርፀው በሕዝብ ላይ የሚጭኑት ፌዴራላዊ ስርዓትና ፌዴራላዊ ሕገመንግስት አለመረጋጋትንና የእርስ በርስ ጦርነትን እንደማያስቀር፣ የዜጎችን ሰላም እንደማያስከብር፣ የተፋጠነ ልማት እንደማያስገኝና የተቀላጠፈ አስተዳደራዊ አገልግሎት እንደማይፈጥር በአለም ውስጥ የታዩ ተጨባጭ አብነቶችን በመጥቀስ ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ስለፌዴራላዊ ስርዓት ከዚህ በላይ የቀረበውን አጠቃላይ ምልከታ መነሻ በማድረግ በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን አለ የሚባለውን የፌዴራል አደረጃጀት መገምገም ይቻላል፡፡

# 2. ፌደራሊዝም በኢትዮጵያ

## 2.1 በኃይል የተጫነ ፌዴራሊዝም በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ተፈጠረ የሚባለውን ፌዴራላዊ አደረጃጀት ባህርይ በግልፅ ለመረዳት የሚያስችሉ በርካታ ጥያቄዎችን አንድ በአንድ እያነሱ ግምገማ ከማድረግ በፊት በቅድሚያ መመለስ ያለበት ጥያቄ ለመሆኑ በዜጎች ፈቃድና ስምምነት ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ስርዓት በሀገሪቱ ውስጥ አለወይ? የሚለው ጥያቄ ነው፡፡ ሀገራችን ኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የአደረጃጀት አማራጭ ፌዴራላዊ ይሁን ወይንስ አሃዳዊ፣ ኮንፌዴራላዊ ይሁን ወይንስ ከፌዴራላዊና ከአሃዳዊ የተወሰኑ ገጽታዎችን ወስዶ በማቀናጀት መጠቀም፣ የሚሉ ልዩ ልዩ አማራጮች ወግና ስርዓት ባለው መንገድ ለዜጎች ቀርበው ነፃ ውይይትና ክርክር ተካሂዶባቸውና ውሳኔ ተሰጥቶባቸው አያውቅም፡፡ በእርግጥ የደርግ ሕገ መንግስትና የኢህአዴግ ሕገመንግስት ረቂቆች በቀረቡበት ጊዜ እነዚህ የአደረጃጀት አማራጮች መኖራቸው በምሁራንና በፖለቲካ ሰዎች እየተነሳ መላውን ሕዝብ ባላሳተፈ ሁኔታ መጠነኛ ውይይቶች የተካሄዱበትና በአንዳንድ የጥናት ጽሑፎች የተጠቀሱበት አጋጣሚ መኖሩ የሚካድ ነገር አይደለም፡፡ ከዚያም በፊት በሀገሪቱ በነበረው የንጉሱ ስርዓት ጭቆናን ለመታገል ይሞክሩ በነበሩ የፖለቲካ ቡድኖችና ግለሰቦች ጥያቄው በተለያየ አጋጣሚ ይነሳ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ከንጉሱ ጊዜ ጀምሮ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ሕገመንግስት እስከተፃፈበት ጊዜ ድረስ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋትን የአደረጃጀት አማራጭ ለመወሰን ወግና ስርዓት ባለው መንገድ በዜጎች መካከል ነፃ ውይይትና ክርክር እንዲደረግበትና ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚያስችል ምቹ መድረክ ተፈጥሮ አያውቅም፡፡

የንጉሱ ሕገመንግስት በራሳቸው መልካም ፈቃድ «የተሰጠ» ስለነበር የሀገሪቱ አደረጃጀት አሃዳዊ መልክ ይኑረው ወይስ ፌዴራላዊ ወይም ሌላ ይሁን ብሎ ለመወያየትና ለመወሰን የሚያስችል እድል ዜጎች እንዳላገኙ ግልፅ ነው፡፡ በደርግ ጊዜ የወጣው የኢሕዲሪ ሕገ መንግስትም የአንድ ፓርቲ አገዛዝ እንዲኖር በቅድሚያ ወስኖ የተነሳ በመሆኑ ዜጎች አማራጭ ያላቸውን ሌሎች የፖለቲካ ቡድኖችና ግለሰቦች የተለየ አስተያየት ለመስማትም ሆነ በአማራጮች ላይ የተመሰረተ ነፃ ውይይት አካሂዶ ለመወሰን እድል አልነበራቸውም፡፡ በሕወሓት/ኢህአዴግ ጊዜ የወጣው የኢፌዲሪ ሕገመንግስትም «መስዋዕትነት ከፍዬ የጨበጥኩትን ስልጣን ለማንም አሳልፌ አልሰጥም» በሚለው የሕወሓት/ኢሕአዴግ መልካም ፈቃድ የተረቀቀ በመሆኑ ሌሎች አማራጭ ያሏቸው የፖለቲካ ቡድኖችና ግለሰቦች አማራጮቻቸውን ለዜጎች አቅርበው ነፃ ውይይትና ክርክር ለማድረግ እድል አልነበራቸውም፡፡ በሕገ መንግስት ጉባኤ ስም የተሰባሰቡት የሕወሓት/ኢሕአዴግ ካድሬዎች በራሳቸው መመዘኛ ከየብሔረሰቡ መልምለው ያሳተፏቸውን ጥቂት ደጋፊዎቻቸውን በመጨመር ቀደም ሲል የሕዝብ ውክልና የሌላቸውን ስብስቦች ይዘው ባረቀቁት ሕገመንግስት ላይ ለጥቂት ሳምንታት በመገናኛ ብዙሃን እርስ በርሳቸው ሲፈላሰፉ ከሰነበቱ በኋላ በሙሉ ድምፅ አጽድቀው ተነሱ፡፡ ከዚህ ውጭ ዜጎች የተለያዩ የፖለቲካ ቡድኖችና ግለሰቦችን አማራጮች መሰረት አድርገው ነፃ በሆነ መንገድ ተከራክረው ነፃ ውሳኔ የሰጡበት አጋጣሚ አልነበረም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ በሀገራችን አለ የሚባለውን ፌዴራሊዝም ጉድለቶች ለማየት እንሞክር፡፡

## 2.2 የግለሰብ ነጻነትን የረሣ ፌዴራሊዝም

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈጠረ የሚባለው ፌዴራሊዝም የቆመበት መሰረት የዴሞክራሲ መነሻ የሆነው የግለሰቦች መብት ሳይሆን በሌኒንና በስታሊን ጽሑፎች ላይ የሰፈሩትና ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የሚሉት ቃላቶች እንደሆኑ በሕወሓት/ኢህአዴግ ልዩ ልዩ ሰነዶች ተገልጿል፡፡ ስለሆነም ብሔሩን ከብሔረሰቡ፣ ብሔረሰቡን ከሕዝብ ለመለየት ወይንም ደግሞ ብሔር ሆኖ ሕዝብ ያልሆነ፣ ሕዝብ ሆኖ ደግሞ ብሔረሰብ ያልሆነውን ለመለየት ከሌኒንና ከስታሊን መመዘኛዎች በስተቀር ሌላ አማራጭ እንደሌለ በመውሰድ ዜጎች በዚህ መስፈርት ብቻ እየተሰፈሩና እየተለኩ ከዚህ በላይ መስፋትም፣ ከዚህ በታች መጥበብም አይገባችሁም ተብለዋል፡፡ ይህ የዚህ ብሔር፣ ያኛው የዚያ ብሔረሰብ፣ ሌላው ደግሞ የዚህኛው ሕዝብ አባል ነው በሚል ቢወዱትም ቢጠሉትም ማንነታቸው በገዢዎች እየተሰፈረ ተሰጣቸው፡፡ የዜጎች ማንነት በሚናገሩት ቋንቋ ብቻ እንደሚገለጽ ሕግ ሆኖ ተጻፈ፡፡ የዜጎች መብት ሊጠበቅና ዋስትና ሊሰጠው የሚገባው ሰው በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን ያንዱ ወይንም የሌላው ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ አባል ሲኮን ብቻ ነው ተባለ፡፡ በተባበሩት መንግስታት የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ አንቀጽ 22 «ማንኛውም ሰው በዘር፣ በቀለም፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ ወይም በሌላ አመለካከት፣ በትውልድ አገር ወይም በማህበረሰቡ ውስጥ የአንደኛው ክፍል አባል በመሆን፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም ይኸንን በመሰለ ምክንያት ምንም አይነት ልዩነት ሳይደረግበት በዚህ መግለጫ ውስጥ የተደነገጉት መብቶችና ነፃነቶች ሁሉ ባለቤት ነው» ተብሎ ተደንግጓል፡፡ ከዚህ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው በተጠቀሱት መብቶች ተጠቃሚ ለመሆን ሰው ከመሆን ሌላ የዚህ ብሔር ወይም የዚያ ብሔረሰብና ሕዝብ አባል መሆን፣ ይኸንን ወይም ያንን ቋንቋ መናገር፣ አንዱን ወይም ሌላውን ኃይማኖት መከተል የማይጠይቅ መሆኑን ነው፡፡

ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝቦች የሚሉትን ቃላቶች በሚመለከት ማርክሲዝም ሌኒንዝም ወደሀገራችን መግባት ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ በአተረጓጎም ረገድ ሰፊ ልዩነቶች እንደነበሩና አሁንም እንዳሉ የሚታወቅ ነው፡፡ እነዚህን ቃላቶች የተለያዩ ቡድኖችና የፖለቲካ ኃይሎች እንደየፍላጎታቸውና ዝንባሌያቸው እየተረጎሙ በሕዝቡ ውስጥ ልዩነቶችን ለማስፋትና ቅራኔዎችን ለማቀጣጠል ሲጠቀሙበት ከነበረው ስህተት መማር ያልቻሉት የአሁኖቹ ገዥዎች ከመብት ሁሉ መሰረታዊው መብት ሰው ሆኖ መፈጠር መሆኑን ወደጎን ለመግፋት ሰፊ ጥረት ሲያደርጉና ይልቁንም የተወሰነ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ አባል ሆኖ መገኘት ከፍ ያለ የመብት ዋጋ እንዳለው ለማሳመን ደፋ ቀና ሲሉ ከርመዋል፡፡ ማንም ሰው በሰውነቱ የተረጋገጠ መብት አለው የሚለው መርህ የየትኛውም ዘር፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖት ወዘተ. አባል ለሆነው ለማንኛውም ሰው የሚሰራ ነው፡፡ ማንም ሰው የተለየ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝብ አባል በመሆኑ ምክንያት በደልና ተፅዕኖ ሊደርስበት የሚችልበት ሁኔታ መኖሩ ባይካድም ዞሮ ዞሮ በሰው ልጅ መብት ላይ የተፈፀመ በደልና ተፅዕኖ ከመሆን አይዘልም፡፡ የሰው ልጅ መሰረታዊ መብት መጠበቅ ያለበት ሰው በመሆኑ ብቻ ሳይሆን የዚህና የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆኑ አድርጎ የመረዳት ሁኔታ ከተፈጠረ የሚከተለው ውጤት የሰውን የተከበረ ተፈጥሯዊ መብት ከሰው ልጅ በኋላ ከመጣው ቋንቋ በታች ማውረድ ይሆናል፡፡

የአሁኑ ፌዴራላዊ አደረጃጀት ዋነኛው ስህተት የሚጀምረው በብሔር፣ ብሔረሰብ ሕዝቦች መመዘኛ የተከለለ አደረጃጀት ብቸኛው መፍትሔ ነው ከሚል መነሳቱ ነው፡፡ በብሔር ፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝቦች ደረሰ የሚባለው ጭቆናና በደል በሰው ልጅ ላይ የደረሰ ጭቆናና በደል እንደሆነ አድርጎ ያለመረዳት መሰረታዊ ችግር አለበት፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው ጭቆና በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ተለይቶ አንደኛው ሕዝብ ሌላውን እየጨቆነ እንደኖረ አድርጎ ከመመልከት የሚመነጭ ስህተት ነው፡፡ ወይም በሌላ አገላለጽ አማርኛ ተናጋሪ የሆነ ሕዝብ ትግርኛ ተናጋሪውን፣ ትግርኛ ተናጋሪ የሆነው ሕዝብ ኦሮምኛ ተናጋሪውን፣ ኦሮምኛ ተናጋሪው ሕዝብ ሶማሊኛ ተናጋሪውን፣ ሶማሊኛ ተናጋሪው ሕዝብ አፋርኛ ተናጋሪውን ወዘተ. ሲጨቁነው ከመኖሩ በስተቀር አማርኛ የሚናገር ጨቋኝ አማርኛ በሚናገረው ጭቁን ላይ ምንም አይነት በደል አድርሶ አያውቅም እንደማለት ነው፡፡ ወይም በሌላ መንገድ አንድ አይነት ቋንቋ በሚናገር ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ መካከል የጨቋኝና የተጨቋኝ ግንኙነት አልነበረም እንደማለት ነው፡፡ ትግርኛ የሚናገር ጨቋኝ በትግርኛ ተናጋሪ ጭቁን ላይ፣ ኦሮምኛ የሚናገር ጨቋኝ ኦሮምኛ የሚናገር ጭቁን ላይ ወዘተ. ጭቆናና በደል አድርሶ እንደማያውቅ አድርጎ የመመልከት ጉድለት በግልጽ ይታያል፡፡

ኢትዮጵያ ውስጥ ቀደም ሲል በሰዎች ላይ ለደረሰው ጭቆናና በደል ሁሉ ተጠያቂው የአገዛዝ ስርዓት መሆኑ እየታወቀ ኃላፊነቱ የአንድ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ መሆን አለበት ብሎ ያምናል:: ጨቋኝነት፣ ነፍጠኝነት፣ ትምክህተኛነት ጠባብነት ከአንድ ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ ጋር ብቻ የተሳሰረ እንደሆነ አድርጎ ያምናል:: በኢትዮጵያ ሁኔታ ነፍጥ (መሣሪያ) መታጠቅ ከአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ ጋር ብቻ የተቆራኘ ባህል እንዳልሆነ ግልፅ ነው:: ጨቋኝ በሆነው አገዛዝ ስርዓት ውስጥ የሥልጣን ተቋዳሽ የነበሩት የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ አባላት ብቻ ሆነው አያውቁም:: ትምክህተኝነትም በአንድ ወይም በሌላ መልኩ የተለያዩ ቋንቋ በሚናገሩ የሕብረተሰብ አባላት ውስጥ ሲንፀባረቅ የነበረ እንጂ ከአንድ የተለየ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር ብቻ የተቆራኘ ባህርይ አይደለም:: አማርኛ ተናጋሪ ጭቁኖች አማርኛ በሚናገሩ ጨቋኞች በደል ሲደርስባቸው መኖሩ ብቻ ሳይሆን አሁንም እንደሚደርስባቸው ማንም የሚክደው አይደለም:: ትግርኛ የሚናገሩ ጭቁኖች ይኸንኑ ቋንቋ በሚናገሩ ጨቋኞች ግፍና በደል ሲደርስባቸው እንደነበረው ሁሉ አሁንም በከፋ መልኩ እየደረሰባቸው ነው:: ኦሮምኛ የሚናገሩ ጭቁኖች ኦሮምኛ በሚናገሩ ጨቋኞች ሲጨቆኑ እንደነበረው ሁሉ ዛሬም ተባብሶ ቀጥሏል:: በሌሎችም ቋንቋ ተናጋሪዎች ያለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው:: የጭቆና አገዛዝ ከአንድ የተለየ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ ጋር ብቻ የተያያዘ ሳይሆን ከአገዛዙ ፀረ-ዴሞክራሲ መሆን የሚመነጭ ነው:: ጨቋኝና ተጨቋኝ በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎችም ውስጥ የነበረና አሁንም ያለ ነው:: ስለዚህ ጭቆናን ለማስወገድ የሚቻለው የአንድን ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ ለይቶ ተጠያቂ በማድረግ ሳይሆን በአጠቃላይ ለጭቆና መሠረት የሆነውን ፀረ-ዴክራሲያዊ አገዛዝ በማስወገድ ነው:: በሌላ አገላለጽ ከጭቆና ፈጽሞ ለመላቀቅ የሚቻለው ማንም ሰው የዚህ ወይም የዚያ ቋንቋ ተናጋሪ፣ ኃይማኖት ተከታይ፣ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ አባል መሆን አለመሆኑን እየመረጡ መብት በመፍቀድ ወዘተ. ሳይሆን ሰው በመሆኑ ብቻ ከማናቸውም አይነት ጭቆና ነፃ መሆን አለበት የሚል ቁርጠኛ አቋም በመያዝ ነው::

በኢትዮጵያ አሁን የተዘረጋው የቋንቋ ፌዴራሊዝም ልክ እንደባንቱስታን ክልሎች ሁሉ እያንዳንዱ ሰው በሰውነቱ ማግኘት የሚገባውን መብት እየረገጡ በአንጻሩ የራስ በራስ አስተዳደር መብት ተከብሮለታል በሚል ሽፋን ሕዝቡ የራሱ ጎሣ ጨቋኖች የሚደርሱበትን ጭቆና እየተሸከመ እንዲኖር የማድረግ አላማ ያለው ነው:: ኤዴፓ የዚህን አገዛዝ ፌዴራሊዝም የማይቀበለው እስካሁን በተገለጹትና በሌሎችም መሰረታዊ ምክንያቶች ነው:: ኤዴአፓ የአንድ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ አባል መሆን ወይንም የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ፣ የአንድ ኃይማኖት ተከታይ አባል መሆን ሰዎችን ሁሉ በአንድ ሚዛን ላይ የሚስቀምጣቸው ብሔር፣ ብሔረሰባቸው፣ ቋንቋቸው፣ ኃይማኖታቸው፣ ሀብታቸው፣ ትምህርታቸው፣ ፆታቸው፣ አመለካከታቸው ወዘተ. ሳይሆን ሰው መሆናቸው ብቻ ነው የሚል ጠንካራ አቋም አለው:: ይህ ሲባል የቡድን መብት የለም ማለት አይደለም:: የቡድን መብት መኖሩን ያለማመንታት ኤዴፓ ያምናል:: የማንኛውም ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ፣ ወይም ጎሣ ቋንቋው፣ ባህሉ፣ ኃይማኖቱ ወዘተ. ሊከበርለትና ከሌሎች ጋር በእኩልነት ደረጃ የመታየት መብቱ ሊጠበቅለት እንደሚገባ ሙሉ በሙሉ ይቀበላል:: ይሁን እንጂ ማንኛውም የቡድን መብት መሰረቱ የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ሊጠበቁለት የሚገቡትን ነፃነቶችና መብቶች በቅድሚያ መቀበልና ማክበር ነው ብሎ ያምናል::

ኢዴፓ በግለሰብና በቡድን መብቶች መካከል ግጭት ሲፈጠር ወይም ተቃራኒ ሁኔታ ሲያጋጥም መፍትሔ መስጠት ያለበት የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ሊከበሩለት የሚገቡ ነፃነቶቹና መብቶቹ እንደማይደፈሩ በማረጋገጥ መሆን አለበት ብሎ ያምናል:: ለምሳሌ አንድ ጎሣ በቋንቋው ትምህርት እንዲማር የጋራ ውሳኔ ቢተላለፍና የዚያ ጎሣ አባል የሆነ አንድ ግለሰብ በዚያ ቋንቋ ለመማር አልፈልግም የሚል አቋም ቢይዝ የጎሣህ ቋንቋ እንዲያድግ በዚህ ቋንቋ የመማር ግዴታ አለብህ ተብሎ የራሱ ነፃ ውሳኔ ሊፈርስ አይገባም:: አንድ ጎሣ በባህሉ ለሴቶች ክብር የማይሰጥ ቢሆን የሰው ልጅ ሊከበሩለት የሚገቡ መብቶችን የሚፃረር በመሆኑ ተቀባይነት የለውም:: አንድ መንግስት ለሀገርና ለሕዝብ ጥቅም በሚል አንድ ግለሰብ በባለቤትነት የያዘውን ቤት፣ ቦታ፣ የእርሻ መሬት፣ ሌላ ንብረት ለመውሰድ ቢፈልግ ግለሰቡን አሳምኖና ፈቃዱን በማግኘት ወይም ተመጣጣኝ የሆነ ካሣ በመክፈል ካልሆነ በስተቀር የሰውን ልጅ መብት በሚጎዳ መንገድ ሊፈጽመው አይገባም:: ስለዚህ ማንኛውም የቡድን መብት የሰው ልጅ ሰው በመሆኑ ሊከበሩለት የሚገቡ ነፃነቶችንና መብቶችን ሊፃረር ስለማይገባው የመብቶች መሠረት መሆን ያለበት የሰው ልጅ መብትና ነፃነት ነው የሚለው መርህ የኤዴፓ አቋም ነው::

*አዴፓ ያለፉት አገዛዞች በሰው ልጅ ላይ የፈፀሙትን ጥፋት አጥብቆ የሚቃወመውን ያህል የአሁኑ አገዛዝ ደግሞ በብሔር ብሔረሰቦች መብት ሽፋን በሰው ልጅ ላይ እያደረሰ ያለውን ጭቆናና በደል አምርሮ ይቃወማል። የአሁኑ የፌዴራል አደረጃጀት ጎሣንና ቋንቋን ብቻ የተከተለ ሆኖ መመስረቱ በጎሣና በቋንቋ መብት ሽፋን በሰው ልጅ መብትና ነፃነት ላይ የሚደርሰውን ጭቆና ከምንጊዜውም በላይ አስከፊ ስላደረገው ኤዴፓ አይቀበለውም። ለፌዴራል ክልል አደረጃጀት ቋንቋ እንደ አንድ ታሳቢ ነጥብ መታየት የሚገባቸው መሆኑን ኤዴፓ ቢያምንም በተለይ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ከጎሣና ቋንቋ በተጨማሪ ሌሎች የሰው ልጅ መብትና ጥቅም የሚረጋገጥባቸው ብዙ መንገዶች አሉ ብሎ ያምናል።*

*የአንድ ጎሣ አባል የሆነና አንድ አይነት ቋንቋ የሚናገር ሰው በሁሉም ነገር ወጥ የሆነ ፍላጎትና አንድ አይነት ጥቅም አለው ማለት አይቻልም። የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ጎሣ አባል ሆኖ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በኢኮኖሚ ጥቅም ልዩነት ሊኖረው ይችላል። የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ጎሣ አባሎች በሙሉ በተመሳሳይ የሀብት፣ የትምህርት፣ የስራ ደረጃ ላይ ሊገኙ አይችሉም። ሁሉም አንድ አይነት የኑሮ ሁኔታ፣ አንድ አይነት ፆታ ያላቸው ሊሆኑ አይችሉም።*

*እንግሊዞች አንድ አይነት ቋንቋ አላቸው፣ ነገር ግን በሁሉም ነገር አንዳችም ልዩነት የላቸውም ማለት አይደለም። በተቃራኒው የተለያየ ቋንቋ የሚናገር ሕብረተሰብ አባል በሆኑ ሰዎች መካከል ደግሞ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ጎሣ አባል ባለመሆናቸው ምክንያት ምንም የሚያገናኛቸው አንዳችም ነገር አይገኝም ብሎ መደምደም ስህተት ነው። የተለያዩ ቋንቋዎችን በሚናገሩ ሰዎች መካከል አንዳች ግንኙነት ማድረግ፣ ስምምነትና ትብብር መፍጠር አይቻልም የሚል ዩኒቨርሳል ሕግ የለም። በአሜሪካ ወስጥ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚናገሩ የተለያየ ኃይማኖትና አመለካከት ያላቸው ሰዎች አሜሪካዊ ዜጋ ሆነው ይኖራሉ። በመጀመሪያ አንድ አድርጎ የሚያስተሳስራቸው ሰው መሆናቸው ሲሆን ሌላው መተሳሰሪያ አሜሪካዊ ዜግነታቸው ነው። አብረው በመኖር የመሰረቱት የጋራ ባህልና ዝምድና ሌላው የሚያስተሳስራቸው ነጥብ ነው። ይህ ለኢትዮጵያም የሚሰራ ነው። አማርኛ ወይም ኦሮምኛ ቋንቋ በሚናገሩ ሙስሊሞች መካከል የቋንቋ ልዩነት ቢኖርም በኃይማኖት የሚያተሳስሩበት ዕድል አላቸው። አማርኛ ወይም ኦሮምኛ ቋንቋ በሚናገሩ ዴሞክራቶች መካከል የቋንቋ ልዩነት ቢኖርም የሚያስተሳስር አንድ አይነት ፖሊቲካዊ አመለካከት አላቸው። በአንድ ማህበራዊ ገጽታ ልዩነት ስላለ በሌላ ምንም አይነት መንገድ ትስስር መፍጠር እንደማይቻልና እንደውም ሁልጊዜ ቅራኔና ግጭት እንደሚኖር ማሰብ ስህተት ነው። በአንዱ ማህበራዊ ገጽታ የሚከሰትን ልዩነት በሌላ ማህበራዊ ግንኙነት እያካካሱ፣ ትስስር እየፈጠሩና እያቻቻሉ አብሮ መኖር ይቻላል። የሰውም ልጅ ሕይወት የተመሰረተው የሚያለያዩትን ከሚያስተሳስሩት ጋር በማቻቻል ዘዴ ነው። የሚያለያዩ ነገሮችን ጨርሶ ማስወገድ የማይቻለውን ያህል የሚያስተሳስሩትንም እንደዚሁ ጨርሶ ማስወገድ አይቻልም።*

*ማንኛውንም አይነት ፖለቲካ በልዩነቶች ላይ ብቻ ተመስርቶ ከቆመ መውጫ ወደማይገኝለት አዘቅት ከመውረድ አያድንም። አንድ የፖለቲካ ሥርዓት ዴሞክራሲያዊና ሰፊ መሰረት ያለው ሊሆን የሚችለው የመብቶች ሁሉ መነሻ የግለሰብን መብትና ነጻነት ማክበር መሆን እንዳለበት ሲቀበል ነው። ስለዚህ በጎሣና በቋንቋ ልዩነት ላይ ብቻ የተመሰረተውን ፌዴራላዊ አደረጃጀት ሕዝቡ ለረጅም ጊዜ አብሮ በመኖር፣ ክፉውንና ደጉን አብሮ በመጋራት፣ በጉርብትና ብቻ ሳይሆን በተለያየ የግንኙነት አውታር (በጋብቻ፣ በቋንቋ፣ በባህል ወዘተ.) በመተሳሰር፣ የጋራ ጥቅምና ማንነት በማዳበር የፈጠሩትን ዝምድና ይበልጥ በሚያጠናክር ፌዴራላዊ አደረጃጀት በአዲስ መልክ መፍጠር ያስፈልጋል። የዜጎችን ፈቃድና ስምምነት በሚያረጋግጥ፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲጎለብት በሚያስችል አዲስ ፌዴራላዊ አደረጃጀት መቀየር ያስፈልጋል።*

## 2.3 በተዛባ የኢትዮጵያዊነት ትርጉም ላይ የተመሰረተ ፌዴራሊዝም

*አሁን በሥራ ላይ ያለውን ፌዴራላዊ አደረጃጀት ኢዴፓ የማይቀበለው በጎሣና በቋንቋ ልዩነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ ብቻ አይደለም። ለአሁኑ ፌዴራሊዝም መፈጠር መነሻ ተደርገው በተወሰዱት የማንነት፣ የታሪክና የሕዝብ ግንኙነት ግምገማዎችና የተሳሳቱ አቋሞችም ላይ ከአሁኖቹ ገዥዎች ጋር ኢዴፓ መሠረታዊ ልዩነቶች አሉት። የአሁኖቹ ገዥዎች አሁን ለፈጠሩት ፌዴራሊዝም ጎሣንና*

ቋንቋን ብቻ መሰረት ለማድረግ ሲወስኑ ከዚህ በፊት ሕዝቡ በኢትዮጵያዊነት ስም ማንነቱ ተደብቆ በመቆየቱ ይህንን በደል ለመቀየር ከኢትዮጵያዊነቱ በፊት የጎሣ ማንነቱ ሊከበርለት ይገባል ከሚል አቋም ተነስተው ነው:: በዚህም አቋማቸው የተነሳ ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊ ማንነትን የኢትዮጵያ ችግሮች ሁሉ ምንጭ እንደሆኑ አድርገው እንደሚያቀርቡ ይታወቃል:: በፖሊሲ ሰነዶች፣ በተለያዩ ስብሰባዎች፣ አለም አቀፍ መድረኮችና የዜና አውታሮች በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ ማንነት ላይ ያላቸውን የመረረ ጥላቻ ግልጽ አድርገዋል:: ከዚህ በፊት በሀገሪቱ ለተፈፀመውም የዘርና ሌላም መድሎ፣ በሕዝብ ላይ ለተፈፀመው ልዩ ልዩ ዓይነት በደልና ጭቆና ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን እንደተጠያቂ አድርገው ይመለከቷቸዋል::

ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ከዚህ በፊትም ሆነ አሁን በዜጎች ላይ ለደረሰውና እየደረሰ ላለው ግፍና ጭቆና መንስኤም ተጠያቂም የሚሆኑበት በቂ ማስረጃ ለማቅረብ አይቻልም:: ኢትዮጵያ የሚለው መጠሪያ ከአንድ የተለየ ሕብረተሰብ ክፍል፣ ቋንቋ፣ ኃይማኖትና አመለካት ጋር የተቆራኘ አይደለም:: ኢትዮጵያ ብዙ ቋንቋዎችን የሚናገሩ፣ የተለያዩ ሃይማኖቶችን የሚከተሉ፣ የተለያየ የኑሮ መሰረትና የመኖሪያ አካባቢ ያላቸው የሕብረተሰብ አባላት ተደበላልቀው የሚኖሩባት አገር ነች:: ኢትዮጵያ የሚለው የአገር መጠሪያ የአንድን ቋንቋ ተናጋሪ ወይም የአንድን ኃይማኖት ተከታይ ሕዝብ ክብር፣ ዝናና ገናናነት በተለየ ሁኔታ እንዲወክል ታስቦ የሌላ ቋንቋ ተናጋሪን ወይም የሌላ ኃይማኖት ተከታይን ዝቅ አድርጎ ለማሳየትና ለማዋረድ ተፈልጎ የተሰጠ ስያሜ አይደለም:: ቆለኛውን ከደገኛው፣ ድሃውን ከባለፀጋው፣ ጉልበተኛውን ከደካማው ለይቶ ለመግለፅ የተሰጠ ስያሜ አይደለም:: አንድን የሕዝብ ክፍል ለማወደስና ሌላውን ለማሳነስ በማቀድ ተዘጋጅቶ የተሰጠ ስያሜ አይደለም:: ይህ ስያሜ ረጅም በሆነ የታሪክ ዘመን ውስጥ አንዴ ሲጋጩ ሌላ ጊዜ ሲተባበሩ፣ በልዩ ልዩ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ግንኙነታቸውን እያጠናከሩ፣ እየተጋቡና እየተዋለዱ፣ እየተሳሰሩና እየተዛመዱ የኖሩ የተለያዩ የሕብረተሰብ አባላት አገር መጠሪያ ነው::

ኢትዮጵያ የሚለው መጠሪያ የፖለቲካ ስም ከመሆኑ አልፎ አንድን የሕዝብ ክፍል ለማስደሰትና ሌላውን ለማስከፋት የሚረዳ መልዕክትና አላማ ያዘለ አይደለም:: ነገር ግን በተለያዩ የማንነት ማረጋገጫ ሰነዶች ላይ ዜጎች ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን ሳይሆን የጎሣ ማንነታቸውን እንዲያሰፍሩ ይጠየቃሉ:: የጎሣ ማንነቱን ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ማንነቱን ለማስፈር የሚፈልግ ሰው ሲኖር የእናቱን ወይም የአባቱን የትውልድ ሀረግ ይጠየቅና እሱ ያልፈለገው ማንነት ይሰጠዋል:: በብዙ የሀገሪቱ ክፍል አዲስ ማንነት የታደላቸው ዜጎች በሚሊዮን የሚቀጠሩ ናቸው::

ኢትዮጵያዊ ሆኖ የትግርኛ ወይም የኦሮምኛ ወይም የሶማሊኛ ወይም የአማርኛ ቋንቋ ወዘተ.. ተናጋሪ በመሆን መካከል ድሮም ሆነ አሁን ቅራኔ የለም:: ድሮም ሆነ አሁን ቅራኔ ያለው ጨቋኝ አገዛዝን ተክለው በሕዝብ እንደታዘሉ ለመኖር የሚልጉ ገዥዎች ሕሊና በሚፈጥረው ቅዠትና ፊት ለፊት በሚታየው እውነት መካከል ነው:: በአለም አቀፍ መድረክ በተገኙና ሀገር ለሀገር በዞሩ ቁጥር ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውን የሚያሳይ ፓስፖርትና ሰንደቅዓላማ አንጠልጥለው የሚዞሩት ገዠዎች ለሚገዙት ሕዝብ ግን ከኢትዮጵያዊነቱ በፊት የጎሣ ማንነቱ መቅደም እንዳለበት የሚሰብኩበት ሁኔታ የገዠዎች ሕሊና በሚፈጥረው ቅዠትና በግልጽ በሚታየው እውነት መካከል ያለውን ቅራኔ ቁልጭ አድርጎ ያሳያል:: እናም የቅራኔዎችና የችግሮች ምንጭ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊ ማንነት ነው በሚል ግምገማና አቋም ላይ በመመስረት በጎሣ ማንነት ላይ የሚቆም ፌዴራሊዝም ለማደራጀት የተወሰደው እርምጃ የተሳሳተ አመለካከት ውጤት ነው::

በዚህ የተነሳ የተበላሸውን ሁሉ ለማስተካከል በቅድሚያ በተዛባ ግምገማ ላይ የተመሰረተው አመለካከት መለወጥ ይኖርበታል:: ኢትዮጵያዊነት የጎሣ ማንነት ጠላት እንዳልሆነ ገዥዎች ተቀብለው ወደህሊናቸው ሊመለሱ ይገባቸዋል:: ኢትዮጵያዊ ማንነትን ለመቀበል የሚቸገር አገዛዝ በኢትዮጵያ ስም እንደሀገር መሪ ለመቆጠር የሚያበቃ የሕግና የሞራል መብትም ሊኖረው አይችልም:: ስለሆነም ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊ ማንነትን የችግር፣ የጭቆናና የበደል ሳይሆን የጋራ ጥቅም መገኛ፣ የክብር መጎናፀፊያና የኩራት ምንጭ እንደሆኑ በማመን ላይ የሚመሰረት ፌዴራላዊ ስርዓት መደራጀት አለበት:: ኢትዮጵያዊ ማንነት በእያንዳንዱ ዜጋ ፍላጎትና ምርጫ የሚወሰን እንጂ በሌላ ግፊት የሚሰጥና የሚነጠቅ አለመሆኑን የሚቀበል ስርዓት መፈጠር አለበት::

# 2.4 የቋንቋ ፌዴራሊዝምና የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት በኢትዮጵያ

የራስን እድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል የሚለው መብት የሰውን ልጅ መብትና ነፃነት በማስከበር ረገድ ሊቀርቡ ከሚችሉ የዴሞክራሲ አማራጮች ሁሉ የተሻለ አማራጭ እንዳልሆነ ይታወቃል። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሲታይ ደግሞ የሚሰራ አማራጭ የመሆኑ እድል የጠበበ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ የተደበላለቀ ባህልና የሕብረተሰብ አወቃቀር ላለው ሀገር በሙሉ የሚያዋጣው የመብትና ነፃነት ማስከበሪያ መንገድ የቋንቋን መስመር የተከተለ ፌዴራላዊ አደረጃጀት መኖርና የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል መብትን መቀበል ብቻ ነው የሚል በቲዎሪም ሆነ በተግባር የተደገፈ ዩኒቨርሳል ሕግ እስካሁን ድረስ በአለም ላይ የለም።

ከቀድሞዎቹ ምስራቅ አውሮፓ ሶሻሊስት ሀገሮች መካከል የቀድሞ ሶቭየት ሕብረትና ዩጎዝላቪያ የዚህ አይነት ተሞክሮ እንደነበራቸው የሚታወቅ ሲሆን መጨረሻው ሳያምር እንደቀረና በተለይ የዩጎዝላቪያው ዘግናኝ በሆነ የዘር  ማጽዳት ፍጅት እንደተጠናቀቀ ይታወቃል። የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገ ንጠል የሚለው ቲዎሪ ቀማሪዎች የሆኑት የሌኒንና የስታሊን ሀገር ሶቭየት ሕብረትም ይህንን የመገንጠል መብት መስጠት የመገንጠልን አደጋ መከላከያና የትምምን ማስገኛ ዘዴ ሆኖ ያገለግላል የሚል አቋም ወስዳ ሕገመንግስታዊ ድንጋጌ ብታደርገውም እንኳንስ አስራ አምስቱን የሕብረት ሪፑብሊኩ አባላት ከመገንጠል ሊያተርፍ ይቅርና በሩሲያ ስር ያለችውን የቼችኒያ ግዛትም ይህንን ጥያቄ እንዳታነሳ መከላከያ ሊሆን አልቻለም። በነገራችን ላይ ራስን በራስ የማስተዳደር መብት እስከመገንጠል የሚል ሕገመንገስታዊ ድንጋጌ በማስፈር አለም ከሚያቃት ሶቭየት ሕብረት ሌላ በዋናነት የምትጠቀሰው በሕወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ስር የወደቀችው የኛዋ ኢትዮጵያ ናት።

ምንአልባት እስካሁን የቋንቋን መስመር ተከትሎ የተቋቋመና በስራ ላይ እየዋለ ነው ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል ፌዴሬሽን ካለ በስዊዘርላንድና በቤልጅየም የተመሰረተው ፌዴሬሽን ነው። ይሁን እንጂ የሁለቱ ሀገሮች ታሪክ፣ ባህል፣ ጂኦግራፊያዊ ሁኔታ፣ የሕዝብ አሰፋፈር፣ ኃይማኖት፣ የሕዝብ ቁጥር፣የኢኮኖሚ ሁኔታና የሕብረተሰቡ አወቃቀር ከኢትዮጵያ በጣም የተለየ ነው። ጥቂቶቹን ልዩነቶች ብቻ ወስደን መጠነኛ ንጽጽር ብናደርግ የልዩነቱን ስፋት ለመረዳት እንችላለን። በመጀመሪያ ስዊዘርላንድን ብንወስድ የቆዳ ስፋቷ በእኛ ሀገር አንድ በስፋቱ ትልቅ ከሆነ አውራጃ የማይበልጥ ነው። የሕዝቧ ብዛት ሰባት ሚሊዮን ገደማ ነው። ሕዝቧ የጀርመን፣ የፈረንሳይና የኢጣሊያ ዝርያ ካላቸው ሕዝቦች የተዋቀረ ሲሆን ከጠቅላላው የስዊዘርላንድ ሕዝብ ውስጥ የእነዚህ ድርሻ 95% አካባቢ ነው። ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ ግማሹ የካቶሊክ ኃይማኖት ተከታይ ሲሆን፣ ግማሹ ደግሞ የፕሮቴስታንት ኃይማኖት ተከታይ ነው። ሃገሪቱ የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት የምትከተል ሲሆን ከብዙዎቹ ፓርቲዎች ውስጥ የመንግስት ስልጣንን በተከታታይ የሚጋሩት አራት ፓርቲዎች ናቸው።

የእነዚህ ዋና ዋና ፓርቲዎች አደረጃጀት ደግሞ ፌዴራሊዝሙ ከቆመበት የቋንቋ መስመር ውጭ በዋናነት በሕዝቡ አመለካከትና ማህበረ- ኤኮኖሚያዊ  ክፍፍል ላይ የተመሰረተ ነው። የፖለቲካ ሥልጣን በአንድ ገናና ፓርቲ እጅ ተጠቃሎ የማይያዝበት፣ ስልጣን እንደርስት ለረጅም ጊዜ ለአንድ ግለሰብና ፓርቲ ብቻ የማይሰጥበት፣ ሕዝቡ ለመንግስት ስልጣን የሚወክላቸውን መሪዎች ተመጣጣኝ የድምፅ ብልጫ መርህን ተከትሎ ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የሚመርጥበት የሰለጠነና ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ስርዓት ያሰፈነች ሀገር ነች። የቋንቋዎቹ ቁጥር ማነስ፣ የሕዘቡ አሰፋፈር ኩታ ገጠም መሆን፣ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ አቅም ከፍተኛ መሆን፣ የሕዝቡ የፖለቲካ ባህል መዳበር፣ የፖለቲካ ስርዓቱ ዴሞክራሲያዊ መሆንና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ሲታዩ ከኢትዮጵያ ጋር ሰፊ ልዩነት መኖሩን መገንዘብ ይቻላል።

ሌላዋ የቋንቋን መስመር ተከትላ የተደራጀች ሀገር ቤልጅየም ነች። በብዙዎቹ ነገሮች ስለስዊዘርላንድ ከተጠቀሰው ጋር ስለምትመሳሰል ለየት ያሉትን ሁኔታዎች ብቻ በማንሳት ከእኛ ሁኔታ የምትለይበትን ማሳየት ይበቃል። የቆዳ ስፋቷ ከስዊዘርላንድም ያንሳል። የሕዝቧ ብዛት ወደ አስራ አንድ ሚሊዮን ገደማ ነው። የፌዴራል ሰርዓቱ በሶስት ጂኦግራፊያዊ ክልሎችና በሶስት ጂኦግራፊያዊ

ባልሆኑ የባህል ማህበረሰቦች የተመሰረተ ነው:: ከጠቅላላው ሕዝብ 90% አካባቢ የሚሆነው ሕዝብ ፈረንሣይኛ ከሚናገሩ ዋሉኖችና ዳች ከሚናገሩ ፍሌሚሾች የተውጣጣ ነው:: ከዚህ ውስጥ የፍሌሚሾቹ ቁጥር ወደ 6 ሚሊዮን የሚጠጋ ሲሆን ከጠቅላላው የቤልጅየም ሕዝብ ያላቸው ድርሻ 57% አካባቢ ነው:: የዋሉኖቹ ቁጥር ደግሞ ወደ 3.5 ሚሊዮን ገደማ ሲሆን ከጠቅላላው የቤልጅየም ሕዝብ 33% ገደማ ድርሻ አላቸው:: የቤልጅየም የፌዴራል ስርዓት በእነዚህ ሁለት የቋንቋ ክልሎቻ በብራስልስ (የቤልጅየም ዋና ከተማ) ላይ ተመስርቶ በጠቅላላው በሶስት ክልሎች ላይ የተመሰረተ ነው:: የብራስልስ ነዋሪ አብዛኛው ፈረንሳይኛ ተናጋሪ ሲሆን ከዳች ቋንቋ ተናጋሪዎች በስተቀር አብዛኛው የቤልጅየም ሕዝብ በሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች የተገነባ ነው:: ቤልጅየም የተመሰረተችው እ.ኤ.ኤ በ1830 የዳች ቋንቋ የሚናገሩ ፍሌሚሾች ፈረንሣይኛ ከሚናገሩት ዋሉኖች ጋር በመቀላቀላቸው ነው:: ሁለቱ ቋንቋዎች ደግሞ እኩል መታየት የጀመሩት በ1930ዎቹ ውስጥ ነው:: ይሁን እንጂ እ.ኤ.አ በ1970 ለሁሉም የየራሳቸው የባህልና የትምህርት አቶኖሚ (ራስገዝ) የሚፈቅድ ሕገመንግስት ፀድቋል::

ከዚህ የውስጥ አቶኖሚ በስተቀር እ.ኤ.አ. እስከ 1990ዎቹ መጀመሪያ ቤልጅየም አሃዳዊ በሆነ የመንግስት አደረጃጀት ስርዓት ስር ነበረች:: እ.ኤ.አ. በ1993 ከፍላንደርስና ዋሎኒያ ሌላ ብራስልስን እንደ አንድ ክልል በመጨመር በሶስት ክልሎች ላይ የተመሰረተ የፌዴራል ስርዓት የምትከተል ሀገር ሆነች:: በዚህች ሀገር ከነበረው የቋንቋ ልዩነት ጋር በተያያዘ የፖለቲካ ፓርቲዎች አደረጃጀት የቋንቋ መስመርን የተከተለ መሆኑ የሚጠበቅ ቢሆንም በዚያ ሀገር ያለውን ክፍፍል አስከፊ መልክ እንዲይዝ ያደረገው ደግሞ ልዩነቱ በካቶሊክ አማኞችና አማኝ ባልሆኑት መካከል ካለው ልዩነት ጋር መግጣጠሙ ነው:: ቤልጅየም የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት የምትከተል ሲሆን ብዙውን ጊዜ የመንግስት ስልጣን የመጋራት ብቃትና ጥንካሬ ያላቸው ሶስት ፓርቲዎች መሆናቸውን ተከትሎ የ3 ፓርቲ ስርዓት ተከታይ ተብላ ትጠራለች:: ክርስቲያን ዴሞክራትስና ሶሻሊስትስ የሚባሉት ሁለት ፓርቲዎች በሀገሪቱ ውስጥ የሚኙት ትላልቅ ፓርቲዎች ሲሆኑ ከእነዚህ ጋር ሲነፃፀር መካከለኛ መጠን ያለውና ሶስተኛው ፓርቲ ሊበራልስ የሚባለው ነው:: ሌሎች በርካታ ትናንሽ ፓርቲዎች ቢኖሩም እ.ኤ.አ ከ1980ዎቹ በኋላ ይበልጥ እየተዳከሙ መጥተዋል:: በአሁኑ ጊዜ ቤልጅየም እንድትከፋፈል ጥያቄ አንስቶ የሚታገል ፓርቲ በሀገሪቱ ውስጥ የለም::

ቤልጅየም የአውሮፓ ፓርላማ፣ የአውሮፓ ኤኮኖሚክ ኮሚሽንና የሌሎችም ትላልቅ አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ተቋማት መቀመጫ በመሆኗ የአውሮፓ ማዕከል ተደርጋ የምትቆጠር ሀገር ነች:: እንደ ስዊዘርላንድ ሁሉ በብዙ ጉዳዮች ከኢትዮጵያ ሁኔታ ጋር የሚያመሳስላት ካለመኖሩም ሌላ ቤልጅየምን ከኢትዮጵያ የተለየ የሚያደርጋት ሌላ ነጥብ በዚያች ሀገር ያለው የፓርቲዎች የቋንቋ ክፍፍል ከሀይማኖትና ከማህበረ ኤኮኖሚያዊ ክፍፍሎች ጋር መገጣጠሙ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ በዚያች ሀገር ያሉ ፓርቲዎች ቤልጅየም እንድትከፋፈል የሚያነሱት ጥያቄ የሌላቸው መሆኑም ከኢትዮጵያ ሁኔታ የተለየ ያደርጋታል:: ስዊዘርላንድም ሆነች ቤልጅየም የቋንቋን መስመር በተከተለ ፌዴራል አደረጃጀት መንግስታቸውን የመሰረቱ ቢሆኑም በሁሉም ሕገ መንግስቶች የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል የሚል ድንጋጌ የለም:: ስለሆነም የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል በቋንቋ መስመር ለተደራጀ ፌዴራሊዝም ሁሉ ዩኒቨርሳል ሕግ ተደርጎ የማይወሰድና በሶቭየት ተሞክሮ ውጤት አልባ ሆኖ ከቀረ በኋላ ሌላዋ ቤተሙከራ ኢትዮጵያ ብቻ መሆኗን መገንዘብ ይቻላል:: በኢትዮጵያ ሁኔታ ደግሞ የቋንቋን መስመር የተከተለ ፌዴራላዊ አደረጃጀት ለመከተል የሚያመች ሁኔታ ጨርሶ የለም:: በመጀመሪያ ደረጃ ከ70 በላይ ቋንቋዎች ባሉባት አገር ከ70 በላይ የሆኑ የክልል መንግስታትን መፍጠር አይቻልም:: በደቡብ ክልል 46 ቋንቋ ተናጋሪዎች በአንድ ክልልነት እንዲደራጁ ግድ የሆነበትም ምክንያትም ይኸው ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለረጅም ጊዜ አብሮ በመኖር፣ በንግድ፣ በፍልሰት፣ በጦርነት፣ በጋብቻ፣ በባህል፣ ወዘተ. የመሰረተው ጠንካራ ዝምድና አለ:: የፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዞች የልዩነት ቀዳዳዎችን እያሰፉ በማጋጨትና በመከፋፈል ለአገዛዛቸው እንዲያመች ብዙ ጥረት እንዳደረጉ ባይካድም ሕዝቡ እነዚህን ሁሉ ተፅዕኖዎች ተቋቁሞ እየተቀላቀለ፣ እየተዋሃደና እየተሳሰረ በመሄዱ በቋንቋና በባህል የፈጠረው ግንኙነት ሎሎች ጉራማይሌ ሕብረተሰብ አላቸው ከሚባሉ ሁሉ የተሻለ ነው:: በተለይም ሀገሪቱ በተደጋጋሚ ጊዜ ለውጭ ጥቃት በመጋለጧ ወረራን በጋራ በመመከትና የሀገርን ነፃነት በመጠበቅ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች በአንድ የጦር ግንባር እየተሰለፉ በባዕድ መጠቃት የሚያደርሰውን

የሕሊና ስብራትና ወረራን አሸንፎ ድል ማድረግ የሚያስገኘውን የመንፈስ ደስታ በአንድነት ተጋርተዋል፡፡ በዚህም ያዳበሩት የአንድነትና የወንድማማችነት ስነልቦና ከዘመን ዘመን፣ ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገረ የቀጠለ በመሆኑ የተለያየ ቋንቋ በሚናገሩ ኢትዮጵያዊያን መካከል የባዕድነት መንፈስ የለም፡፡

በቋንቋ የሚለያዩ ኢትዮጵያዊያን በሠርግ፣ በኃይማኖት፣ በሀዘን ስርዓቶች አብረው ሲቆሙና ሲደጋገፉ ማየት አዲስ ነገር አይደለም፡፡ በከተማም በገጠርም የሚገኙ የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያን በመኖሪያ፣ በስራና በመዝናኛ ስፍራ አብረው ሲያሳልፉ፣ በፍቅር ሲኖሩና ሲረዳዱ ማየት የዘወትር ክስተት ነው፡፡ ደስታንና ሀዘንን፣ የጭቆና አገዛዝንና ረሃብን እየተጋሩና እየተደጋገፉ በመኖር የፈጠሩት ዝምድና ገዥዎች እንደሚያናንቁት ቀላል ነገር አይደለም፡፡ ለረጅም ዘመን ክፉውንና በጎውን አብረው በማሳለፋቸው የፈጠሩትን ቤተሰባዊ ትስስር በቋንቋም ይሁን በሌላ ልዩነት ምክንያት በቀላሉ እንደሚፈርስ አድርጎ ማሰብ በሕዝቡ መካከል የተመሰረተውን ግንኙነት ጥልቀትና ደረጃ አለመገንዘብ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ከቋንቋ ልዩነት መስመሮች ጋር በቀጥታ የሚጣጣሙ ሌሎች አደገኛ ክፍፍሎች እስከቅርብ ጊዜ ድረስ አልነበሩም፡፡ የቋንቋ መሰረት የሚከተሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሆን ተብለው በብዛት የተፈበረኩት ከሕወሓት/ኢህአዴግ ወደመንግስት ስልጣን መውጣት ጋር ተያይዞ ነው፡፡ በእርግጥ ቀደም ሲል ኢጣሊያ የተወሰነውን የኢትዮጵያ ክፍል በቅኝ ግዛት ከያዘችበት ጊዜ ጀምሮ በአስመራ የጀመረቻቸው ከኃይማኖት ጋር የተያያዙ አደረጃጀቶች ተከስተው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በሌላው የኢትዮጵያ ክልል ቀርቶ በኤርትራም ሰፊ መሰረት የነበራቸው አልነበሩም፡፡ ከዚያ በኋላ ጀብሃና ሻዕቢያ ኤርትራን ለመገንጠል የጀመሩትን ትግል ለማሳካት በኢትዮጵያ ውስጥ በጎሣ መሰረት ላይ የቆሙ ድርጅቶች እንዲፈጠሩ ጥረት አድርገዋል፡፡ ይህንን ሁኔታ በማጠናከር ኢትዮጵያን የማዳከም አጀንዳ ያላቸው የውጭ ሀይሎችም ተሳትፈውበታል፡፡ ከዚያ በኋላ በሰሜን የሀገሪቱ ክፍል ሕወሓት ከመደራጀቱም ሌላ በምስራቅ፣ በመሃልና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎችም ተመሳሳይ አደረጃጀቶች ተከስቱ፡፡ የዚህ አይነቱ አደረጃጀት ሆን ተብሎ በተነደፈ እቅድና በከፍተኛ ሁኔታ ተጠናክሮ እንዲቀጥል መንግስታዊ ድጋፍ ተሚልቶለት በሰፊው ተግባራዊ የሆነው በሕወሓት/ኢህአዴግ አገዛዝ ዘመን ነው፡፡ ብቸኛ የመብት ማረጋገጫ አማራጭ ሰውን በየቋንቋው ከፋፍሎ ማደራጀትና የመገንጠል መብት እንዳለው በሕገመንግስት መደንገግ ነው ብሎ የሚሰብከው ሕወሓት/ኢህአዴግ ወደስልጣን ከመጣ በኋላ የተባለውን መብት መጎናፀፍ የቻለ አንድም የሕብረተሰብ ክፍል ግን የለም፡፡ በዚህ ፖሊሲ ሕወሓትና በጎሣ ውክልና ሽፋን እየመረጠ የሾማቸው ምልምሎች ያገኙት ጥቅም መኖሩ ባይካድም ሕዝቡ የተረፈው ነገር የለም፡፡ ሕዝቡ ያጋጠመው ነገር ካለ ከቀድሞው የከፋ ጭቆናና ግፍ ነው፡፡ ልዩነቱ የአንድነት መፈክር አንግበው ይገዙት የነበሩት ጨቋኞች ሲወገዱ የጎሣ መፈክር ያነገቡት ጨቋኞች በቀድሞዎቹ እግር መተካታቸው ነው፡፡

# 2.5 ከአንድነት ይልቅ ለልዩነት ትኩረት የሰጠ ፌዴራሊዝም

በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ለማንኛውም ሕዝብ ቋንቋና ባህል አለመከበር ዋናው አደጋ የፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዝ ሊወገድ አለመቻሉ ነው፡፡ የአሁኑ አደረጃጀት ይህንን ያልተቀበለና የአንዱ ሕዝብ ቋንቋና ባህል ለሌላው አደጋ እንደሆነ በማስመሰል የጎሣን ልዩነቶች መሰረት ባደረገ አዲስ አቀራረብ የነበረውን የጭቆና አገዛዝ ለማስቀጠል የተቀየሰ አደረጃጀት ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ አይነቱ አደረጃጀት በኢትዮጵያ ሁኔታ ለፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዝ እድሜ መራዘም የሚጠቅም ከመሆኑ በስተቀር የሕዝብን መብትና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ሊፈጥር አይችልም፡፡ ሕዝብን የሕዝብ ጠላት አድርጎ በማሰብ የተመሰረተ አደረጃጀት የማንንም ሕዝብ መብት ሊያስከብር ይችላል ብሎ ማመን አይቻልም፡፡ እንዲህ አይነቱ አደረጃጀት ጥላቻና ቂም በቀልን እየዘራ ከሚያበቅል በስተቀር በእኩልነት ላይ የተመሰረተ የሕዝብ አንድነትን ሊያመጣ አይችልም፡፡ በኢትዮጵያ ሁኔታ የቋንቋንና የጎሣ መስመርን የተከተለ ፌዴራሊዝም ሊያመጣ የሚችለው በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነትን ሳይሆን በዩጎዝላቪያና በሩዋንዳ ከተፈፀመው የከፋ እልቂትና ብጥብጥ ነው፡፡

የአሁኑ አደረጃጀት የሕዝቡን የጠበቀ ትስስርና ዝምድና ይበልጥ ለማሳደግ በሚረዳ መርህ ላይ የተመሰረተ አይደለም፡፡ በመሆኑም አንዱን ወይም ሌላውን ቋንቋና ባህል የሌላው አደጋና ስጋት

አድርጎ ስለሚነሳ ለአንድ ወይም ለሌላው ቋንቋና ባህል የተለየ እንክብካቤና ጥቅም ማሟላት ያስፈልጋል ወደሚል ዘረኛ አቋም የሚወስድ ነው። ይህ ደግሞ ነገሩን ሁሉ ታጥቦ ጭቃ የሚደርግና ወደኋላ የሚመልስ አቋም መሆኑ የማይቀር ነው። እንደገና ወደዘር ማንቋሸሽና እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ ወደሚል ጤናማ ያልሆነ ፉክክር ውስጥ የሚያስገባ ነው። በሕዝቦች መካከል በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲጠናከር የሚያስችሉ እድሎችን ሁሉ የሚያጠፋ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ በሕዝቦች ፈቃድና ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የተፈጠረ አደረጃጀት ባለመሆኑ ሕዝቦች ተቀብለው ሊደግፉትና ሊያጠናክሩት የሚችሉበት እድል የለም። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሕዝብን የሚያስተሳስሩ የጋራ ጥቅሞች፣ ፍላጎቶችና አላማዎች መኖራቸው እየታወቀ ሕወሓት/ኢህአዴግ የተከተለው በልዩነቶች ላይ ብቻ የተመሰረተ አደረጃጀት በመሆኑ ሕዝቡ በተለያየ መንገድ ተቃውሞታል። በሕዝብ ፈቃድ ላይ ያልተመሰረተ ማንኛውም አደረጃጀት ደግሞ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ከመሆኑም በላይ ለግጭትና አለመረጋጋት መንስኤ መሆኑ የማይቀር ነው። የአሁኑ አደረጃጀት በሀገሪቱ ውስጥ እንዲገነባ ከሚፈለገው የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ስርዓት መርሆዎች ጋርም የሚጋጭ ነው። የካፒታልና የሠራተኛ ኃይል ነፃ ዝውውር የካፒታሊዝም ስርዓት ዋነኛ ባህርይ ነው። የነፃ ገበያ ሰርዓት በጎሣና በቋንቋ አጥር ተከልሎ ሊገነባ የሚችል አይደለም። በካፒታሊዝም ስርዓት መርህ መሰረት ማንም ሰው ወይም ተቋም ኢንቨስትሜንት ከፍቶ ምርት ለማምረትና ጥቅም ለማግኘት የሚችልበትን አካባቢ እስካገኘ ድረስ ዘሩንና የትውልድ ሀረጉን እየተከተለ ራሱን አስሮ መቀመጥ አይፈልገም። ካፒታል ያለው ኢንቨስትሜንት ለማካሄድ የሚያስችለውን ቦታ ሲመርጥ ቀዳሚ መመዘኛ የሚያደርገው የጎሣና ቋንቋ ትስስርን ብቻ አይደለም። በመጀመሪያ መነሻ የሚያደርገው ጥሬ ዕቃ፣ ጉልበትና ገበያ መኖሩን ነው። ጉልበትና እውቀት ያለው ሠራተኛ ደግሞ ጉልበትንና እውቀቱን ሸጦ ጥቅም የሚያገኝበትን አካባቢ ይፈልጋል እንጂ ዘሬና ጎሣዬ በሌለበት ቦታ ሄጄ አልሰራም በሚል እስረኛ ሆኖ መቀመጥ አይፈልግም። በዚህም ምክንያት ባለካፒታልና የሥራ ኃይል ገበያ ፍለጋ ወጥተው ገበያ በሚያገኙበት ስፍራ ይገናኛሉ እንጂ ሁልጊዜ በጎሣቸው አጥር ውስጥ ተከልለው የሚኖሩበት ሁኔታ የለም። ስለዚህ የአሁኑ አደረጃጀት የካፒታልና የሠራተኛ ጉልበት ነፃ ዝውውር እንዳይኖር አጥር የሚያበጅ በመሆኑ የሁሉንም ሕዝቦች የመልማትና የማደግ እድል የሚጎዳ ነው።

ከዚህ አይነቱ ዘረኛና ከፋፋይ አደረጃጀት ወጥቶ የሕዝብን መብት፣ እኩልነትና አንድነት የሚያረጋግጥ፣ ሰላምንና ብልጽግናን በአስተማማኝ ሁኔታ የሚፈጥር አቅጣጫ ለመከተል ሌላ አማራጭ መኖሩን መቀበል ያስፈልጋል። ይኸኛው አማራጭ በሕዝብ ፍላጎትና ውሳኔ ላይ የተመሰረተ እንዲሁም በእኩልነትና በጋራ ጥቅም ላይ የተመሰረተ ፌዴራላዊ አደረጃጀት መፍጠር ያስፈልጋል ከሚል ሃሳብ የሚነሳ አማራጭ ነው። ሕዝቡ ከልዩነቶቹ በበለጠ ሁኔታ የሚያስተሳስሩት የጋራ ጥቅሞች፣ ፍላጎቶችና አላማዎች ስላሉት እነዚህን ለመጠበቅ የሚረዳው ፌዴራላዊ አደረጃጀት ይፈልጋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ በቋንቋና በጎሳ ልዩነቶች ብቻ ታጥሮ የተቀመጠ አይደለም። በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በቋንቋ እየተለያዩ በኃይማኖት የተሳሰሩ፣ በኃይማኖት እየተለያዩ በቋንቋ የተገናኙ፣ በቋንቋ እየተለያዩ በጋብቻ የተሳሰሩ፣ በአመለካከት እየተለያዩ በአሰፋፈር የተቀራረቡ በአጭሩ በአንዱ አይነት ማህበራዊ ገጽታ ያላቸውን ልዩነት በሌላው አይነት ማህበራዊ ገጽታ አስተሳስረው የሚኖሩ፣ የጋራ እሴት፣ ዝምድናና ግንኙነት የፈጠሩ፣ የጋራ ጥቅም፣ ፋላጎትና አላማ ያላቸው ሕዝቦች እንዳሉ መቀበል ተገቢ ነው። የሚመሰረተው ፌዴራላዊ ስርዓትም ይህንን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል። የሁሉንም ሕዝብ ቋንቋና ባህል በእኩልነት መጠበቅ የሚቻለው በዚህ አይነት አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ፌዴራላዊ አደረጃጀት ሲኖር ነው። በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነትም የሚመጣው የሕዝቡን ፈቃድና የጋራ ጥቅሞች መሰረት ያደረገ አደረጃጀት ሲፈጠር ነው። በዚህ አይነቱ አደረጃጀት ውስጥ ሆኖ ማንም ሕዝብ የራሱን ቋንቋና ባህል ለመጠበቅ ለመንከባከብና ለማሳደግ የሚከለክለው ነገር የለም። አንዱ የሌላውን ቋንቋና ባህል እንዳያከብር የሚያደርገው በፍላጎትና በጋራ ጥቅም መርህ ላይ የተመሰረተ ፌደራሊዝም ሳይሆን በጥላቻና በዘር ልዩነት ላይ የተመሰረተ ፌዴራሊዝም ነው።

ሕዝቦች ካልተከፋፈሉ መብታቸው፣ ጥቅማቸውና እኩልነታቸው አይጠበቅም የሚል ሕግ የለም። የተለያየ ቋንቋና ባህል ባላቸው ሕዝቦች መካከል ሌላ የመገናኛና የዝምድና ማስተሳሰሪያ መንገድ የለም የሚል ቲዎሪና የተግባር ማረጋገጫ የለም። ስለዚህ የተሻለው አደረጃጀት የልዩነት መስመሮችን በመከተል ሳይሆን የሚያስተሳስሩ የግንኙነት መስመሮችንና የጋራ ጥቅሞችን መሰረት በማድረግ የሚመሰረት ፌዴራላዊ አደረጃጀት ነው። ይህ ሲባል ልዩነቶችን ሁሉ ጨርሶ ማጥፋት ወይንም

*በኃይል ማፈን ያስፈልጋል ማለት አይደለም፡፡ ወይንም በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የቋንቋ፣ የባህል፣ የአመለካት፣ የኃይማኖት ወዘተ.. ልዩነቶች እንደሌሉ ይቆጠሩ ማለት አይደለም፣ ይልቁንም ልዩነቶች እንደሚኖሩ በማመንና እነዚህንም በማክበር ላይ የተመሰረተ የጋራ ግንኙነትና ዝምድና መፍጠር የተለያዩ ጥቅሞችንና ፍላጎቶችን ለመንከባከብ እንቅፋት ሊሆን አይችልም ማለት ነው፡፡ የጋራ ጥቅሞችን መሰረት አድርጎ የሚፈጠረው ግንኙነት ደግሞ ልዩነቶች ቢኖሩም የጋራ ጥቅሞች እስካሉ ድረስ አንዱ የሌላው ስጋት የሚሆኑበትን የጥርጣሬና ያለመተማመንን መንፈስ ስለሚያስቀር በእኩልነትና በመከባበር ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲኖር የሚረዳ ግንኙነት ነው፡፡ የአንዱ ጥቅም መከበር ለሌላው ጉዳት እንደማይሆን፣ የአንዱ ጥቅም መጓደል የሌላውንም ጥቅም መጓደል እንደሚያስከትል ለመገንዘብና አንዱ የሌላው አጋር እንጂ ስጋትም ጠላትም እንዳልሆነ ለመተማመን የሚያስችል እድል የሚፈጠረው የጋራ መተሳሰሪያ መንገዶችን የተከተለ የፌዴራል አደረጃጀት ሲኖር ነው፡፡*

*የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል የሚለው መርህ በአለም አቀፍ ደረጃ የመብት ማስከበሪያ መንገድ ሆኖ የተወሰደውና በስራ ላይ የዋለውም በቅኝ ገዥዎች ሉዓላዊነታቸውንና ነፃነታቸውን በኃይል ተነጥቀው የነበሩ ሀገሮች ከቅኝ አገዛዝ ነፃ እንዲወጡ የሚያስችል መሆኑ ስለታመነበት ነበር፡፡ ቅኝ አገዛዝ ደግሞ አንድ የራሱ ነፃ መንግስት ያለው ሉዓላዊ ሀገር በሌላ መንግስትና ሀገር ወረራ ሉዓላዊነቱንና ነፃነቱን የተነጠቀበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው፡፡ የራስን እድል በራስ የመሰወን መብት ደግሞ ይህንን በሌላ ጉልበተኛ መንግስት በግድ የተነጠቀ የሀገር ሉዓላዊነትና የነፃ መንግስት ሕልውና መልሶ የማግኘት መብት በቅኝ ገዥዎቹ መልካም ፈቃድ ሳይሆን በራሳቸው በቅኝ ተገዥዎቹ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ መወሰን ያለበት መሆኑን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ መብት ከቅኝ ገዢዎቹ አስተዳደራዊ ትስስር በመገንጠል የራስን ነፃ መንግስት እስከመመስረት ድረስ የሚያደርስ መሆኑንም ያመለክታል፡፡*

*ከዚሁ ጎን ኮሚኒስቶች ለፀረ-ቅኝ አገዛዝና ፀረ-ካፒታሊዝም ትግል፣ ለወዛደራዊ አለማቀፋዊነትና ለሶሻሊዝም ስርዓት ምስረታ ጠቃሚ ፅንሰ ሀሳብ እንደሆነ በመቀስቀስ ከራሳቸው ርዕዮተ ዓለማዊ ቅኝት አንፃር በሰፊው ሲያስተጋቡት ቆይተዋል፡፡ በተለይ ደግሞ የሩሲያ ኮሚኒስቶች በዛሩ አገዛዝ ዘመን በታላቁ ፒተር አማካይነት በሩሲያ ግዛት ስር በሀይል የተጠቃለሉት ሩሲያዊ ያልሆኑ ሕዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብት እስከመገንጠል ከተከበረላቸው በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሕብረት ፈጥረው አብሮ ለመኖር ይችላሉ የሚለውን አስተሳሰብ በመያዝ ይኸንኑ በስራ ለመተርጎም ሞክረዋል፡፡ በዚህም መሰረት የጥቅምቱ ሶሻሊስት አብዮት ድል አደረገ እንደተባለ በቀድሞዋ ሩሲያ አገዛዝ ተፅዕኖ ስር የነበሩ ሕዝቦች የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመሰወን መብታቸው እስከመገንጠል ድረስ የተረጋገጠ መሆኑ ታወጀ፡፡ እ.ኤ.አ. ጥቅምት* 2 *ቀን* 1917 *ይህ አዋጅ እንደታወጀ በዚሁ ዓመት ህዳር ወር ውስጥ የዩክሬይንና የፊንላንድ ነፃ መንግስት መሆን እውቅና አገኘ፡፡ በዚህ አይነት «እየተለያዩ እንደገና መገናኘት ይቻላል» በሚል አስተሳሰብ በመጓዝ የተወሰኑ ግዛቶች በአንድ ላይ ተሰባስበው በህዳር* 1922 *የተባበረች ሶቭየት ሶሻሊስት ሪፐብሊክን ማቋቋማቸው ይፋ ሆነ፡፡ «ለአንድነት ሲባል መለያየት»* (Disunity for the sake of unity) *የሚባለው የሌኒን አመለካከት በጊዜ ሂደት ውስጥ* 15 *የሕብረቱ አባል ግዛቶችን ያቀፈ መንግስት ለማቋቋም በማስቻሉ የኮሚኒዝም ቲዎሪ ያስገኘው ድል ሆኖ በሰፊው ተሰበከ፡፡ ይሁንና በዚያች አገር የጭቆና አገዛዝ ከቀድሞው በተለየ መልኩ ተተክሎ የሰዎችን መብትና ነፃነት በአስከፊ ሁኔታ መደፍጠጡን በመቀጠሉ ብዙ የተነገረለት ድል እ.ኤ.አ በ*1991 *አካባቢ በሚያስገርም ሁኔታ እንዳልነበረ ሆኖ በሽንፈት ተደመደመ፡፡*

*እነሌኒን «የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል» የሚል ድንጋጌ በሕገመንግስታቸው ሲጽፉ መነሻ ያደረጉት ሀሳብ የአሁኖቹ የኢትዮጵያ ገዥዎች በፃፉት ሕገመንግስት አንቀጽ* 39 *ለምን እንደተደነገገ ከሚያቀርቡት ምክንያት ጋር አንድ አይነት ነው፡፡ እነሌኒን ይኸንን ድንጋጌ ማስፈር የፈለጉት የተለያዩ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የዚህ ዓይነት ሕገመንግስታዊ ዋስትና ሲረጋገጥላቸው በፈቃዳቸውና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ይመሰርታሉ፣ የመገንጠል ሕገመንግስታዊ መብት እንዳላቸው ሲያውቁ የመገንጠል ጥያቄ ማንሳታቸው ይቀርና አብሮ ለመኖር የሚያስችል መተማመን በመካከላቸው ይሰፍናል የሚል አስተሳሰብ ነበር፡፡ የሕወሓት/ኢህአዴግ መሪዎችም ስለአንቀጽ* 39 *የሚያቀርቡት ምክንያት ይኸንኑ ነው፡፡ ሁለቱም ስለፅንሰ ሃሳቡ ተገቢነት ከሚሰጡት ምክንያት ባሻገር ተግባር ያረጋገጠው ሀቅ ግን ሌላ ነው፡፡ በሶቭየት ሕብረት ሕገመንግስት*

የተገፈው ይህ ድንጋጌ የሕብረት መንግስት ለመሰረቱት ሕዝቦች መብት መጠበቂያ ዋስትና ሳይሆናቸው በመቅረቱ የታሰበው መተማመን ሳይፈጠር ቀረ፡፡ የመገንጠሉም ጥያቄ የሚነሳበት ምክንያት ስለተፈጠረ የመሰረቱትን የሕብረት መንግስት እንደ እንቧይ ካብ አፈራርሰው ብትንትናቸው ወጣ፡፡ ወደ 70 ዓመታት ለሚጠጋ ጊዜ ገነባን ያሉት ዴሞክራሲ፣ ብልፅግናና አለም አቀፍ ዝና በአንዴ በመትነኑ በአሁኑ ጊዜ ከሩሲያና ከሌሎቹ ሁለትና ሶስት ግዛቶች በስተቀር ሌሎቹ ወደድህነት ደረጃ ወርደው ዓለም አቀፍ ምፅዋት ከሚሰፈርላቸው ሀገሮች ተራ ተሰልፈዋል፡፡ አንዳንዶቹ ከተገነጠሉ በኋላ ሰላማዊ ጎረቤቶች እንኳ መሆን ተስኗቸው ወደባላንጣነት ተሸጋግረዋል፡፡ አንዱ የሌላውን ተቃዋሚ እያደራጀና እያስታጠቀ በመውጋት ሁልጊዜ ጦርነት የሚቀሰቀስባቸውና አለመረጋጋት የነገሰባቸው ሆነዋል፡፡ ሩሲያን ጨምሮ ሌሎቹም ከሕብረቱ ተገንጥለው የወጡ ግዛቶች እንደገና ከውስጣቸው በተፈጠሩና የመገንጠል ጥያቄ በሚያነሱ ተፋላሚዎች ሰላማቸው አደጋ ላይ እንደወደቀ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ያለው የ12 ዓመታት ልምድ ብቻ ቢሆንም «ለአንድነት ሲባል መለያየት» የሚለው የሌኒን ፍልስፍና ለእኛ ሁኔታም ጠቃሚ ውጤት እንደማያስገኝ በተጨባጭ እየታየ ነው፡፡ የአሁኑ አገዛዝ የመንግስት ስልጣን ከመንጠቁ በፊት ከነበረበት የአማጺነት ዘመኑ አንስቶ እስካሁን ድረስ እንደትልቅ የመብት ማስጠበቂያና በእኩልነት ላይ ለሚመሰረት አንድነት መተማመኛ አድርጎ የሚያቀርበው ነጥብ ይኸው የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል» የሚለው ሲሆን በነሐሴ 1987 በወጣው ሕገመንግስትም እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ይሁን እንጂ የሕዝብ መብት ማስጠበቂያና የአንድነት መተማመኛ ሊሆን ቀርቶ ሌሎች አዳዲስ ችግሮችም እንዲፈጠሩ ምክንያት እየሆነ ነው፡፡ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚገናኙባቸውን ነጥቦች ላለማየት አይናቸውን እየጨፈኑ የሚለያዩበትን መስመሮች ብቻ እንዲመለከቱ መንግስታዊ ግፊት እየተደረገባቸው ነው፡፡

ከኢትዮጵያዊ ማንነት ይልቅ የጎሣ ማንነት የበለጠ መሆኑ በሰፊው ይሰበካል፡፡ የኢትዮጵያዊነት ምልክትና የሀገሪቱ ነፃነት አርማ የሆነው ሰንደቅ ዓላማ እንደማንኛውም ተራ ጨርቅ ሆኖ እንዲታይ ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል፡፡ በዚህ የአንድነትና የነፃነት ምልክት ከሆነ ብሔራዊ አርማ ይልቅ የአሁኑ አገዛዝ እያዘጋጀ ለሚያድላቸው የየጎሣው ሰንደቅ ዓላማዎች የተለየ ክብር እንዲሰጣቸው የሚደረግበት ሁኔታ አለ፡፡ የአክሱም ሀውልት ለሌላው ኢትዮጵያዊ ምኑም እንዳልሆነ ለማሳመን ይሞከራል፡፡ እስካሁን በሕዝብ ትግል የተገነባው ታሪክ ሁሉ ተረት ተረት እንደሆነ ተደርጎ ነው በየአጋጣሚው የሚገለፀው፡፡ በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል የነበረው ግንኙነት የቅኝ ግዛት ግንኙነት እንደነበረ ተደርጎ ታሪካዊ መሠረት የሌለው ቅስቀሳ ይካሄዳል: በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ ለኢትዮጵያዊ ማንነትና ለኢትዮጵያ ታሪክ ተገቢውን ትኩረት የሚሰጥ ሀሳብ አልተካተተም፡፡ በአጭሩ የሕዝቡን ዝምድናና ትስስር በሚገባ ያሳያሉ በሚባሉና በሕዝቡ የጋራ ጥረት በተገነቡ ብሔራዊ እሴቶች፣ የታሪክ ቅርሶችና የባህል ትውፊቶች ላይ የሚደረገውን ትኩረት የማዳከም ሰፊ ዘመቻ ይካሄዳል፡፡ በአጠቃላይ መልካም የሆኑትን የግንኙነት እሴቶች በማጥላላት፣ በተዛባ መንገድ በመተርጎምና በዋናነት በታሪካችን ውስጥ ለታዩ መጥፎ ክስተቶች ብቻ ትኩረት በመስጠት ሕዝቡ በዋናነት ወደሚለያዩት ጉዳዮች እንዲመለከት በተለያየ መንገድ ከፍተኛ ጫና እየተደረገ ነው፡፡

ከዚህ በፊት የተገነባውን መልካም ነገር በሙሉ ከመሰረቱ እያፈረሱ ሌላ መልካም ነገር መገንባት አይቻልም፡፡ የሀገር ግንባታ ስራ በረጅም ጊዜ ሂደት የሚከናወን ነው፡፡ መንግስት ሲቀየር እየፈረሰ ሁልጊዜ ከዜሮ የሚጀመር ስራ አይደለም፡፡ ካለፈው የሚጎዳውን እየተው የሚጠቅመውን መቀበል፣ የዛሬውን በትናንቱ ላይ መመስረትና ለመጪው ማስተላለፍ በሀገር ግንባታ ሂደት የተለመደ አሰራር ነው፡፡ በአሁኑ አገዛዝ የተያዘው ደግሞ ከዚህ በፊት ኢትዮጵያ እንዳልነበረች በመቁጠር ገና አዲስ ኢትዮጵያን እንፈጥራለን የሚል አቋም ነው፡፡ በዚህም አስተሳሰብ በመመራት ሀገርን የሚያክል ነገር እያፈረሱ ለመካብ ሙከራ እየተደረገ ነው፡፡

በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 39 የሰፈረው የራስን እድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል ሕጋዊ ድንጋጌ መሆኑ በሕዝቦች መካከል በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት እንዲፈጠር ይረዳል የተባለው ግምት የሚሰራ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ይህ አንቀፅ በመኖሩ በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች መካከል መተማመን ስለሚፈጠር የመለያየት ስጋት ይወገዳል የሚለው መላምት በተግባር ሊገለጥ የማይችል ሆኖ ቀርቷል፡፡ ይህ አንቀፅ ሕገመንግስታዊ ድንጋጌ በመሆኑ የተገነባ መተማመን፣ በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ዝምድናና የተጠበቀ መብት አለ ብሎ ለመናገር የሚያስችል ምልክት

እንኳ አልታየም። በእርግጥ አገዛዙ የስልጣን ጊዜውን እንዲያራዝምና በስርዓቱ የተለያዩ መዋቅሮች የተሰገሰጉት ግብረበላዎች ከዜሮ ተነስተው ትላልቅ ከበርቴዎች እንዲሆኑ አስችሏቸዋል። ራሳቸውን የብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ወኪል እያደረጉ የሾሙ የዚህ አገዛዝ ምልምሎች እንወክለዋለን የሚሉትን ሕዝብ ለመግዛት የሚያስችል ሕጋዊ መሰረት አግኝተናል የሚሉት አንቀፅ 39ን እየጠቀሱ ቢሆንም እውነቱ ሌላ ነው። ማንኛውም የክልል ሹም ለስርዓቱ ያለው ታማኝነት በሕወሓት/ኢህአዴግ መመዘኛ እየተለካ ተመልምሎ ከመመደቡ በስተቀር ነፃና ሀቀኛ በሆነ የምርጫ ውድድር በሕዝብ የተመረጠ አይደለም። በመሆኑም በተመደበበት ክልል ውስጥ ለሥልጣን መልምሎ የመደበውን ሥርዓት የፖለቲካ አጀንዳ ከማስፈፀም ውጪ የሕዝቡን መብትና ነፃነት የሚያረጋግጥ ቁምነገር ለመስራት የሚያስችል አቅምና ፍላጎት የለውም። እንኳን የሕዝብ መብትና ነፃነት ሊያስከብር ይቅርና እያንዳንዱ የክልል ሹም የራሱ መብትና ነፃነትም እየተሰፈረ የሚሰጠው ከሕወሓት/ኢህአዴግ ከፍተኛ መሪዎች ምንአልባትም ከሕወሓት/ኢህአዴግ ሊቀመንበር ነው።

በመጨረሻ መነሳት ያለበት ሌላው ነጥብ የመገንጠል መብት የተሻለው የመብት ማረጋገጫ መፍትሔ ተደርጎ የሚታይበት አመለካከት ራሱ የተሳሳተ መሆኑ ነው። አንድ ሕዝብ አንድ ላይ ተሳስሮ ለመኖር የማያበቃ ሁኔታ ሲያጋጥመው የመገንጠል መብቱን ተጠቅሞ በመለየት አስተማማኝ ሰላም፣ ዘላቂ ልማትና የተሟላ ዴሞክራሲ እንደሚጎናፀፍ አድርጎ ማመን በራሱ ትክክል አይደለም። ጭቆናንና በደልን በሽሽት ለማምለጥ አይቻልም። አንዱን ጭቆና ሲሸሹ ሌላ ጭቆና እንደማያጋጥም ምንም መተማመኛ የለም። ከጭቆናና ከበደል ለመዳን የተሻለው መፍትሔ እየሸሹ ለማምለጥ መሞከር ሳይሆን ጭቆናና በደልን እዚያ ባለበትና በተገኘበት ስፍራ እየታገሉ ድል በመንሳት ብቻ ነው። አለበለዚያ ከአስከፊ ከአገዛዝ ሸሽቶ በሌላ ጨቋኝ አገዛዝ ስር መውደቅ ይመጣል።

ኤርትራ ከኢትዮጵያ በመገንጠሏ የዴሞክራሲ ደሴት፣ የሰላም ተምሳሌትና የፈጣን ልማት ምልክት ለመሆን አልቻለችም። ከቀድሞው የከፋ የጭቆና አገዛዝ ተቀብላት። ከጎረቤቶቿ ጋር ብቻ ሳይሆን ከራሷም ጋር ሰላም መፍጠር ያልቻለች የትርምስ ሀገር ሆናለች። የኤርትራ ሕዝብ እንደገና ከአዲሱ ጭቆናና ግፍ ጋር ግብ ግብ ለመግጠም ተገዷል። ከአገዛዝ ወጥቶ በሌላ አገዛዝ ቀንበር ስር ወድቆ እየዳከረ ነው። አገዛዝን እዚያው ባለበት ገጥሞ ማሸነፍ ካልተቻለ ሸሽቶ ማምለጥ አይቻልም። ኢስት ቲሞር ከኢንዶኔዥያ በመገንጠሏ የተሟላ ሰላም አልተፈጠረም። የሶቭየት ሪፑብሊኮች ስለተገነጠሉ ሁሉም ነገር አልጋ ባልጋ አልሆነም።

ስለዚህ የመገንጠል መብት ሕገመንግስታዊ ዋስትና ስለተሰጠውና መገንጠል የሚፈልግ እየተገነጣጠለ መብቱንና ነፃነቱን የሚያስጠብቅበት የገነት መንገድ እንደተመቻቸለት አድርጎ ማየት ራሱ ችግር ያለበት የመፍትሔ አማራጭ ነው። ከዚህ ሁሉ ዙሪያ ጥምጥም የተሻለውና ቀጥተኛው መፍትሔ የዴሞክራሲ ስርዓት መፈጠር ነው። የዴሞክራሲ ስርዓት ባለበት ሁኔታ እራስን በራስ የማስተዳደር መብት መረጋገጡ የማያጠራጥር ስለሚሆን ሌላ ዋስትና አስፈላጊ አይሆንም። የመብት ማስጠበቂያው ሁነኛ ዋስትና የአገዛዝ ስርዓት መወገድና የዴሞክራሲ ሥርዓት መመስረት ብቻ ነው።

ኢዴፓ የሕገመንግስቱን አንቀፅ 39 የሚቃወመው ዝም ብሎ ሕወሓት/ኢህአዴግን ለመኮነን አይደለም። እስካሁን በተዘረዘሩት የመርህና የአመለካከት ልዩነቶች ላይ በመመስረት ነው። ይህ አንቀፅ ለኢትዮጵያ ሁኔታ የግለሰብም ይሁን የቡድን መብት ማስጠበቂያ መፍትሔ ሆኖ እንደአማራጭ የሚቀርብበት በቂ የቲዎሪም ሆነ የተግባር ማረጋገጫ እንደሌለ በማመን ነው። ኢዴፓ ይህንን አንቀጽ ሲቃወም ዋና መነሻ የሚያደርገው ጭቆናና በደል የተፈፀመበት ቋንቋና ባህል በኢትዮጵያ ውስጥ የለም በሚል አይደለም። ወይንም የተለያዩ ቋንቋዎችና ባህሎች ሊጠበቁ፣ እንክብካቤ ሊደረግላቸውና ሊከበሩ አይገባም በሚል አስተሳሰብም አይደለም። ወይንም ሕዝብ እራሱን በራሱ የማስተዳደር መብት በተሟላ መንገድ ሊከበርለት አይገባም፣ በመብት ላይ መጠነኛ ገደብ ማስቀመጥ ይገባል ከሚል አስተሳሰብ አይደለም። ወይም ደግሞ የሕዝቦች አንድነት በፍላጎትና በፈቃደኝነት፣ በእኩልነትና በመተማመን፣ በጋራ ጥቅምና በመከባበር መርህ ላይ መመስረት አይገባውም ከሚል አስተሳሰብ በመነሳት አይደለም። ኢዴፓ ይህንን አንቀፅና የቋንቋ መስመርን ተከትሎ የተቋቋመውን ፌዴራላዊ አደረጃጀት የማይቀበለው እነዚህ አማራጮች ከተሳሳተ ግምገማ ላይ ተመስርተው ወደተሳሳተ መደምደሚያ የደረሱ በመሆናቸው ነው።

ገዥዎቻችን በኢትዮጵያ ውስጥ በፊትም ሆነ አሁን ላሉት የመብት ረገጣዎች ዋና መንስኤ የሚያደርጉት የአገዛዝ ስርዓትን ሳይሆን ራሱ የአገዛዝ ስርዓት ሰለባ የሆነውን ሕዝብ ስለሆነ ነው። መፍትሔ የሚሉት ደግሞ የነበረውን ችግር የሚያቃልል ሳይሆን ተጨማሪ ችግር የሚወልድ፣ በእኩልነትና በፍላጎት የተመሰረተ አንድነትና ዝምድና የሚፈጥሩ ሳይሆን ይበልጥ ወደሚያለያይና ወደሚከፋፍል ዘረኛ ፉክክር ውስጥ የሚያስገባ አማራጭች በመሆኑ ነው። ኢዴፓ እነዚህን አማራጮች የሚቃወመው የኢትዮጵያን ሕዝብ ካስተሳሰሩት የጋራ ታሪኮች፣ ባህላዊ ትውፊቶች፣ ጥቅሞች፣ ፍላጎትና እምነቶች ይልቅ ለልዩነት መጠናከር አስተዋፅኦ ለሚያደርጉት ጉዳዮች ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ወደሚያገናኙት ሳይሆን ወደሚለያዩት አቅጣጫዎች እንዲሳብ የማድረግ አላማ አላቸው ብሎ ስለሚያምን ነው። ኢዴፓ የሚያምነውና ለሁሉም ወገኖች መብትና ነፃነት መጠበቅ የተሻለ ዋስትና እንደሚሆን የሚቀበለው እስካሁን ድረስ ለታዩት፣ አሁንም ገና ላልተወገዱት የመብት ረገጣዎች መንስኤ የሆነውን ችግር ተገንዝቦ ከምንጩ ማድረቅ ይገባል የሚለውን አማራጭ ነው። መገንጠል ለኢትዮጵያ ሕዝብ መብት መከበር ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ ትናንሽ መንግስታት እየፈጠሩ ራሳቸውን ፕሬዚዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትር አድርጎ ለመሾም ለሚያቅዱ የሥልጣን ጥመኞች የሚሰጠው እርካታ የበለጠ ነው። ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል የተወሰደው እርምጃ ሁለቱንም ሕዝቦች ከድህነት አላላቀቀም። ሁለቱንም ሕዝቦች የዴሞክራሲ ስርዓት ባለቤት አላደረገም። ያስገኘው ውጤት ካለ በአንድ ሀገር ተጠቃሎ የነበረውን የአገዛዝ ስርዓት ለሁለት በመክፈል ሁለት አምባገነን ሥርዓቶች እንዲፈጠሩ ማድረጉ ነው። አዳዲስ ፕሬዚዳንቶች፣ ጠቅላይ ሚኒስትሮች፣ የሲቪልና የጦር ሹማምንቶች፣ የለተያዩ ሰንደቅ ዓላማዎችና አርማዎች ከማስገኘት ሌላ ለሕዝቦች ያስገኘላቸው መልካም ነገር የለም።

## 2.6 ማጠቃለያ

በኢዴፓ እምነት የዚህች ሀገር ሕልውና እንዲቀጥል፣ የሕዝቡ ሰላም፣ ልማትና ብልፅግና እንዲረጋገጥ ከሁሉ በፊት ሀገሪቱ እንደሀገር እንዴት ትኑር በሚለው ጉዳይ ላይ አንድ አይነት ብሔራዊ መግባባት መፍጠር ያስፈልጋል። ሀገሪቱ እንደሀገር ልትኖር የምትችልበትን አማራጭ የማቅረብ ጉዳይ ደግሞ ሥልጣን የያዘ ወይም በተቃዋሚነት የቆመ የፖለቲካ ኃይል ኃላፊነት ብቻ ተደርጎ የሚታይ አይደለም። የዚህች ሀገር ሕልውና የሚያገባቸውን ሁሉንም ወገኖች የሚመለከት የጋራ አጀንዳ ነው። የሀገሪቱ ህልውና የሚመለከታቸው ወገኖች ደግሞ አማራጮች እንዳሏቸው የታወቀ ነው። እነዚህ ሁሉ በግልጽ ወጥተው ብሔራዊ አጀንዳ ካልሆኑና ነፃ ውይይት ተደርጎባቸው አንድ ብሔራዊ መግባባት ካልተፈጠረ ይህቺ ሀገርና ይህ ህዝብ ሥልጣን በኃይል የሚጨብጡ አገዛዞች በየተራ የሚያቀርቧቸው የማይረቡ አማራጮች መሞከሪያ ሆነው ለረጅም ጊዜ ባሉበት እየረገጡ መቆየታቸው የማይቀር ነው። የሀገርን ሕልውናና የሕዝብን እድል የመወሰን ኃላፊነት የአሸናፊዎች ብቻ መሆኑ እስካልተቋረጠ ድረስ ከገባንበት የችግር አዙሪት መውጣት አንችልም። ሁሉም ወገኖች የሚያቀርቡትን አማራጭ ለሕዝብ ይፋ ውይይት አቅርቦ ሀገሪቱ እንዴት ትኑር በሚለው ነጥብ ላይ ብሔራዊ መግባባት ካልተፈጠረ እያንዳንዱ የኃይል አገዛዝ አለኝ የሚለውን አማራጭ ተራ በተራ ሞክሮ እስኪጨርስ ጊዜ ድረስ ሀገሪቱ ቁማ መቅረት የለባትም።

ሕዝብን ቤተሙከራ ማድረግ ደግሞ በኃይማኖት፣ በሞራል፣ በሳይንስና በማንኛውም ማህበራዊ ሕግ ተቀባይነት የለውም። አገዛዞች በሙሉ አንድ የጋራ ባህርይ አላቸው። ሁሌም በሕዝብ ላይ በኃይል የሚጭኑትን አማራጭ «ብቸኛ ፣ አንድና አንድ፣ ተወዳዳሪ የማይገኝለት» ወዘተ.. እያሉ መጥራት ይቀናቸዋል። ከዚህም አልፈው እነሱ ከሥልጣን ከተወገዱ ሀገር እንደሚፈርስና ሰላም እንደሚደፈርስ በማስፈራራት ስልጣናቸው ተቃውሞ እንዳይነሳበት ለማድረግ ይሞክራሉ። በዚህ መንገድ የስነልቦና ሽብር እየፈጠሩ ሀገርና ሕዝብን መያዣ (hostage) አድርገው ስልጣናቸውን ለማቆየት የሚችሉትን ሁሉ ጥረት ያደርጋሉ። በአፄው ዘመን በኃይማኖት ተቋማት ጭምር እየታገዘ የሚካሄድ ሰፊ የስነልቦና ዘመቻ ነበር። በእርሳቸው ስልጣን ላይ ጥያቄ ማንሳት ፈጣሪን እንደመጋፋት ተደርጎ እንዲታይ ለማድረግ ብዙ ተደክሟል። በደርግ ጊዜም ከሶሻሊዝም ሌላ ለሀገሪቱ የሚቀርብ አማራጭ ሊኖር እንደማይችል ለማሳመን ሰፊ ቅስቀሳ ተደርጓል። የአሁኑም አገዛዝ እኔ ከሌለሁ ሀገሪቱ እንደሶማሊያ ትሆናለች እያለን ነው። አንቀፅ 39 በሕገመንግስቱ ውስጥ ካልሰፈረ ይህቺ ሀገር የሚጠ ብቃት እድል የሶማሊያ ዓይነት መበታተን ነው ይላል። ይህ ባህርይ የሁሉም አገዛዞች የጋራ ባህርይ መሆኑ የታወቀ ነው። ራሳቸውን ዘላለማዊ ለማድረግ መፍጨርጨርና የእነርሱ ውድቀት የአለም

ፍፃሜ እንደሚሆን ለማሳመን መሞከር ዋነኛው የአገዛዞች ባህርይ ነው፡፡ ከካሙዙ ባንዳ በኋላ ማዕከላዊ አፍሪካ ሪፑብሊክና ሕዝቧ እየኖሩ ነው፡፡ ከሂትለር በኋላ ጀርመንና ሕዝቧ መኖር ቀጥለዋል፡፡ ከሞሶሎኒ በኋላ ኢጣሊያና ሕዝቧ አሉ፡፡ ከሣዳም በኋላም ኢራቅ እየኖረች ነው፡፡ በእኛም ሀገር ቢሆን የሆነውና ወደፊትም ሊሆን የሚችለው ከዚህ አጠቃላይ ሕግ የተለየ አይደለም፡፡ ነገር ግን ሕወሓት/ኢህአዴግ እርሱና አንቀፅ 39 ከሌሉ ሀገርና ሕዝብ አይኖሩም ማለቱን እንደቀጠለ ነው፡፡ ራሱን ብቸኛው ሀገር ጠባቂና የእርሱ አማራጭ ምትክ የማይገኝለት እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ የሌሎች አማራጭ ሀገር በታኝ ነው እያለ ነው፡፡

ለዚህ ግትር አቋም አለመለወጥ ዋናው ምክንያት የራሱ የአገዛዙ ፀረ-ዴሞክራሲ ባህሪይ ቢሆንም የተሻለ አማራጭ አለን የሚሉ ወገኖች በዚህ ወሳኝ የሀገር ሕልውና አጀንዳ ላይ ግልጽ ውይይት አድርገው ብሔራዊ መግባባት አለመፍጠራቸውም ሌላው ምክንያት ነው፡፡ ሀገሪቱ ከጥፋት እንድትድንና ሕዝቡም ከጭቆና አገዛዝ እንዲገላገል በፀረ-ዴሞክራሲ አገዛዝ ላይ የተቀናጀ ተፅዕኖ ማሳረፍ የሚያስችል ብሔራዊ መግባባት ፈጥሮ የተሻለ አማራጭ መኖሩን ማሳየት ያስፈልጋል፡፡

በኢዴፓ እምነት ሁሉም ኢትዮጵያዊ በመረጠው መንገድ መደራጀትና የመሰለውን አማራጭ ማቅረብ የማይደፈር መብቱ ነው፡፡ ከዚህ ጎን ደግሞ ለሁሉም ምኞትና ተስፋ ማስተሳሰሪያ ሆኖ የሚያገለግል ሀገርና ዴሞራሲያዊ የፖለቲካ ስርዓት መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ ከእነልዩነቶቻችን ተቻችለን የምንኖርበት የጋራ ሀገርና ስርዓት ለመፍጠር ሀገራዊ በሆኑ አጀንዳዎች ላይ ግልጽ ውይይት ማድረግና ብሔራዊ መግባባት መፍጠር ይገባናል፡፡ ወደዚህ ብሔራዊ መግባባት ለመምጣት ካልቻልን ለአገዛዝ ስርዓቱ ይበልጥ እየተራራቅንና እየተዳከምን ለአገዛዝ የምንመች ሆነን እንድንኖር ማድረጉን አይተውም፡፡ ኤዴፓ በኢትዮጵያ ውስጥ አሉ የሚባሉት የባህል፣ የቋንቋ፣ የኃይማኖት፣ የአመለካከትና ሌላም ልዩነቶች ብሔራዊ መግባባት እንዳንፈጥር የሚከለክሉ ናቸው ብሎ አያምንም፡፡ ምክንያቱም ከልዩነታችን በላይ የሚያገናኙን የጋራ ጥቅሞች፣ ፍላጎቶችና አላማዎች ብዙ ናቸው፡፡

ያለፈው የጋራ ታሪካችን በልዩነት፣ በፍጥጫና በግጭት ብቻ የተሞላ አድርገን ማየታችንን እየተውን በዝምድና፣ በትስስርና በአንድነት የታጀበ እንደነበርም ማመን በዘላቂነት እንዲጠናከር ለምንፈልገው ብሔራዊ መግባባት መንገድ ጠራጊ እርምጃ ሊሆን ይችላል፡፡ ያለፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግንኙነትና አንድነት በኃይል ብቻ የተመሰረተ ግንኙነትና ዝምድና እንደሆነ ተደርጎ የሚገለፅበትን ጎደሎ አቀራረብ እየተውን ወይንም ግንኙነቱ የአንድ ነጠላ ክስተትና የአንድ ጊዜ ድርጊት ውጤት ሳይሆን የብዙ ተደራራቢ ክስተቶችና የረጅም ጊዜ ሂደት ውጤት እንደነበር መተማመን ለዘላቂ የሕዝብ ግንኙነት ሌላው ጠቃሚ እርምጃ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕልውናና የሕዝቡ አንድነት ታላቁ ፒተር ሩሲያን፣ ቢስማርክ ደግሞ ጀርመንን፣ ወይንም ጋሪባልዲ ኢጣሊን በገነቡበት የኃይል መንገድና የዛሬ አንድ መቶ ዓመት ገደማ በአፄ ምኒሊክ አገዛዝ ወቅት በተከናወነ ድርጊት ብቻ የተፈጠረ አድርጎ መግለፅ የታሪክን ሚዛን የጠበቀ እንዳልሆነ መስማማት ተገቢ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ግንኙነት በ16ኛው ክፍለ ዘመን በግራኝ አህመድ በተመራው እንቅስቃሴና በኦሮሞ ፍልሰት ብቻ የተፈጠረ አድርጎ ማቅረብም የታሪኩ ሙሉ ገጽ እንዳልሆነ መተማመን ያስፈልጋል፡፡ ያለፈው የኢትዮጵያ ሕዝብ ግንኙነትና አንድነት በሰላምና በጦርነት፣ በንግድና በኃይማኖት፣ በጋብቻና በፍልሰት ወዘተ.. ከሁሉም ማዕዘናት እየተነሳ ወደሌላው ማዕዘን በተካሄደ መደባለቅና መዋሃድ በተራዘመ ጊዜ የተፈጠረ መሆኑን መቀበል ይገባል፡፡ በውስጥ በሚፈጠሩ በርካታ ምክንያቶች አንዱ በሌላው መኖሪያ ላይ ሲደረብ፣ ከሌላው ጋር ሲደባለቅና ሲሳሳብ የተመሰረተ የጋራ ባህል፣ ኃይማኖትና ማንነት መኖሩ ብቻ ሳይሆን የውጭ ወረራንና ግፊትን በጋራ በመመከት የተገነባ ዝምድናና አንድነት መሆኑን መተማመን ይጠቅማል፡፡ በዚህ ሁሉ መንገድ የተመሰረተ የሕዝብ አንድነትና ኢትዮጵያዊ ማንነት አለ፡፡ በረጅም ጊዜ ሂደትና በተለያዩ ወስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች ግፊት የተፈጠረው የሕዝብ ትስስርና አንድነት መጥፎም ጥሩም ገጽታዎች የነበሩት እንደመሆኑ ካለፈው ታሪካችን መጥፎውን እያረሙ ጥሩውን ደግሞ መነሻ እያደረጉ የአሁኑንና የወደፊቱን ዝምድና ይበልጥ ሊያጠናክሩ በሚችሉ የጋራ እሴቶች ላይ ትኩረት መስጠት መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህ ሁሉ በላይ በረጅሙ ታሪካችን ውስጥ የታየው አንድ ትልቅ ጉድለት ከአገዛዝ ስርዓት ተላቀን የዴሞከራሲን መንገድ ሳንይዝ መቆየታችን ነው፡፡ የአገዛዝ ስርዓት ደግሞ የሕዝቡን መብትና ነፃነት እየገፈፈ እጅግ ከሚያሳፍር የድህነትና የኋለቀርነት ሰልፍ እንዳንወጣ አድርጎናል፡፡ በተጨማሪም የአገዛዝ ስርዓት አማካይነት በሕዝብ ላይ ለደረሰውና እየደረሰ ላለው የመብት ረገጣና የነፃነት

መገፈፍ መንስኤው ራሱ የአገዛዝ ሥርዓት ቢሆንም አንዱ ሕዝብ በሌላው ሕዝብ ላይ በደል አድርሷል፣ የአንዱ ሕዝብ ባህልና ቋንቋ የሌላውን ረግጦታል እየተባለ ሕዝብን በሕዝብ ላይ ለማነሳሳት የሚካሄደው ዘረኛ ቅስቀሳ የችግሩን እውነተኛ ባህርይ ደብቆታል። የአገዛዝ ስርዓት በፈፀመው ጭቆናና በደል ራሱ ከጭቆና ማምለጥ ያልቻለውን ሕዝብ ተጠያቂ እያደረጉ መውቀስና መክሰስ የችግሩን ምንጭ ለማድረቅ የሚያግዝ አይደለም። ስለዚህ ከሁሉም በፊት ለአገዛዝ ሥርዓት መውደቅና ለዴሞክራሲ ስርዓት መመስረት ቅድሚያ ትኩረት መስጠት አለብን። ይህ ሲባል ግን ሰላምና ልማት ምንም ድካምና ጥረት ሳይጨመር በራሳቸው ይሟላሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን የዴሞክራሲ ስርዓት ባለበት ሁኔታ ሰላምንና ልማትን ለማረጋገጥ ከዚህም ጋር ጠንካራ የሕዝብ አንድነትና ቋሚ ዝምድና ስር እንዲሰድ ለማድረግ የሚመች ምዕራፍ ይከፈታል ለማለት ነው። ለማንኛውም ዓይነት ችግር የሰከነ መፍትሔ ለመፈለግ የሚያበቃ አዲስ ባህል ይመሰረታል ለማለት ነው። እስካሁን ድረስ አንድ አይነት ችግር ለመፍታት ስንሞክር በሌላ ችግር እየተጠለፍን የምንወድቅበት አዙሪት ይበጠስና ወደፊት የምንራመድበት መንገድ ይጠረጋል ለማለት ነው። ከዚህ ውጭ ሺህ ጊዜ መፈክር ቢለወጥ፣ የራስን እድል በራስ የመሰወን መብት እስከመገንጠል እየተባለ ቢዘመር ትርጉም የለውም። የዴሞክራሲ ስርዓት በሌለበት ሁኔታ መብት የሚባል፣ ሕገመንግስታዊ ዋስትና የሚባል ነገር ዘበት ነው።

# 3. ፌዴራላዊ አደረጃጀትን በተመለከተ ኢዴፓ የሚከተለው አማራጭ

ገዥው ፓርቲ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት የቋንቋ ልዩነቶችን መሰረት ያደረገ ፌዴራሊዝም ነው ወደሚል መደምደሚያ እንዲደርስ ካስቻሉት የንድፈ ሃሳብ መነሻዎች ጀምሮ እስከተግባራዊ አፈፃፀሙ ድረስ ኢዴአፓ የመርህ ልዩነቶች አሉት። በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ካሉን ልዩነቶች መካከል ዋና ዋና የሚባሉት ቀደም ሲል በዚሁ ፅሑፍ ውስጥ በተወሰነ ደረጃ ተተንትነው ቀርበዋል። ከዚህ በኋላ ለማየት የሚሞከረው ደግሞ ኢዴፓ ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል ብሎ የሚያምነው ፌዴራሊዝም በምን መመዘኛዎች ላይ መመስረት እንደሚገባው ያቀረበውን አማራጭ ነው።

የመጀመሪያው መመዘኛ በኢትዮጵያ የሚመሰረተው ፌዴራሊዝም በሕዝብ ፍላጎትና ፈቃድ ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት የሚል ነው። በኢዴፓ እምነት የሀገሪቱን ፌዴራላዊ አደረጃጀት የሚወስነው አሁን በስራ ላይ ያለው ሕገመንግስት ራሱ በሕዝቡ ነፃ ውሳኔ የፀደቀ አይደለም። ይሁን እንጂ ሕገመንግስቱ በሕዝብ ውሳኔ ፀደቀም አልፀደቀም የአሁኑ አገዛዝ ተግባራዊ እያደረገው እንደመሆኑ በዚሁ ሕገመንግስት ውስጥ ተቀባይነት አግኝተዋል በተባሉ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መሰረት ቢያንስ በዚህ ብሔራዊ ጉዳይ ላይ ሕዝቡ የተለያዩ አማራጮች ቀርበውለት ግልጽ ውይይት እንዲያደርግና ነፃ ውሳኔ እንዲሰጥ መድረክ መዘጋጀት አለበት ብሎ ኢዴፓ ያምናል።

ሁለተኛው መመዘኛ በኢትዮጵያ የሚመሰረተው ፌዴራሊዝም የሕዝቡን ታሪካዊና ባህላዊ ትስስር እንደአንድ መመዘኛ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት የሚል ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ባህሎች፣ ኃይማኖቶችና አመለካከቶች ቢኖሩም ምንም አይነት የሚያስተሳስር ነገር በሌለበት ሁኔታ በየፊናቸው ተለያይተው የተቀመጡ ናቸው ማለት አይደለም። በዚህ ጽሑፍ ሌሎች ርዕሶች ስር ተደጋግሞ እንደተብራራው የኢትዮጵያ ልዩ ልዩ ሕብረተሰብ ክፍሎች በረጅም ጊዜ የታሪክ ሂደት ውስጥ የገነቡት የጋራ ባህልና ማንነት አላቸው። ልዩነቶቻቸውን አቻችለውና አስማምተው የሚኖሩበትን የጋራ ዝምድና መስርተዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የቋንቋ ልዩነት ገደብን እየሰበረና እየተቀላቀለ በአንድ ዓይነት የጂኦግራፊ ክልል ውስጥ በመኖር፣ የጋራ ታሪክና ባህል ሲገነባ እንደኖረ የሚያከራክር አይደለም። በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎችና ሂደቶች በአንድ አይነት ክልል ውስጥ የብዙ ቋንቋ ተናጋሪዎች ተደባልቀው በመስፈራቸውና ለረጅም ጊዜ አብረው በመኖራቸው የተነሳ ልሣነ ክልኤት በግልፅ ይንፀባረቃል። የባህልና የኃይማኖት መመሳሰልና የኢኮኖሚ መተሳሰር ተፈጥሯል። አማርኛ የአንድ ዓይነት ሕብረተሰብ ክፍል ቋንቋ ብቻ ከመሆን አልፎ በሀገሪቱ የሚገኙ አብዛኛዎቹ የሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚግባቡበት የመገናኛ ቋንቋ ሆኗል። ኦሮምኛ በተመሳሳይ መንገድ የአንድ ዓይነት ሕብረተሰብ ክፍል ቋንቋ ብቻ ከመሆን አልፎ በሀገሪቱ የሚገኙ በርካታ የሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች መግባቢያና መገናኛ ቋንቋ እየሆነ ነው። በርካታ ትግርኛ ተናጋሪች ባሉበት አካባቢ

የሣሆና ኩናማ ብቻ ሳይሆን ኩታ ገጠም የሆኑት የአማርኛና አፋርኛ ቋንቋዎች መግባቢያና መገናኛ ሆነው ያገለግላሉ። ሌሎችም ቋንቋዎች እንደዚሁ። በአንድ ዓይነት ጂኦግራፊ ክልል ውስጥ ሰፍረው ተመሳሳይ ባህልና ኃይማኖት የመሰረቱ የሕብረተሰብ ክፍሎች ማንነት በየፊናቸው በሚናገሩት የተለያየ ቋንቋ ብቻ ሳይሆን በጋራ በመሰረቱት ባህልና ኃይማኖትም ጭምር የሚገለጽ ነው።

ስለሆነም የኢትዮጵያን ፌዴራላዊ አደረጃጀትና የአስተዳደር ክልል ለመወሰን የሕዝቡን የታሪክና የባህል ትስስር እንደ አንድ መነሻ መውሰድ ያስፈልጋል ብሎ ኢዴፓ ያምናል። የቋንቋ ክልኤት ከመፈጠሩ ሌላ በተለያዩ ሁኔታዎች ሕዝቡ የመሰረተው የጋራ ትስስር የቋንቋን ልዩነት የተከተለ መስመር ለማበጀትና በዚህ ልዩነት ላይ ብቻ የሚቆም ፌዴራላዊ አደረጃጀት ሥርዓት ለመመስረት የሚመች አይደለም። ስለሆነም የሀገሪቱ የፌዴራል ሥርዓት መመስረት የሚገባው ሕዝቡ በታሪክ ሂደት በፈጠረው የጋራ ባህልና ማንነት ጭምር መሆን አለበት።

ሶስተኛው መመዘኛ በኢትዮጵያ የሚመሰረተው ፌዴራሊዝም ለሕዝቡ ቋንቋ መከበር፣ መዳበርና ማደግ ትኩረት የሚሰጥ ጭምር መሆን አለበት የሚለው ነው። በታሪክ ሂደት በሕዝቡ መካከል የተፈጠረ የጋራ ባህልና ማንነት ስላለ እያንዳንዱ የሕብረተሰብ ክፍል የራሱን ቋንቋና ባህል እርግፍ አድርጎ እንዲተው ወይንም አንድ ብቸኛ ቋንቋ፣ ባህል፣ ኃይማኖትና አመለካከት በሀገሪቱ እንዲሰፍን መደረግ አለበት ማለት አይደለም። እንደዚህ ለማድረግ መፈለግና መሞከር ዞሮ ዞሮ የሰውን ግለሰባዊ ነፃነት መግፈፍ ከመሆን አይዘልም። የጋራ ዝምድና የሚመሰረተውና የሚጠናከረው የግል ነፃነትን በማጣት ላይ ተመስርቶ ሊሆን አይችልም። መሆንም የለበትም። የጋራ ባህልና ማንነት ትርጉም የሚኖረው እያንዳንዱ ሰው እርስ በርሱ እንዲተሳሰር የሚያደርገው የጋራ ፍላጎት፣ ጥቅምና ዓላማ እንዳለው አምኖ ሲቀበለው ነው። የአንዱ ጥቅም መሟላት የሌላውን ጥቅም እንደማያጓድል፣ ያንዱ መብት መጓደል የሌላውን መብት የተሟላ እንደማያደርግ ሙሉ እምነት ሲፈጠር የጋራ ዝምድናና ትስስር አስፈላጊነት ጎልቶ ይወጣል። ስለዚህ በሀገሪቱ የሚፈጠረው ፌዴራላዊ ስርዓት የሕዝቡን ታሪካዊና ባህላዊ ትስስር መነሻ ያደረገ ይሁን ሲባል የተለያዩ ቋንቋዎችና ባህሎች እንደሌሉ ይቆጠሩ ወይንም ትኩረት ይነፈጋቸው ማለት ስላልሆነ ቋንቋ ከሀገሪቱ የፌዴራል አደረጃጀት መስፈርቶች ውስጥ አንዱ መመዘኛ ሆኖ እንደሚችል ኢዴፓ ያምናል።

አራተኛው መመዘኛ በኢትዮጵያ የሚመሰረተው ፌዴራሊዝም የሀገሪቱን መልክዓ ምድራዊ ገጽታ ከግምት ውስጥ የሚያስገባ መሆን አለበት የሚለው ነው። ሀገሪቱ የተለያየ ጆኦግራፊያዊ ገፅታ ያላት መሆኑ በሕዝቡ አሰፋፈርና አኗኗር ላይ የራሱ የሆነ ተፅዕኖ እንዳለው የታወቀ ነው። ብዙ ቁጥር ያለው ሕዝብ ለጤና ተስማሚ በሆነው ደጋና ወይናደጋ የሰፈረ ነው። አነሰተኛ ቁጥር ያለው ደግሞ ለጤንነት አደገኛ የሆነ የአየር ንብረት ባለው ቆላና በረሃ ውስጥ ሰፍሯል። ከሀገሪቱ ቆዳ ስፋት አነስተኛ ድርሻ ያለው ደጋው ሲሆን ቆላው ደግሞ ሰፊውን ድርሻ ይዟል። የጂኦግራፊ ገጽታው ከእርሻና ከኢንዱስትሪ፣ ከንግድና መሰረተ ልማት ግንባታ ጋር ብቻ ሳይሆን  እያንዳንዱ ክልል ራሱን እንዲችል የሚያበቃውን መነሻ መሰረት የሚያስገኝ ነው። የሀገሪቱ ክልል ከዚያ ተራራ ወዲህ ለእነዚህ፣ ከዚያ ወንዝ በመለስ ለእነዚያ ተብሎ በዘፈቀደ መሰራት የሚገባው አይደለም። ወይንም የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎችን በአንድ ክልል ውስጥ ለማጠቃለል በሚል ታሳቢ ብቻ ለግንኙነት በሚያስቸግር መንገድ መከለል የለበትም። ክልሎች ሲወሰኑ የሀገሪቱ ጂኦግራፊያዊ ገጽታም ከሚታዩት ታሳቢዎች አንዱ መሆን ይገባዋል ብሎ ኢዴፓ ያምናል።

አምስተኛው መመዘኛ በሀገሪቱ የሚመሰረተው ፌዴራሊዝም ቀልጣፋ ለሆነ አስተዳዳራዊ አገልግሎት አሰጣጥ የተመቸ መሆን አለበት የሚለው ነው። ሕዝቡ በቋንቋው የመጠቀም፣ ባህሉንና ታሪኩን የመጠበቅና በዚህም የመኩራት መብቱ ሊጠበቅለት እንደሚገባ ሁሉ የተቀላጠፈ አስተዳደራዊ አገልግሎት የማግኘት መብቱም ሊጠበቅለት ይገባል። ይህ እውን የሚሆነው ተስማሚ የክልል አደረጃጀት ሲኖር ነው። አሁን የሚሰራበት የቋንቋ ክልል ይህንን የሕዝብ መብት የሚረግጥ መሆኑ በተግባር እየታየ ነው። በአንድ ቋንቋ ስም ሰፊ ጂኦግራፊያዊ አካባቢ አንድ ክልል ሆኖ በመጠቃለሉ በሕዝቡ ላይ የደረሰው ችግር ከፍተኛ ነው። አንድ የሰሜን ሸዋ ነዋሪ፣ አንድ የኢሉባቡር ወይም የወለጋ ነዋሪ አዲስ አበባ ወይም ናዝሬት ከሚገኘው የኦሮሚያ ክልል ማዕከል አስተዳደራዊ አገልግሎት ለማግኘት ያለበትንም ችግር በተመሳሳይ ሁኔታ መገንዘብ ይቻላል። ቦረና አንድ ክልል ሆኖ ሕዝቡ የተቀላጠፈ አስተዳደራዊ አገልግሎት እያገኘ ቋንቋውንና ባህሉን የማይጠብቅበት መንገድ የለም። ወለጋም ይሁን ኢሉባቡር ወይንም ሰሜን ሸዋም ይሁን ሰሜን ጎንደር እንደዚሁ። ደቡብ ኦሞ

አንድ ክልል ቢሆን የሕዝቡን ባህልና ቋንቋ እየጠበቀ የተቀላጠፈ አስተዳደር አገልግሎት መስጠት የማይቻልበት መንገድ የለም። ምዕራብ ሀረርጌ ወይንም ጅማ ራሳቸውን የቻሉ ክልሎች ሆነው የተቀላጠፈ አስተዳደራዊ አገልግሎት እየሰጡ የሕዝቡ ቋንቋና ባህል ሊጠበቅ የማይችልበት ሁኔታ ይኖራል ተብሎ አይገመትም። ደቡብ ወሎም ይሁን ሰሜን አሞ፣ ምስራቅ ጎጃም ይሁን ከፍቾ ሸክቾ፣ ደቡብ ጎንደር ይሁን ቤንች ማጂ ወዘተ. እንደዚሁ። ስለዚህ የፌዴራል ክልሎች አወሳሰን የሕዝቡን ቀልጣፋ አስተዳደራዊ አገልግሎት የማግኘት መብት በሚያስጠብቅ መንገድ መሰራት ይገባዋል ብሎ ኢዴፓ ያምናል።

እዚህ ላይ ሊነሳ የሚችለው ክርክር ክልሎች ሲበዙ የመንግስት ወጪ ይጨምራል። ከአቅም ጋር የሚመጣጠን ቆጣቢ አደረጃጀትም አይሆንም የሚል ነው። በመሰረቱ ሕዝብ ግብር እየከፈለ የሚያደራጀው መንግስት ከሁሉም በፊት ቅድሚያ መስጠት የሚገባው ለሕዝቡ የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት በሚችልበት ሁኔታ ላይ ነው። ይሁን እንጂ በአሁኑ አደረጃጀት የሚታየው ከዚህ የተለየ ነው። ከዚህ በፊት ያልነበሩና ከሕዝቡ የራቁ አዳዲስ የክልል ማዕከሎችን ለመመስረት የወጣው ከፍተኛ ሀብት ወደሕዝቡ ቀረብ ብለው የሚገኙና ቀልጣፋ አስተዳደራዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ ነባር ማዕከላትን ወደክልል ደረጃ ከፍ እያደረጉ ለማደራጀት ሊውል ይችል ነበር። የሀብት አጠቃቀም ብክነትም ሆነ የተቀላጠፈ አስተዳደራዊ አገልግሎት ያለማሟላት ድክመትም ባልተከሰተ ነበር። የአሁኑ አደረጃጀት ግን ውጤቱ በሁለቱም መመዘኛ ቢታይ አክሳሪ እንጂ አትራፊ አይደለም። ቁጠባን አላስገኘም፣ አገልግሎትንም አላሳለጠም። በአሁኑ አደረጃጀት ወደ ሕዝቡ የቀረቡትን ማዕከላት ምንም አይነት የሕዝብ ውክልና የሌላቸው የስርዓቱ ካድሬዎች ለውለታ መክፈያ የሚሾሙበት የዞን ደረጃ በመስጠት ከሕዝቡ ጋር ጨርሶ ሊገናኙ የማይችሉ አዳዲስ ማዕከላትን ደግሞ የክልል ደረጃ እንዲኖራቸው በማድረግ የስርዓቱ ቁልፍ አገልጋዮች ሀገሪቱን በቀጠና ተከፋፍለው የመንግስታቸውን ሕልውና የሚጠብቁበት አሰራር ብቻ ነው የተፈጠረው።

በኢዴፓ እምነት ዞን የሚባለውን እርከን ጨርሶ በማስቀረትና አሁን ያሉትን ከሕዝቡ በጣም የራቁ ክልሎችን በማጠፍ ወደሕዝቡ የቀረቡ የአካባቢ አስተዳደሮች መመስረት ይገባል። ከአካባቢ አስተዳደሮች በታች ያሉ እርከኖች በሕዝቡና በክልል መንግስታት መካከል ያለውን ግንኙነት ስለሚያራዝሙት በዞን ፋንታ የወረዳ እርከን ብቻ ቢኖር ይመረጣል የሚል እምነት በኢዴፓ በኩል አለ። ከዚህ በተጨማሪ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ቢኖሩ የወረዳዎችንና የቀበሌዎችን ስፋት እየቀነሱ ተጨማሪ ወረዳዎችንና ቀበሌዎችን በማደራጀት በሕዝብ ቁጥርና በቆዳ ስፋት እንዲመጣጠኑ ማድረግና የመንግስትን አስተዳደራዊ አገልገሎት በማቀላጠፍ የሕዝቡን ድካም መቀነስ ይቻላል። ይህ ሁኔታ በቀበሌዎችና በወረዳዎች መካከል ጤናማ ውድድር እንዲኖር ስለሚያበረታታ ሕዝቡን የበለጠ ተጠቃሚ ለማድረግ ይረዳል።

አሁን ያለው አደረጃጀት ከሀገራችን መልክዓ ምድር ወጣገባነት፣ ካለብን የመሰረተ ልማት (መንገድ፣ ትራንስፖርት፣ ስልክ፣ ፖስታ፣ ወዘተ.) እጥረት፣ ከሕዝቡ ድህነትና ከተከሰተው የኑሮ ውድነት ጋር ጨርሶ የሚገናኝ አይደለም። ስለሆነም የሀገሪቱ ፌዴራላዊ አደረጃጀት የክልል አወሳሰን ሕዝቡ የተቀላጠፈ አስተዳደር ለማግኘት ያለውን መብት መሰረት ያደረገ መሆን አለበት።

ስድስተኛው መመዘኛ በኢትዮጵያ የሚመሰረተው ፌዴራሊዝም ለተፋጠነ ልማትና ተመጣጣኝ እድገት አመቺ በሆነ ሁኔታ መመስረት አለበት የሚለው ነው። የሀገሪቱ ፌዴራላዊ አደረጃጀት አንድ አካባቢ ለልማት የተመቹ ሁኔታዎች የተሟሉለት ሆኖ ሌላው ደግሞ ምንም አይነት ምቹ ሁኔታ ሳይኖረው እንደገባህ ውጣው በሚል ሂሳብ የሚሰራ መሆን የለበትም። አንድ የተከማቸ እውቀትና ጉልበት ይዞ ይህንን በጥቅም ላይ የሚያውልበት ምቹ ሁኔታ የማይኖረው ከሆነ ልማት ሊመጣ አይችልም። አንዱ ለልማት የሚመች የተፈጥሮ ሁኔታ እያለው ይህንን መጠቀም የሚያስችለው የካፒታልና የሰው ኃይል የሚያገኝበት ሁኔታ ከሌለ ልማት አይኖርም። አንዱ የሀገሪቱ አካባቢ የተለየ የልማት እድል እንዲኖረው እየተደረገ ሌላው የበይ ተመልካች ከሆነ ተመጣጠኝ እድገት አይኖርም። ገጠሩ የተሻለ እድገት እስኪያሳይ ከተማው ባለበት ሁኔታ እንዲቆይ ከተደረገ ወይም ከተማው ይበልጥ እየተመነደገ ገጠሩ ከተረሳ ልማትም፣ ተመጣጣኝ እድገትም አይመጣም። የመሃሉ አካባቢ በፍጥነት እያደገ የጠረፉ አካባቢ እንደተረሳ ከቆየም ልማትና ተመጣጣኝ እድገት አለ ሊባል አይችልም።

አሁን ያለው አደረጃጀት ይህንን ችግር የሚያባብስ እንጂ የሚያሻሽል አይደለም፡፡ ከሕዝብ በጣም የራቁ አዳዲስ ማዕከሎችን ለመገንባት ከፍተኛ ሀብት፣ ጉልበትና ጊዜ እየባከነ ከዚህ በፊት መልማት የጀመሩ አካባቢዎች እየወደቁና እየፈረሱ ነው፡፡ አዋሳ ስትመነደግ አርባ ምንጭ ለተረሳችበት ሁኔታ አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ አይቻልም፡፡ ናዝሬት በእድገት ጎዳና ስትጓዝ ነቀምት ለወደቀችበት ሁኔታ፣ ወይንም ባህር ዳር እድገት እያሳየች ጎንደር፣ ደብረማርቆስ፣ ደሴ፣ ወልዲያ፣ ሰቆጣ፣ ደብረብርሃን የተወረሩ ከተሞች እስኪመስሉ ድረስ ለተጎሳቆሉበት ሁኔታ በቂ ምክንያት የለም፡፡ መቀሌን ከፍተኛ የሕክምና ተቋሞች፣ በርካታ ዩኒቨርስቲዎች፣ ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች፣ ዘመናዊ የመገናኛ አውታሮች፣ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ፣ ትላልቅ ሆቴሎች ወዘተ.. አንፃራዊ በሆነ መጠን ስታገኝ አሳኢታ፣ ጋምቤላ፣ አሶሳ፣ ጅጅጋ፣ ሀረር፣ ወዘተ. ንፁህ የመጠጥ ውሃ እንኳ እንደልብ ለማያገኙበት፣ የረባ የሕክምና ተቋም ሳይገነቡ ለቀሩበት ሁኔታ ምንም ማስተባበያ መፈለግ አይቻልም፡፡ በሀገሪቱ ለሚታየው የልማት መጓተትና ያልተመጣጠነ እድገት አንዱ ምክንያት የአሁኑ ፌዴራላዊ አደረጃጀት ነው፡፡ ካፒታል ያለው ወደፈለገው ቦታ በነፃነት ተዘዋውሮ ኢንቨስት ለማድረግ ወይም እውቀትና ጉልበት ያለው በፈለገው ጊዜ ወደፈለገው ቦታ ሄዶ ሰርቶ ለመኖር እንዳይችል የቋንቋ ፌዴሬሽኑ የሚያበረታታ ስላልሆነ ሁሉም በተወሰኑ ከተሞች ተከማችቶ ይተራመሳል፡፡ በጥቂት ከተሞች ውስጥ ያለችውን እየተናጠቁ ከመኖር በስተቀር በሁሉም አካባቢዎች ተሰማርቶ ለማልማትና እድገት ለማምጣት እድል የሚሰጥ አደረጃጀት አይደለም፡፡ ስለዚህ የፌዴራል አደረጃጀቱ በከተማና በገጠር፣ በመሀልና በጠረፍ ወይም በደጋና በቆላ መካከል ያለውን ልዩነት ቀስ በቀስ ለመቀነስና ለተፋጠነ ልማትና ተመጣጣኝ እድገት በሚያመች መንገድ ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በተናጠልም ሆነ በጋራ ግምት ውስጥ በማስገባት መደራጀት አለበት ብሎ ኢዴፓ ያምናል፡፡

እነዚህ የተጠቀሱት መርሆዎች ዋና ዋናዎቹ ይሁኑ እንጂ ሌሎች ከግምት ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ የሕዝብ ብዛት፣ የተፈጥሮ ሀብት ክምችት፣ የመሰረተ ልማት ሥርጭት፣ የጠረፍ ፀጥታ አጠባበቅና ሌሎችም በርካታ ታሳቢዎች በፌዴራል አደረጃጀትና በአስተዳደር ክልሎች አወሳሰን ሊታዩ የሚችሉ ጠቃሚ ጉዳዮች ናቸው፡፡

## 3.1 በፌዴራል አደረጃጀት ስልጣንን ወደ ህዝብ የማውረድ ተግባር (decentralization of Power)

ፌዴራላዊ የሆነ ሥርዓት የመንግስት ሥልጣን በተለያዩ አካላት መካከል ሕገመንግስታዊ በሆነ አግባብ የሚከፋፈልበት መሆኑ ቀደም ሲል ተገልፆል፡፡ እንደ እኛ ሀገር ጉራማይሌ የሆነ የሕብረተሰብ ጥንቅርና አወቃቀር ባለበትና ከአንድ ማዕከል በሚመነጭ ፖለቲካዊ አመራር ብቻ ለማስተዳደር የማያስችል ሰፊ ጂኦግራፊያዊ ክልል በሚገኝበት ሀገር ውስጥ ፌዴራላዊ የሆነ አደረጃጀትና አሰራር የተሻለው አማራጭ መሆኑም በሚገባ ተብራርቷል፡፡ የመንግስት ስልጣን ክፍፍል ሲባል ደግሞ በሕግ አውጭው፣ በሕግ አስፈፃሚውና በሕግ ተርጓሚው መካከል ያለውንና ወይንም በተለያዩ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቶችና፣ ድርጅቶች መካከል የሚኖረውን የስልጣንና የስራ ክፍፍል ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡ በማዕከል፣ በክልሎችና በአካባቢ የመንግስት አካላት መካከል ያለውንም የስልጣን ክፍፍል የሚያጠቃልል ነው፡፡ የመንግስት ስልጣንን ወደ ክልሎችና የአካባቢ መንግስት አካሎች የማውረዱ ሂደት ያልተማከለ ፌዴራላዊ አደረጃጀት አካል ነው፡፡

ያልተማከለ ፌዴራላዊ አደረጃጀት የሚያመለክተው የመንግስት ሥልጣንና ኃላፊነት በአንድ ማዕከላዊ አካል የሚከማችበት ሁኔታ ቀርቶ ወደ አካባቢ የመንግስት አካላት የሚሸጋገርበትን ወይንም የሚወርድበትን ሂደትና አሰራር ነው፡፡ ፌዴራላዊ አደረጃጀት ባላቸው እንደ ጀርመን፣ አውስትራሊያ፣ አሜሪካና በመሳሰሉት ዴሞክራሲያዊ ሀገሮች ስልጣንን ወደታች የማውረድና ያልተማከለ እንዲሆን የማድረግ ተግባር በተሳካ ሁኔታ ተከናውኖ ውጤታማ መሆኑ በሚገባ ተፈትሿል፡፡ በዚህ ያልተማከለ ፌዴራላዊ አደረጃጀት ዋነኛው ጉዳይ በማዕከላዊ አካል የተከማቸ ስልጣን እንዳይኖር ማድረግና በዚህ ምትክ ስልጣን ወደ ክልሎች ወደታችኞቹ አካላት እንዲሸጋገር (Devolution of power) ማድረግ ነው፡፡ ምክንያቱም የዚህ አይነቱ የስልጣን ክፍፍል የመንግስት ብቃት እንዲጨምርና ሕዝቡ የራሱን ጉዳይ በራሱ ለመቆጣጠርም ሆነ ለመወሰን ያለውን ፍላጎት ለማሟላት እንዲችል ስለሚያደርግ ነው፡፡ ብዙዎቹ የዴሞክራሲ ስርዓቶች ወደዚህ አሰራር የገቡበት በርካታ

ምክንያቶች ቢኖሯቸውም እንደመሰረታዊ ነጥብ የሚታየው ግን በማዕከላዊ መንግስት አመራር ብቻ ሊሟሉ ያልቻሉትን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የሶሻል ፍላጎቶች ለማሳካት የሚያስችል የሲቪክ ሕብረተሰብ ተሳትፎ እንዲሰፋና ዴሞክራሲ ጥልቀት እንዲያገኝ ይረዳል የሚለው ነው፡፡ ኪራይ መሰብሰብን ጨምሮ በሁሉም የዜጎች ጉዳይ ላይ አድራጊና ፈጣሪ ከሆነ ብቸኛ ማዕከላዊ አካል ስልጣንን በማራቅ ወደሕዝቡ የቀረቡ በርካታ የስልጣን ማዕከላትን መፍጠርና የሕብረተሰቡን የተባበረ የልማት ጥረት ጥቅም ላይ ማዋል ድህነትን ለማስወገድም ሆነ ፈጣን እድገት ለማምጣት የተሻለው አማራጭ እንደሆነ ይታመናል፡፡

ያልተማከለ ፌዴራላዊ አደረጃጀት ለዴሞክራሲ ጥልቀት ለመስጠት ያስችላል ሲባል የተለያየ ፍላጎትና እምነት ያላቸው ኃይሎች እንደየፍላጎታቸውና እምነታቸው እንዲደራጁ፣ እንዲወዳደሩና የመራጩን ውክልና አግኝተው የመንግስት ስልጣንን እየተጋሩ ሕልውናቸውን እንዲጠብቁ የሚያደርግ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት እንዲኖር ይረዳል ማለት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አደረጃጀት ሕዝቡ የራሱን ጉዳይ በራሱ እንዲወስን፣ በመንግስት አስተዳደርና አመራር ስራ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርግና የማዕከላዊ መንግስት ጣልቃ ገብነት የተገደበ እንዲሆን የሚያስችል በመሆኑ እውነተኛ ዴሞክራሲ ስር የሚሰድበት መንገድ ነው፡፡

ያልተማከለ ስልጣን ሲባል አስተዳደራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን በራሱ በሕዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲንቀሳቀሱ ኃላፊነትና ስልጣን መስጠት ማለት ነው፡፡ አንዳንድ ሀገሮች የማዕከላዊ መንግስት ተወካዮችን በዝቅተኞቹ የስልጣን እርከኖች መድበው የሚሰሩበትን ሁኔታ ወይንም በተወሰኑ የፋይናንስ ውሳኔዎች የበጀት አስተዳደር ጉዳዮች የታችኞቹ የስልጣን አካላት ውክልና የሚያገኙበትን አሰራር ያልተማከለ ስልጣን ማረጋገጫ አድርገው ለማቅረብ ይሞከራሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሀቀኛ ያልተማከለ ስልጣን በዚህ መንገድ ብቻ ሊገለጽ አይችልም፡፡ የማዕከላዊ ስልጣን ተወካዮች በክልልና በአካባቢ አስተዳደርና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ስለተሳተፉ ሕዝቡ የራሱን ጉዳይ በራሱ ለመወሰን እድል አግኝቷል ሊባል አይችልም፡፡ እነዚህ በማዕከላዊ መንግስት የተወከሉ የአካባቢ መሪዎች ተጠሪነታቸውና ተጠያቂነታቸው ለሕዝቡ ሳይሆን ለመደባቸው ማዕከላዊ የስልጣን አካል እንደመሆኑ ሕዝቡ ሊቆጣጠራቸውና የሚፈልገውን እንዲፈፅሙለት ትርጉም ያለው ተፅዕኖ ሊያሳድርባቸው አይችልም፡፡ በመሆኑም ሀቀኛ ያልተማከለ ስልጣን ሊኖር የሚችለው ሀብትን፣ ሥልጣንና ኃላፊነትን ከማዕከል ወደ የአካባቢ አስተዳደር መንግስት እርከኖች ከማዕከላዊው ስልጣን አካል ቁጥጥርና ተፅዕኖ ነፃ ሆነው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ ሲቻል ነው፡፡

የፖለቲካ ስልጣን በክልሎችና በአካባቢ የመንግስት ስልጣን አካሎች መካከል በሚከፋፈልበት መንገድ የተደራጀ የፌዴራል ስርዓት ዜጎች በራሳቸው ሕልውናና የዕለት ከዕለት ጉዳይ ላይ በቀጥታ እንዲወስኑ በማስቻል ለዴሞክራሲ ጥልቀት የሚሰጥ ብቻ ሳይሆን ሌሎችም በርካታ ጥቅሞች አሉት፡፡ ልማትን በአካባቢ ፍላጎት፣ እውቀትና አቅም ላይ የተመሰረተ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በሀብት አስተዳደር፣ በአካባቢ ጥበቃና በግጭቶች አፈታት ረገድ የአካባቢ ጠቃሚ ልምዶችና ዘይቤዎች በመደበኛው የፖለቲካ ሂደት ውስጥ ተካትተው አገልገሎት እንዲሰጡ ያስችላል፡፡ በመንግስትና በሕዝብ መካከል፣ በማዕከልና በክልል ወይም በክልልና በአካባቢ አካላት መካከል ጠንካራ ዝምድናና አጋርነት እንዲኖር ያግዛል፡፡ በፕሮጀክቶች ቀረፃ ዝግጅት፣ ተግባራዊነትና ቁጥጥር የበታች አካላት የባለቤትነት ስሜት እንዲያድርባቸውና በዘላቂነት እንዲጠቀሙባቸው ያስችላል፡፡ በፖለቲካና በሌላም መስክ የመገለል ስሜት የሚያድርባቸው አናሳ ክፍሎች በመንግስት አሰራር ውስጥ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማስቻል ከዚህ አደገኛ ስጋት እንዲገላገሉና በአንድ ሀገር ስር አብረው ለመኖር የሚያስችል እምነት እንዲያዳብሩ ይረዳል፡፡ ለጠረፍ አካባቢዎች፣ ለተበደሉትና ቀደም ሲል ተገቢ ውክልና ሳያገኙ ለቆዩት ክልሎች አንድም በተሻለ ሁኔታ ላይ ከሚገኙት አጎራባች ክልሎች ጋር በማዋሃድ ወይንም የበለጠ ፍትሃዊ የሀብት ምደባና ክፍፍል በማድረግ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል ይረዳል፡፡

በማዕከላዊ መንግስት ስልጣን ለመጋራትም ሆነ ተፅዕኖ ለማሳደር እድል ያላገኙት ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ማህበራዊ ክፍሎች በዝቅተኛ የመንግስት እርከኖች ስልጣን እንዲጨብጡ በማድረግ ከመገለል አደጋ የሚድኑበትን እድል ይፈጥራል፡፡ በመንግስት ስራ ቁጥጥር፣ ግምገማና እቅድ አወጣጥ ላይ የበላይ አካላት ብቸኛ ሚና እንዲቀርና ከታችም የሕዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎ እንዲጨመርበት ይረዳል፡፡ ድህነትን ለመቀነስ፣ ለሴቶች እኩልነት ተገቢ ትኩረት ለመስጠት፣ በገጠርና በከተሞች

መካከል ያለውን የሀብት አመዳደብ፣ በስልጣን ውክልናና ወዘተ መካከል የሚኖረውን ልዩነት ለማጥበብ፣ የፖለቲካ ስርዓቱን ሕጋዊነት ለማጠናከርና በሰፊ መሰረት ላይ እንዲቆም የሚያስችል የሕዝብ ድጋፍ ለመፍጠር ያግዛል:: የአካባቢ አካላት የሰለጠኑ ሞያተኞችን ለመጠቀም እንዲችሉ፣ ድሆቹና ወደኋላ የቀሩት አካባቢዎች በሀገር ፖለቲካ ውስጥ ተገቢ ውክልናና ተሳትፎ እንዲኖራቸው፣ በማዕከልና በአካባቢ አካላት መካከል ጠንካራ የግንኙነት ድልድል እንዲዘረጋ፣ በአካባቢና በብሔራዊ አካላት መካከል በትብብርና በእኩልነት መርህ ላይ የቆመ ቅንጅታዊ አሰራር እንዲኖር ለከፍተኛ ኃላፊነትና ስልጣን የሚያስፈልጉ ሰዎች ሕዝብን የመምራትና የማስተባበር ልምድ እንዲያዳብሩ ለማድረግ ወዘተ. ያገለግላል::

ስለዚህ እነዚህንና የመሳሰሉትን ዓላማዎች ለማሳካት በሀገራችን ሀቀኛ ያልተማከለ ስልጣን እንዲኖር ያስፈልጋል:: አሁን አለ የሚባለው ያልተማከለ ስልጣን እውነተኛ የሆነ የሕዝብ ቀጥተኛ ተሳትፎና ውክልና ሳይኖር ማዕከላዊው መንግስት ለራሱ ተጠሪና ተጠያቂ የሆኑ ካድሬዎቹን በአካባቢ መንግስት ስልጣን ላይ እየሾመ ያስቀመጠበት አሰራር ነው:: እነዚህ በዝቅተኛዎቹ የስልጣን እርከኖች ላይ የተመደቡት የማዕከላዊው መንግስት ወኪሎች ተጠሪነታቸው ለመደባቸው የበላይ አካል እንጂ ለሚገዙት ሕዝብ አይደለም:: ስልጣን ላይ ባለው አገዛዝ አማካይነት የተወሰነ የፋይናንስና የበጀት አስተዳደር ስልጣን ለበታች አካለት በማስተላለፍ ያልተማከለ ስልጣን እንዳለ ለማስመሰል የሚደረግ ሙከራ ቢኖርም እውነቱ ግን እንደውም ከማዕከላዊ መንግስት የሚሰጠውን የበጀትና የፋይናንስ ድጋፍ በመጠቀም በበታች አካለት ላይ ከፍተኛ ቁጥጥርና ተፅዕኖ የሚደረግ መሆኑ ነው:: ወይንም ሀገሪቱ ያላት ውስን ሀብት ለአካባቢዎች ልማት ሳይሆን ለአንድ ፓርቲ ፕሮግራም ማስፈፀሚያ እየዋለ መሆኑ ነው::

ቀደም ሲል ለመግለጽ እንደተሞከረው ትክክለኛ ያልተማከለ ስልጣን አለ ለማለት የሚቻለው ሀብትን፣ ስልጣንና ኃላፊነትን ከማዕከላዊው መንግስት ተፅዕኖና ቁጥጥር ነፃ በሆነ መንገድ ወደታችኞቹ የስልጣን እርከኖች በተሟላ ሁኔታ ማዛወር ሲቻል ነው:: የታችኞቹ የስልጣን እርከኖች ተጠሪነትና ተጠያቂነት በውክልና ለሾማቸው የበላይ አካል መሆኑ ቀርቶ በሕዝብ የተመረጡና ለዚሁ ሕዝብ ተጠሪነትና ተጠያቂነት ያላቸው እንዲሆኑ ሲደረግ ነው:: አሁን በተግባር እንደሚታየው ማዕከላዊው መንግስት የሚፈልጋቸውና በስልጣን ላይ ያስቀመጣቸው ወኪሎች የፈለገውን ያክል በመራጩ ሕዝብ ቢጠሉና ተቃውሞ ቢቀርብባቸው ከሥልጣናቸው የሚነቀንቃቸው የለም:: በተቃራኒው የፈለገውን ያክል የሕዝብ ድጋፍ ያላቸው ቢሆኑም አገዛዙ እስካልፈለጋቸው ድረስ ለአንድ ቀን እንኳ ስልጣን ላይ ለመቆየት አይችሉም:: በክልልና በአካባቢ የሥልጣን እርከኖች የተመደቡ ሰዎች ሕዝቡ የሚፈልገውን ሳይሆን ከማዕከል ተቀርፆ የሚሰጣቸውን አጀንዳ ብቻ ለማስፈፀም የተሰለፉና በማዕከላዊው ስልጣን አባላት እጃቸውን እየተጠመዘዙ የሚሰሩ ናቸው:: እነዚህ የአካባቢውን ሕዝብ አፍንጫ እየሰነጉ ግብርና ታክስ በማስከፈል ለአካባቢ ልማት መዋል የሚገባውን ሪሶርስ ለወከላቸው ማዕከላዊ የሥልጣን አካል በማቀበል ለተላላኪነት ስራ የተሰለፉ ካድሬዎች ተወግደው ሕዝቡ ራሱ በመረጣቸው ወኪሎች የሚተኩበት ሁኔታ ሳይፈጠር ያልተማከለ ስልጣን አለ ለማለት አይቻልም:: ሕዝቡ በማዕከላዊው ስልጣን አካል በሚሾሙ የሞግዚት አስተዳዳሪዎች መገዛቱ ቀርቶ ራሱ በመረጣቸው ወኪሎቹ መተዳደር እስካልጀመረ ድረስ ያልተማከለ ስልጣን አለ ለማለት አይቻልም::

ሀቀኛ የሆነ ያልተማከለ ስልጣን መኖሩ የሚረጋገጠው ዜጎች በራሳቸው ተሳትፎ የሚያደርጉበት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ሲፈጠር፣ ከተስፋና ከመፈክር ባሻገር የሚጨበጥ መብትና ነፃነት ባለቤት መሆናቸው በተግባር ሲረጋገጥ፣ የአሰራር ግልጽነትና የሕዝብ ተጠያቂነት ያለው መልካም አስተዳደር ሲመሰረት፣ በማዕከልና በክልል ስልጣን አካሎች መካከል ስላለው የስልጣን ክፍፍልና ግንኙነት ግልጽና የማያሻሙ ሕጋዊ ስርዓቶች ሲፈጠሩ፣ የመንግስት አደረጃጀትና አሰራር ያልተንዛዛ፣ ቀላልና ወጪ ቆጣቢ ሆኖ ሲገኝ፣ የአካባቢ ልማትና ገቢ እንዲጠናከር የሚያግዝ የኢንቨስትሜንት ስርጭትና እንቅስቃሴ ሲጀመር፣ ፍትሃዊ የሀብት አመዳደብና ስርጭት ሲኖር፣ በማዕከላዊው መንግስትና በክልል ስልጣን አካላት መካከል ያለው ግንኙነት የጌታና የሎሌ መሆኑ ቀርቶ በእኩልነትና በአጋርነት መርህ ላይ ሲመሰረት፣ የፋይናንስና የሰለጠነ የሰው ሀይል ድጋፍና ድጎማ የፖለቲካዊ ቁጥጥርና ተፅዕኖ ማድረጊያ ዘዴ መሆኑ ሲቀር፣ ሪሶርስን ለመቆጣጠር፣ የአካባቢ ጥበቃን ለማጠናከር፣ ግጭቶችን ለማስወገድና ለመሳሰሉት ጉዳዮች አካባቢያዊ ዘይቤዎችና አሰራሮች ጥቅም ላይ

እንዲውሉ ሲደረግ ወዘተ. ብቻ ነው:: ከዚህ ውጭ የሚደረገው ማስመሰልና ማደናገር እውነቱን ለመደበቅ የሚደረግ ሙከራ ነው::

ኢዴፓ የፌዴራል ስርዓት ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል የሚል አቋም የያዘው ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ አይደለም:: ወይንም ፌዴራሊዝም የብዙዎቹ ፖለቲከኞች አፍ መፍቻ ሊሆን በመቻሉ የዚህ ፋሽን ተከታይ ሆኖ ለመታየት አይደለም:: ወይንም ደግሞ የሰዎችን ቀልብ የሚገዛ መፈክር አንጠልጥሎ ጊዜያዊ የፖለቲካ ትርፍ ለማግኘት አይደለም:: ኢዴፓ የፌዴራል ስርዓት ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል የሚል አቋም የያዘው የሀገሪቱን ያለፈ ታሪክ፣ የአሁኑን ተጨባጭ እውነታና መጪውን ሁኔታ በሚገባ ገምግሞና የተሻለው አማራጭ ይኸው መሆኑን በማመን ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በራሱ ጉዳይ ራሱ እንዲወስንና ከአገዛዝ ቀንበር ተላቆ በመንግስት አሰራር የተሟላ ተሳትፎ እንዲኖረው የሚያስችለው የተሻለ አማራጭ የፌዴራል ስርዓት መሆኑን በማመን ነው:: ሕዝቡ በከፍተኛ የውስጥ ክፍፍል እንዲጠመድና ሀገሪቱም ለከባድ የመበታተን አደጋ እንድትጋለጥ ከውስጥና ከውጭ የሚደረገውን ግፊት በማስቆም በእኩልነት ላይ የተመሰረተ አንድነት ለመፍጠር የሚያስችለው ትክክለኛ አቅጣጫ መሆኑን በመረዳት ነው:: እንዲህ ዓይነቱ የሥልጣን ክፍፍልና የእርስ በርስ ቁጥጥር ሲኖር የተለያየ አመለካከት፣ ፍላጎትና ጥቅም ያላቸው ሁሉም ዜጎች ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ጥቅሞቻቸውን ለማረጋገጥ የሚችሉበት ዴሞክራሲያዊ ማዕቀፍ እንዳለ ስለሚተማመኑ በአንድ ሀገር ጥላ ስር ተሳስረው ለመኖር የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል ከሚል ጠንካራ እምነት በመነሳት ነው::

ያልተማከለ ፌዴራላዊ የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖር ሲፈለግ ሁለት መሰረታዊ ችግሮች ሊያጋጥሙ ይችላሉ:: ይኸውም አንደኛው የአስተዳደር ክልሎች ከሕዝቡ ፈቃድና ፍላጎት ውጭ በዘፈቀደ የሚወሰኑበት ሁኔታ ከተፈጠረ በሕዝብና በመንግስት መካከል አለመታማመን ይነግሳል:: እንደውም የእርስ በርስ ብጥብጥና አለመረጋጋት ይስፋፋል:: ሕዝቡ መብቱን፣ ነፃነቱንና ክብሩን ካለፍላጎቱ እንደተቀማ ስለሚቆጥረው መንግስትን እንደራሱ ወኪል ሳይሆን እንደወራሪ ጠላት አድርጎ የሚመለከትበት ሁኔታ ይፈጠራል:: ሁለተኛው ችግር ደግሞ በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ራሳቸውን እንደብቸኛ ሹም አድርገው ስለሚመለከቱ የአስተዳደር ክልሎች በሕዝቡ ፍላጎትና ፈቃድ በመመስረት እንዲቋቋሙና አንዱ ከሌላው እንዲቀላቀል ወይም እንዲለይ በሚደረግበት ጊዜ ክብራቸው የሚጎደል፣ ስልጣናቸው የሚቀነስና ጥቅማቸው የሚቋረጥ መስሎ ስለሚሰማቸው እንቅፋት ከመፍጠር የማይመለሱ መሆኑ ነው::

በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ ዋነኛው የሥልጣን ባለቤትና ምንጭ ሕዝቡ ራሱ እንደመሆኑ የአስተዳደር ክልሎችንም ሆነ የመንግስት ስልጣን ክፍፍሎችና ግንኙነቶችን በሚፈልገው መንገድ የመወሰን መብት ለሕዝቡ መስጠት ይኖርበታል:: ከመንግስትና ከሌላ ማንኛውም ቡድን በኩል የሚጠበቅ ነገር ቢኖር ለሕዝቡ ውሳኔ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችንና ልዩ ልዩ ድጋፎችን በሚፈለገው ፍጥነትና ጥራት አሟልቶ ማቅረብ ስለእያንዳንዱ አካባቢ ሕዝብ ብዛት፣ አሰፋፈርና ስርጭት፣ እንዲሁም ስለእያንዳንዱ አካባቢ ክልል ስፋትና ጥበት፣ የኢኮኖሚ መሰረት፣ የመሰረተ ልማት አገልግሎት፣ ስለሕዝቡ ባህልና የአኗኗር ስርዓት፣ በሕዝቡ መካከል ስላለው የተለያየ አይነት ግንኙነት ወዘተ. እውነተኛ መረጃዎች በወቅቱና በአግባቡ እስከቀረቡለት ድረስ ሕዝቡ ስለራሱ አስተዳደራዊ ክልሎች ቅርጽና ይዘት በሚገባ እንደሚወስን ይታመናል:: ስለዚህ በሀገሪቱ ውስጥ ሀቀኛ በሆነ መንገድ የተደራጀና ያልተማከለ የስልጣን ክፍፍል እንዲኖር ከተፈለገ ሕዝቡ የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን ለይቶ እንደሚያውቅ በማመን የፖለቲካ ስልጣን በራሱ በሕዝቡ ፍላጎትና ፈቃድ ላይ ብቻ ተመስርቶ የሚገኝ እንዲሆን ማድረግ ይገባል:: የመንግስት ስልጣን በእጁ ያስገባ ሁሉ እንደፈለገው የአስተዳደር ክልልን የሚያሰፋበትና የሚያጠብበት አሰራርና የእናውቅልሃለን አካሄድ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መቋረጥ አለበት:: በሀገሪቱ አስተዳደራዊ ክልሎች አመሰራረትና ያልተማከለ ስልጣን አደረጃጀት አማራጭ አለን የሚሉ ወገኖች ሁሉ አማራጮቻቸውን በነፃ መድረክ ለውይይት እያቀረቡ ሕዝቡ የፈለገውን መርጦ የሚወስንበት ዴሞክራሲያዊ አሰራር መኖር እንዳለበት ኢዴፓ በፅኑ ያምናል::

## 3.2 ተመጣጣኝ የሥልጣን ክፍፍልና የርስ በርስ ቁጥጥር በፌዴራላዊ አደረጃጀት

*ፌዴራላዊ የመንግስት አደረጃጀት ማለት ሕገመንግስታዊ በሆነ ሥርዓት ውስጥ በሚገኙ የተለያዩ የመንግስት አካላት ማለትም በማዕከልና በክልል፣ እንዲሁም በየደረጃው ባሉት ሕግ አውጭዎች፣ ሕግ አስፈጻሚዎችና ሕግ ተርጓሚዎች መካከል ሥልጣን ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ የሚከፋፈልበት*

ስርዓት መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል፡፡ የሥልጣን ክፍፍል ሲባል በፌዴራል ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከዚያም በታች ባሉት የክልል መንግስታት ጭምር በሶስቱ የመንግስት ስልጣን አካላት ማለትም በሕግ አውጭው፣ በሕግ አስፈፃሚውና በሕግ ተርጓሚው መካከል ያለውን የሚያጠቃልል ነው፡፡

የዴሞክራሲ ስርዓት ባላቸው ሀገሮች በመንግስት አካላት መካከል የሥልጣን ክፍፍልና የርስ በርስ ቁጥጥር መኖር እንደዋነኛ ጉዳይ የሚታይ ነው፡፡ ምክንያቱም የተከማቸ ስልጣን በአንደኛው አካል እጅ ብቻ እንዳይገባና በስልጣን ያለአግባብ መጠቀም እንዳይኖር ነው፡፡ የዚህ ዓይነቱ አሰራር የስልጣን ብልግና አደጋን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን የመንግስትንም የስራ ብቃት ያሳድጋል ተብሎ ይታመንበታል፡፡ በተለያዩ የስልጣን አካላት መካከል የስልጣን ክፍፍል ሲኖር የርስ በርስ ቁጥጥር ለማድረግና የተመጣጠነ የሥልጣን ሚዛን እንዲኖር ያስችላል የሚል እምነት አለ፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ ሕገመንግስታዊ ስርዓት ውስጥ ኮንግረሱ ፕሬዚዳንቱን ለመክሰስ ስልጣን ያለው ሲሆን ፕሬዚዳንቱ ደግሞ በኮንግረሱ ውሳኔ ላይ ድምፅን በድምጽ የመሻር ስልጣን (Veto power) አለው፡፡ ኮንግረሱ በተራው የፕሬዚዳንቱን ድምጽን በድምጽ የመሻር ውሳኔ ውድቅ (Over-ride) የማድረግ ስልጣን አለው፡፡ እንዲሁም ሕግ ተርጓሚው በሕግ አውጭውና በሕግ አስፈፃሚው ውሳኔዎች ላይ ሕጋዊ ቁጥጥር የሚያደርግበት ስልጣን ሲኖረው ሴኔቱ (ሕግ መወሰኛው ምክር ቤት) ደግሞ ፕሬዚዳንቱ ለዳኝነት የሚያቀርባቸውን እጩ ዳኞች የመደገፍና ያለመደገፍ ስልጣን አለው፡፡ ሴኔቱና ዴፓርትሜንቶች ሳይቀሩ እርስ በርሳቸው አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠሩበት አሰራር አለ፡፡ በሌሎችም ዴሞክራሲያዊ ሀገሮች ውስጥ በመንግስት ስልጣን አካላት መካከል የስልጣን ክፍፍልና የርስ በርስ ቁጥጥር መኖር የተለመደ ነው፡፡

በኢትዮጵያ ወስጥ ያለው አሰራር ግን ውስብስብና ግልጽነት የሌለው በመሆኑ ለመረዳትም አስቸጋሪ ነው፡፡ አሁን በሥራ ላይ ባለው ሕገመንግስት ክፍል አምስት ስር የስልጣን አወቃቀርና ክፍፍልን በሚመለከት በተለይም በአንቀፅ 50 ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 9 የተዘረዘሩ ድንጋጌዎች አሉ፡፡ ይሁን እንጂ በዚህ አንቀጽ ከተደነገጉት የስልጣን አወቃቀርና ክፍፍል ድንጋጌዎች መንፈስ በማይጣጣም ሁኔታ በዚሁ ሕገመንግስት በሌሎች አንቀጾች ስልጣኑን ሁሉ ለአስፈፃሚው አካል በተለይም ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ጠቅልሎ በማስረከብ የስልጣን ክፍፍሉን ትርጉም የሌለው ያደርገዋል፡፡ በሌላ አገላለጽ በሕገመንግስት ተወሰነ የተባለውን የሥልጣን ክፍፍል መልሶ ዋጋ ያሳጣዋል፡፡

ይህንን በግልጽ ለመረዳት በሕገመንግስቱ ውስጥ ስለሕግ አስፈጻሚው አካል ማለትም ስለጠቅላይ ሚኒስትሩና ስለሚኒስትሮች ምክር ቤት አሰያየም፣ ሥልጣንና ተግባራት ከአንቀጽ 72 እስከ 77 የተደነገጉትን ማየት ይበቃል፡፡ ሕግ አስፈፃሚው በተለይም ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሕግ አውጭውንና የዳኝነት አካሉን እንዲሁም በዚሁ ሕገመንግስት አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሕግ የመተርጎም ስልጣን የተሰጠውን የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ስልጣን ጭምር በቀጥታና በተዘዋዋሪ አጠቃሎ እንዲይዘው በመደረጉ የሥልጣን ክፍፍል አለ ለማለት አይቻልም፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ ለፍትህ አካል መሰጠት የነበረበት ሕግን የመተርጎም ስልጣን በሕገ መንግስቱ ለሌላ አካል በመስጠቱ ሕገመንግስትን የመተርጎም ስራ ከባድና የተወሳሰበ ሆኗል፡፡ ሕግ የመተርጎም ስልጣን የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሆኖ የተደነገገ ሲሆን ሕገመንግስታዊ ጉዳዮችን መርምሮ ውሳኔ የሚሰጠው በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 84 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ስልጣን የተሰጠው የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ አጣርቶ በሚቀርብለት መሰረት ነው፡፡ ይኸንን አጣሪ ጉባኤ በሰብሳቢነትና በምክትል ሰብሳቢነት እንዲመሩት በሕገመንግስቱ አንቀፅ 82 ንዑስ አንቀጽ 2 በፊደል «ሀ» እና «ለ» ስልጣን የተሰጣቸው በሕገመንግስቱ አንቀጽ 74 ንዑስ አንቀጽ 7 መሰረት በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተመርጠው ሹመታቸው በተወካዮች ምክር ቤት የሚጸድቅላቸው የማዕከላዊ (የፌዴራሉ) ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ ናቸው፡፡

ከዚህ መረዳት የሚቻለው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ተሰጠ የሚባለው ሕግ የመተርጎም ስልጣን ለስሙ ያህል የተሰጠ መሆኑንና ዋናውን የሕገመንግስታዊ ጉዳይ የማጣራት ስልጣን በተዘዋዋሪ መንገድ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የተሰጠ መሆኑን ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ ሕግ የተመርጎም ስልጣን በተዘዋዋሪ መንገድ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁጥጥር ስር የወደቀ መሆኑን እንረዳለን፡፡

የተወካዮች ምክር ቤት ደግሞ በሕገመንግስቱ አንቀፅ 54 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው የአብላጫ ድምፅ ስርዓት መሰረት የአንድ ፓርቲ ተወካዮች አብዛኛውን የፓርላማ መቀመጫ ጠቅልለው በሚይዙበት አመራረጥ ዘይቤ የሚመሰረት ነው፡፡ በመሆኑም በሕገመንግስቱ አንቀጽ 56 መሠረት አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት የሚመራው ሕግ አስፈፃሚና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 73 ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚመረጠው ጠቅላይ ሚኒስትር የሚያቀርቡለትን የውሳኔ ሀሳብ ተቀብሎ ከማፅደቅ ያለፈ ስልጣን ፓርላመው የለውም፡፡ ስለዚህ ሕግ አውጭውም በተዘዋዋሪ መንገድ በሕግ አስፈፃሚው በተለይም በሕገመንግስቱ አንቀፅ 76 ንዑስ አንቀፅ 2 በተደነገገው መሰረት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪ በሆኑት ጠቅላይ ሚኒስትር ቁጥጥር ስር የወደቀ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በፌዴራሉ መንግስትና በክልል መንግስታት መካከል ያለውን የሥልጣን ክፍፍል በሚመለከት በሕገመንግስቱ አንቀፅ 50 ንዑስ አንቀጽ 8 የሰፈረ ድንጋጌ ቢኖርም አንድ ጊዜም ተከብሮ አያውቅም፡፡ በአንዳንዶቹ ክልሎች የተመደቡ የክልል ሹሞች በተለይ ታዳጊ በሚባሉት ክልሎች የሚገኙት ከማዕከል ተመርጠው በሚላኩላቸው ሞግዚቶች እጃቸውን እየተጠመዘዙ የሚሰሩ ናቸው፡፡ የክልል ምክር ቤቶች በክልላቸው ሥልጣን ስር በሆኑ ጉዳዮች የክልሉ ሕግ አውጭ አካል ናቸው የሚል በሕገመንግስቱ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 5 የተደነገገ ቢሆንም ሕግ እየተፃፈ የሚታደላቸው ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽህፈት ቤት ነው፡፡ በተለይ ታዳጊ ክልሎች ለሚባሉት ተፅፎ የሚሰጣቸው ሕገ መንግስት ከክልሎቹ ስም መለያየት በስተቀር አንድ አይነት ሆኖ የተዘጋጀና የየክልሎቹን ልዩ ሁኔታ እንኳ ከግምት ውስጥ የማያስገባ ነው፡፡

በክልል የመንግስት ሥልጣን በሕግ አውጭነት፣ ሕግ አስፈፃሚነትና በዳኝነት የተከፋፈለ ሳይሆን ሁሉም ስልጣን የሕግ አስፈፃሚ በሆነው የክልል መስተዳድር ተጠቃሎ የተያዘ ነው፡፡ በተለይም የክልል ፕሬዚዳንቶች የሕግ አውጭውን ምክር ቤትና የዳኝነቱን ስልጣን ሙሉ በሙሉ ተክተው ይሰራሉ፡፡

የክልል ዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤት ብቻ ነው በሚል በሕገመንግስቱ አንቀጽ 50 ንዑስ አንቀጽ 7 የተደነገገ ቢሆንም ዳኞች ስራቸውን በሕጉ ተመስርተው የሚያካሂዱበት ነጻነት የላቸውም፡፡ የክልል ፕሬዚዳንቶች በዳኝነት ስራ ውስጥ ጣልቃ መግባት ብቻ ሳይሆን ምን ዐይነት ፍርድ መሰጠት እንደሚገባው ትዕዛዝ እስከመስጠት የሚደርስ ተጽዕኖ ያደርጋሉ፡፡

የክልሉን ጉዳዮች የሚመለከት አጀንዳ በራሱ አውጥቶ በነፃነት ለመወያየት የሚያስችል መብት የሌለው የክልል ምክር ቤት በነጻነት የሚሰራ የክልል መንግስት ተደርጎ ሊወሰድ አይችልም፡፡ በማንኛውም ጉዳይ ላይ ተወያይቶ ለመወሰን የገዥውን ፓርቲ መሪዎች ፈቃድ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ በዚህ መንገድ መፈፀሙን ገዥው ፓርቲ የሚያረጋግጥበት ሁለት መንገዶች አሉት፡፡ አንደኛው የክልል ፕሬዚዳንቶች የገዥው ፓርቲ የፓሊት ቢሮ አባላት በሚሆኑበት ጊዜ ዴሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በሚባለው የፓርቲው የውስጥ አሰራር መርህ መሰረት የፓርቲውን የግንኙነት መስመር እየተከተሉ መመሪያ እንዲቀበሉና ሪፖርትም እንዲያቀርቡ በማድረግ ነው፡፡ ሁለተኛው የፓርቲው የፖሊት ቢሮ አባል ያልሆኑ ፕሬዚደንቶች ከተሾሙ ፓርቲው መርጦ በአማካሪነት ስም በሚመድባቸው ካድሬዎች አማካይነት ይቆጣጠራቸዋል፡፡ አሁን በየክልሉ ስልጣን ይዘው የተቀመጡ ሰዎች በገዥው ፓርቲ ማዕከላዊ አመራር ሙሉ ቁጥጥር ሥር የወደቁ በመሆናቸው ነፃ የፌዴራል ክልል እንደሚመሩ የሕዝብ ተወካዮች የሚቆጠሩበት አንዳችም ምክንያት የለም፡፡ ሀገሪቱ አሃዳዊ የመንግስት አደረጃጀት በነበራት ጊዜ በየክፍለ ሀገሩ ተመድበው ይሰሩ ከነበሩት ሹሞች በባሰ መንገድ ሙሉ በሙሉ በማዕከላዊ አመራር ቁጥጥር ስር ነው የአሁኖቹ ክልሎች የሚገዙት፡፡

በክልሎችና በፌዴራል መንግስት መካከል ያለው የሥልጣን ክፍፍል ትርጉም ያለው ሊሆን የሚችለው በቅድሚያ ክልሎቹ በአንድ ገዥ ፓርቲ መልካም ፈቃድ የተመሰረቱና ሕልውናቸውም በዚሁ ፓርቲ ሙሉ ቁጥጥር ስር የወደቀበት ሁኔታ መለወጥ ሲችል ነው፡፡ የሕዝቡን የተለያዩ አመለካከቶች የሚወክሉ ፓርቲዎች በሕዝቡ መካከል በነጻነት የሚንቀሳቀሱበትና ትክክለኛ በሆነ ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ስርዓት ተወዳድረው የሕዝብ ድጋፍ ያገኙት ብቻ የመንግስት ስልጣን የሚረከቡበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ በሕዝብ ነጻ ምርጫና ውሳኔ የተመሰረቱ ክልሎችና ፌዴራላዊ መንግስት ሲኖሩ የሚያቋቁሙት የሕብረት መንግስት በእኩልነትና በትብብር መርህ መመራቱ የማይቀር ነው፡፡ ለመረጣቸው ሕዝብ ተጠሪነትና ተጠያቂነት ያላቸው ክልሎች ሲኖሩ በክልሎችና በማዕከላዊ

መንግስት መካከል ያለው ግንኙነት የጌታና የሎሌ መሆኑ ይቀርና በእኩልነትና በትብብር መንፈስ ላይ የተመሰረተ ሕጋዊ ግንኙነት ይሆናል። ክልሎች የአንድ ፖለቲካ ቡድን አጀንዳ አስፈጻሚ መሆናቸው ይቀርና እውነተኛዎቹ የሕዝብ ስልጣን ባለቤትነት መገለጫና የራስ በራስ አስተዳደር መብት ማረጋገጫ ይሆናሉ። ስለዚህ አሁን ያለው የአንድ ወጥ ፓርቲ የሥልጣን ክፍፍልና ግንኙነት በሕዝብ ነጻ ምርጫ በተቋቋሙና በእኩልነትና በትብብር መርህ በሚመሩ የክልልና የፌዴራል መንግስታት ግንኙነት መተካት ይኖርበታል። እንዲህ ዓይነት መሰረታዊ የሆነ የአደረጃጀትና የግንኙነት ለውጥ ካልተደረገ በስተቀር በሀገሪቱ ውስጥ ከሰፈነው የአንድ ቡድን አገዛዝ ወጥቶ በዴሞክራሲ መርህ ላይ የቆመ ሕጋዊ ስርዓት ለማግኘት አይቻልም።

በክልልና በፌዴራል መንግስታት መካከል ያለውን የሥልጣን ክፍፍል የዴሞክራሲ ስርዓት በሚፈቅደው መንገድ ማደራጀት አንድ ነገር ሆኖ፣ በየደረጃው የሚመሰረቱ መንግስታዊት አካላትም ተመጣጣኝ የሥልጣን ክፍፍል እንዲኖራቸው ማድረግ ሌላው ቁልፍ ጉዳይ ነው። በፌዴራሉም ይሁን በክልል መንግስታት ውስጥ ስልጣን በሕግ አውጭ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ መካከል ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ ካልተከፋፈለ አሁንም የመንግስት ስልጣን በአንድ የፖለቲካ ቡድን ወይንም ግለሰብ እጅ የሚከማችበት አደጋ ይፈጠራል። የዚህ ዓይነቱ ችግር የሚወገድበትና የተለያዩ የስልጣን አካላት የርስ በርስ ቁጥጥር ተግባራዊ የሚሆንበት ዋነኛው መንገድ በመካከላቸው ያለውን የሥልጣን ክፍፍል በግልጽ የሚወስን ሕገመንግስታዊ ስርዓት መፍጠር ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ሥልጣን የያዘው አገዛዝ በየደረጃው የመሰረታቸው አካላት ተገቢ የሥልጣን ክፍፍል ያላቸውና የርስ በርስ ቁጥጥር ተግባራዊ የሚደረግባቸው አይደሉም። የመንግስት ስልጣን በአስፈጻሚ አካላት በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትሩና በክልል ፕሬዚደንቶች እጅ ተጠቃሎ እንዲያዝ የሚያደርግ ስርዓት በመዘርጋቱ ሕግ አውጭውና ሕግ ተርጓሚው ጠቃሚ ሚና አይጫወቱም። ስለዚህ እነዚህ የሥልጣን አካላት የሕዝቡ ሥልጣን ባለቤትነት የሚገለጽባቸውና ጥቅሙም የሚከበርባቸው እውነተኛ የዴሞክራሲ ተቋሞች እንዲሆኑ ተመጣጣኝ የሥልጣን ክፍፍል ሊኖራቸው ይገባል ብሎ ኢዴአፓ ያምናል። በሕግ አውጭው፣ ሕግ አስፈፃሚውና ሕግ ተርጓሚው መካከል መኖር ያለበትን የስልጣን ክፍፍልና የእርስ በርስ ቁጥጥር ባህርይ በሚገባ ለመገንዘብ በእያንዳንዱ የሥልጣን አካል ውስጥ ሊዘለሉ የማይገባቸውን ኃላፊነቶች እንደሚከተለው በዝርዝር ማየት ይጠቅማል።

## 3.2.1 ሕግ አውጭ አካል (ፓርላማ)

በየትኛውም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በሚከተል ሀገር ውስጥ የሕግ አውጭው አካል ኃላፊነት ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ቢሆንም እንደየሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ መጠነኛ የአደረጃጀትና አሰራር ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ። ፕሬዚዳንታዊ ሕገ መንግስት ባለባቸው ሀገሮች ሕግ የማውጣቱ ስራ በከፊል ለፕሬዚዳንቱ (ሕግ አስፈጻሚው) የሚሰጥበት አሰራር አለ። በአንዳንድ ሀገሮች ደግሞ ለምሳሌ በዴንማርክ፣ እስራኤል፣ ኒዊዘርላንድ፣ ጋናና በመሳሰሉት ሕግ የማውጣት ተግባት በአንድ ሕግ አውጭ ፓርላማ (Uni-cameral legislature) ይከናወናል። አብዛኛዎቹ ሀገሮች ግን ሁለት ሕግ አውጭ ምክር ቤቶችን (Bi-cameral legislature chambers) ያቋቁማሉ።

የፌዴራል ሥርዓት በመሰረቱ ዴሞክራሲያዊ ሀገሮች ባለሁለት ምክር ቤት ሕግ አውጭ አካላት መኖራቸው እጅግ አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም በተለምዶ የታችኛው ምክር ቤት እየተባለ የሚጠራው የተወካዮች ምክር ቤት የሚቋቋመው የመራጩን ህዝብ ቁጥር መሠረት በማድረግ ስለሚሆን አነስተኛ ቁጥር ያላቸውን ክልሎች ውክልና ተመጣጣኝነት ሙሉ በሙሉ ለማረጋገጥ አያመችም። በተለያዩ ምክንያቶች በእኩል የጥንካሬ ደረጃ ላይ የማይገኙትንና መሰረታዊ የሆኑ ልዩነቶች የሚታዩባቸውን ክልሎች ሕግ በማውጣት ተግባር ተመጣጣኝ ውክልናና እኩል ተሳትፎ እንዲኖራቸው በሚያስችል ፌዴራላዊ ስርዓት ለማስተሳሰር ከተወካዮች ምክር ቤት በተጨማሪ በተለምዶ አጠራር የላይኛው ምክር ቤት የሚባለውን ሕግ አውጭ አካል ማቋቋም ያስፈልጋል። ለምሳሌ በአውስትራሊያ በሕዝብ ቁጥር ላይ ተመስርቶ በምርጫ የሚቋቋም የተወካዮች ምክር ቤት ያለ ሲሆን ሴኔቱ (የላይኛው ምክር ቤት) ደግሞ ስድስቱ ግዛቶች እያንዳንዳቸው በሚወክሏቸው 10 (አስር) ተወካዮች የሚመሰረት 60 አባላት ያሉት አካል ነው። በሌሎችም የፌዴራል ስርዓት በመሰረቱ ሀገሮች ለተመሳሳይ ዓላማ የሚቋቋሙ ባለ ሁለት ምክር ቤት ሕግ አውጭ አካላት አሉ። የተወካዮች ምክር ቤት ዋነኛ ተግባር ሕግ ማውጣት፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩን መምረጥና በመንግስት አሰራር ላይ ክትትል

ማድረግ ሲሆን የሴኔቱ ተግባር ደግሞ ሕግ ማውጣት፣ የክልል መንግስታት ጥቅም ፍትሐዊ በሆነ መንገድ መጠበቁን ማረጋገጥና የመንግስትን አሰራር መከታተል ነው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚቋቋመው የፌዴራል ስርዓትም ባለሁለት ምክር ቤት ሕግ አውጭ አካላት ሊኖሩት ይገባል ብሎ ኢዴፓ ያምናል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ አካላት የሚቋቋሙት ሌሎች ሀገሮች ስላደረጉት ኢትዮጵያም ማድረግ አለባት ከሚል አስተሳሰብ በመነሳት አይደለም፡፡ እነዚህ ሕግ አውጭ አካላት መቋቋም ያለባቸው ዜጎች በተወካዮቻቸው አማካይነት ሕግ በማውጣትና የመንግስትን ስልጣን በመያዝ እኩልና ተመጣጣኝ ተሳትፎ የሚያደርጉባቸው እውነተኛ የዴሞክራሲ ተቋሞች እንዲኖሩ ያስፈልጋል ከሚል ጠንካራ እምነት ነው፡፡ አሁን በስራ ላይ ያለው ሕገመንግስት ባለሁለት ምክር ቤት ሕግ አውጭ አካላት እንዲኖሩ ፈቅዷል ቢባልም ሁለቱም ምክር ቤቶች ትርጉም ባለው ደረጃ ሕግ ለማውጣት የሚችሉበት እድል በራሱ በሕገመንግስቱ የጠበበ እንዲሆን በመደረጉ የዴሞክራሲ መርህ በሚፈቅደውና የፌዴራል ስርዓት አደረጃጀት በሚጠይቀው መንገድ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ የሚችሉ አይደሉም፡፡ የሁለቱም ምክር ቤቶች ስልጣን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሕግ አስፈጻሚው አካል በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁጥጥር ስር የወደቀ ነው፡፡ ሕግ አስፈጻሚውን ለመቆጣጠር የሚያስችል ምንም አይነት ስልጣን ያልተሰጣቸው መሆኑ ብቻ ሳይሆን እንደውም የሕግ አስፈጻሚውን አመራር ካልተቀበሉ ሕልውናቸውም አጠራጣሪ የሚሆንበት እድል ሰፊ ነው፡፡ ይኸንን ሀቅ ለመረዳት በአሁኑ አገዛዝ ሕገመንግስት የተደነገገውን የምርጫ ስርዓትና የሥልጣን ክፍፍል ማየት ይበቃል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ የምርጫ ስርዓቱ የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት በሀገሪቱ እንዲኖር የሚያግዝ አይደለም፡፡ የአብላጫ ድምጽ አሰጣጥ ስርዓት በኢትዮጵያ ሁኔታ የሕዝቡን ልዩ ልዩ አመለካከቶች፣ እምነቶችና ጥቅሞች የሚወክሉ እንደራሴዎችን ወደሁለቱም ምክር ቤቶች ለማስገባት የሚያስችል አይደለም፡፡ አብዛኞቹ የፌዴራልና የክልል ምክር ቤቶች ካለተወዳዳሪ በሕዝብ ተመርጠዋል እየተባሉ የተሰባሰቡ ናቸው፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩና የየክልሉ ፕሬዚዳንቶች ብቻ ሳይሆኑ አብዛኞቹ የምክር ቤት አባላት በነጻ ውድድርና በሕዝብ ፈቃድ ተመርጠው የተሰባሰቡ ሳይሆኑ በምርጫ ስም ራሳቸውን በራሳቸው የሕዝብ ተወካይ አድርገው የሰየሙ ናቸው፡፡ በሁለቱም ምክር ቤቶች ውስጥ የተሰባሰቡ ካድሬዎች ሕዝቡን የሚወክሉና ለሕሊናቸው የሚገዙ ሳይሆኑ ገዥው ፓርቲ የሰጣቸውን ድርጅታዊ ተልዕኮ ለማሳካት ሲሉ በሕዝብና በሀገር ቅም ላይ አደገኛ ውሳኔ ለመስጠት የማያመነቱና «ቅጥረኞች» የሚል ስም ቢሰጣቸው የሚያንሳቸው ናቸው፡፡ በየትኛውም የዴሞክራሲ ስርዓት እንደሚሰራበት በሕዝብ ጥቅምና በወከላቸው ፓርቲ ፍላጎት መካከል ግጭት ሲያጋጥም ለሕዝብ ጥቅም ወግነው ነጻ ውሳኔ ከመስጠትና ለሕሊናቸው ተገዥ ከመሆን ይልቅ አይናቸውን ጨፍነው ለገዥው ፓርቲ ዲስፒሊን የሚታዘዙና የሕዝብን ጥቅም ከመርገጥ የማይመለሱ ናቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ምክር ቤቶቹ በሕገመንግስቱ መሰረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚመራው የመንግስት አስፈጻሚ አካል ቁጥጥርና ተጽዕኖ ስር የሚወድቁበት ሁኔታ በመፈጠሩ በዚህ አካል ከሚቀርብ አጀንዳ ወጥተው የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት ነጻ ውይይት ማድረግና ሕግ ማውጣት አይችሉም፡፡ እንዲያውም በሕገመንግስቱ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ 1 እንደተደነገገው ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት የተወካዮች ምክር ቤት እንዲበተን ለማድረግ የሚያስችል ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ ይህ ምክር ቤት ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ፈቃድ ቢወጣ የሚጠብቀውን አደጋ ስለሚያውቅ ነጻ ሆኖ ለመስራት የሚችልበትን የሕግና የሞራል ነጻነት የተነጠቀ አካል ነው፡፡ እንደዚህ ባለው መዋቅራዊና ሕገመንግስታዊ ማነቆ የተተበተቡ ምክር ቤቶች የሕዝብ ስልጣን ባለቤትነት መገለጫና የተሳትፎ ማረጋገጫ ተቋሞች ተደርገው የሚታዩ አይደሉም፡፡

ስለዚህ ከአስፈጻሚው አካልና ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ሙሉ ቁጥጥርና ተጽዕኖ ነጻ ሆነው የሚመሩ ሕግ አውጭ አካላት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ስርዓት ውስጥ እንዲፈጠሩ ከተፈለገ መደረግ የሚገባቸው መሰረታዊ ጉዳዮች አሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያ መደረግ ያለበት የተወካዮች ምክር ቤትና ሴኔቱ ነፃ በሆነ ውድድር የሚመረጡ እውነተኛ የሕዝብ ተመራጮች የሚወከሉባቸው የዴሞክራሲ ተቋሞች መሆናቸው መረጋገጥ አለበት፡፡ ይኸንን ለማረጋገጥ ከሚያስችሉት መንገዶች አንደኛው ነጻና ገለልተኛ የምርጫ ተቋም መፍጠር ነው፡፡ ነጻና ገለልተኛ የምርጫ ተቋም መፍጠር ብቻውን ለእነዚህ ተቋሞች ዴሞክራሲያዊ መሆን በቂ መተማመኛ ላይሆን ይችላል፡፡ በተለይ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ባለ ሰፊ የማህበራዊ ውክልናና

የአመለካት ልዩነቶች ባለበት ሀገር ከአብላጫ ድምጽ ስርዓት ይልቅ የተመጣጠኝ ውክልና ስርዓት የመራጩን ሕዝብ ልዩ ልዩ ፍላጎቶች፣ ጥቅሞችና አመለካከቶች በተሻለ መንገድ ለመወከል ስለሚረዳ የምርጫ ስርዓቱን መቀየር ያስፈልጋል:: በተመጣጣኝ የምርጫ ስርዓት የሕዝቡን አመለካከቶችና ጥቅሞች በሰፊው የሚወክሉ የምርጫ መንግስታት በፌዴራልና በክልሎች ደረጃ መመስረት ከተቻለ ሁለቱ የሕግ አውጭ ምክር ቤቶች ከአስፈጻሚው አካል ሙሉ ቁጥጥርና ተፅዕኖ ነጻ ሆነው የሚሰሩ የዴሞክራሲ ተቋሞች የሚሆኑበት እድል ሰፊ ነው::

በሶስተኛ ደረጃ ሁለቱ ምክር ቤቶች በተለያየ የውክልና መሰረት ላይ እንዲመሰረቱና ተመጣጣኝ ስልጣን እንዲኖራቸው ያስፈልጋል:: የፌዴራል ስርዓት አደረጃጀት በሚጠይቀውና የዴሞክራሲ መርህ በሚፈቅደው መሰረት የተወካዮች ምክር ቤት በሕዝብ ቁጥር ላይ ተመስርቶ በምርጫ የሚቋቋም ሕግ አውጭ ምክር ቤት መሆኑ ይታወቃል:: ይሁን እንጂ ሁሉም ክልሎች በሁሉም ሁኔታ እኩል ደረጃ ላይ ስለማይገኙ ዜጎች በዚህ ምክር ቤት ብቻ የሚኖራቸው ውክልናና ተሳትፎ በቂ አይደለም:: ቁልፍ በሆነው ሕግ የማውጣት ስራና የመንግስት ተግባር ተመጣጣኝ ውክልናና እኩል ተሳትፎ እንዲያደርጉ ከተፈለገ ሁሉም ክልሎች በእኩል ደረጃ የሚወከሏቸው ተወካዮች የሚገኙበት ሌላ ምክር ቤት (ሴኔት) መቋቋም ይገባዋል:: ይኸኛው ምክር ቤት ከተወካዮች ምክር ቤት በተለየ መንገድ የአናሳዎች ውክልና ትርጉም ባለው ሁኔታ የሚረጋገጥበት እንዲሆን ሁሉም ክልሎች ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸው ተወካዮችን መወከላቸው ብቻ በቂ አይደለም:: ከዚህ በተጨማሪ ከአናሳ ክልል ወይም ከብዙሃን ክልል የመጣ እየተባለ ልዩነት የማይደረግበትና ከሁሉም አካባቢ የመጡት ተወካዮች እኩል ድምጽ እንዲኖራቸው በሕግ የተረጋገጠ መብት መፍቀድ ይገባል::

ሌላው ጠቃሚ እርምጃ ሁለቱ ምክር ቤቶች ሕግ በማውጣት ረገድ ተመጣጣኝ ስልጣን ሊኖራቸው ይገባል የሚለው ነው:: በብዙዎቹ ዴሞክራሲያዊና ፌዴራላዊ ስርዓት በመሰረቱ ሀገሮች የሴኔቱና የተወካዮች ምክር ቤት ስልጣን ተመጣጣኝ እንዲሆን በማድረግ ዜጎች ሕግ በማውጣት ተግባር ያላቸው ተሳትፎ የሚሰፋበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ከፍተኛ ጥረት ይደረጋል:: እንዲያውም ከክልሎች አስተዳደርና ፋይናንስ ጋር የተያያዘ የሕግ ጉዳይ ሲሆን የሴኔቱን ድጋፍ ካላገኘ ውድቅ የሚሆንበትን ሕጋዊ ስርዓት በመፍጠር ከተወካዮች ም/ቤት የማያንስ ስልጣን እንዲኖረው ይደረጋል::

የዚህ ዓይነቱ የአሰራር መርህና ልምድ ለኢትዮጵያ ሁኔታም የሚጠቅም ነው:: ሴኔቱ ከተወካዮች ምክር ቤት ጋር የሚመጣጠን ስልጣን እንዲኖረው ማድረግ ማለት የአናሳዎችን ጥቅምና ፍላጎትም በእኩል ደረጃ ማረጋገጥ ማለት ነው:: እንያዲውም ሴኔቱ እንደተወካዮች ምክር ቤት የፓርቲ ውክልና ያላቸው ፖለቲከኞች ብቻ የሚሰባሰቡበት ሳይሆን በሞያቸው፣ በስነምግባራቸውና በስራ ልምዳቸው ከፍተኛ ሕዝባዊ ከበሬታና ተቀባይነት ያገኙ ሰዎችም ጭምር ከተለያዩ ክልሎች የሚወከሉበት ምክር ቤት ስለሚሆን ከፓርቲ አጀንዳና ክፍፍል ወጣ ብሎ ለመወያየት የሚያስችል መድረክ ሆኖ ያገለግላል:: ስለዚህ በተወካዮች ምክር ቤት አደረጃጀትና አሰራር ባህርይ የተነሳ ብዙ ትኩረት የማያገኙ ጉዳዮች በዚህኛው ምክር ቤት የሚታዩበት እድል ስለሚኖር የአንደኛውን ጉድለቶች በሌላኛው እያካካሱ የዜጎችን ጥቅምና ፍላጎት በተሟላ መንገድ የሚያስጠብቁ ተቋማት ማድረግ ይቻላል:: ስለሆነም የሁለቱ ምክር ቤቶች ስልጣን ተመጣጣኝ እንዲሆን ማድረግ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው:: የሴኔቱ አባላት በየክልሉ ሕዝብ በቀጥታ ወይም በተወካዮቻቸው እንዲመረጡ ማድረግ ይቻላል:: በሕግ አወጣጥ ላይ ሁለቱ ምክር ቤቶች ስምምነት ላይ መድረስ የማይችሉበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከሁለቱም ምክር ቤቶች የተውጣጡ አባላት የሚገኙበት የግልግል ኮሚቴ በመመስረት የመስጠትና የመቀበል ዘዴ እየተጠቀሙ ስምምነት እንዲፈጠር ይደረጋል::

አራተኛው ጠቃሚ ነጥብ የሕግ አውጭ ምክር ቤቶች በአስፈጻሚው አካል ላይ ቁጥጥር ማድረግ የሚያስችል ስልጣን ሊኖራቸው የሚገባ መሆኑ ነው:: አሁን በስራ ላይ ባለው ሕገመንግስት የሕግ አውጭ ምክር ቤቶች በአስፈጻሚው አካል ላይ ቁጥጥር የሚያደርጉበት ግልፅ ስርዓት አልተቀመጠም:: በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 72 ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ጠቅላይ ሚኒስትሩና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪዎች መሆናቸውና በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑ ተደንግጓል:: ነገር ግን በፓርላማ ፊት እየቀረቡ የስራ ሪፖርት ከማሰማት በስተቀር ጥፋት ቢገኝባቸው ምክር ቤቱ ምን ዓይነት የቅጣት ውሳኔ ሊሰጥ እንደሚችል በግልጽ የተቀመጠ የሕግ ስርዓት የለም:: በሕገመንግስቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 17 የተወካዮች ምክር ቤት ጠቅላይ ሚኒስትሩንና ሌሎች የፌዴራል መንግስት ባለስልጣናትን ለጥያቄ የመጥራትና የሕግ አስፈጻሚውን

አሰራር የመመርመር ሥልጣን እንዳለው እንዲሁም በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 18 ለሕግ አስፈጻሚ አካል በተሰጠ ማንኛውም ስልጣን ላይ የምክር ቤቱ አባላት በአንድ ሶስተኛ ድምጽ ሲጠይቁ ምክር ቤቱ እንደሚወያይና አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ የመውሰድ ስልጣን እንዳለው የተደነገገ ቢሆንም የሚወስደው እርምጃ ግልጽ ሆኖ የተወሰነ አይደለም። በተለይም በንዑስ አንቀጽ 18 የሰፈረው በቅድመ ሁኔታ የታሰረ በመሆኑ ለምክር ቤቱ ተሰጠ የሚባለውን ስልጣን በስራ ላይ ለማዋል በቀላሉ የሚቻለው አይደለም። ስለዚህ እነዚህ ምክር ቤቶች በአስፈጻሚው አካል ያሉትን ጨምሮ ማንኛውም የመንግስት ባለስልጣን በመንግስት ስልጣን ላይ እያለ የክህደት፣ የሰብዓዊ መብት ረገጣ፣ የጉቦ፣ የስርቆት ወንጀል ወይም ሌላ ከፍተኛም ሆነ አነስተኛ ጥፋት ሲፈፅም እንዲከሰስ የመወሰን ስልጣን (power of impeachment) በሕገ መንግስቱ በግልጽ ሊሰጣቸው ይገባል።

በሕገመንግስቱ አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 2 አስፈፃሚው አካል ማለትም የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት በመንግስት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነት እንዳለባቸው የተደነገገው ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ሕግ አውጭው ምክር ቤት የትምምን ድምጽ በመስጠት ሲደግፍ ወይም ድጋፉን ሊነፍግ የሚችልበት ስልጣን በግልፅ ሲሰጠው ነው። አሁን በስራ ላይ ባለው ሕገመንግስት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የተወካዮች ምክር ቤትን ለማፍረስ ስልጣን ሲሰጠው ሕግ አውጭው ግን በሕግ አስፈጻሚው ላይ ከባድ ጥፋት ቢያገኝ ሥልጣኑን እንዲለቅ ለማድረግ የሚያስችል ሕጋዊ መብት በግልፅ አልተሰጠውም። በዚህም ምክንያት አስፈፃሚው አካል የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ፣ ከፍተኛ ጥፋት በተደጋጋሚ ጊዜ እየፈፀመ የሚጠይቀው ባለመኖሩ ታላቅ ብሔራዊ ጥቅሞች ጉዳት ደርሶባቸዋል። አንድም ጊዜ ግን የሚጠበቅበትን ኃላፊነት ያልተወጣውን አስፈጻሚ አካል ከሥልጣን እንዲወገድ ማድረግ ይቅርና ምክር ቤቱ ወቀሳ ለመሰንዘር እንኳ እንዳልቻለ ታይቷል።

ስለዚህ ፓርላማው ሙሉ በሙሉ በአስፈፃሚው አካል ቁጥጥርና ተፅዕኖ ስር ከወደቀበት ሁኔታ ነጻ ወጥቶ፣ እንዲያውም በአስፈጻሚው አካል ላይ ወግና ስርዓት ባለው መንገድ ቁጥጥር ማድረግ እንዲችል በጠቅላይ ሚኒስትሩና በሌሎች ሚኒስትሮች ላይ የትምምን ድጋፍ የመስጠትና የመንፈግ ስልጣን በግልጽ ሊሰጠው ይገባል። በዚህ ስልጣን እየተጠቀመ አስፈጻሚው አካል በሕጉ መሰረት ኃላፊነቱን የሚወጣ መሆንና አለመሆኑን፣ የተፈቀደለትን የመንግስት ገንዘብና ንብረት ለታሰበው አላማ ማዋሉንና አላማዋሉን፣ ቢሮክራሲውንና አስተዳደራዊ ዘርፉን በብቃት እየመራ መሆንና አለመሆኑን፣ ማንኛውም በአስፈጻሚው አካል የሚፈፀም ተግባር በሕጋዊ መሰረት ላይ የቆመ መሆን አለመሆኑን መቆጣጠር አለበት።

አንድ የምክር ቤት አባል በፓርላማ ውስጥ አገልገሎት በሚሰጥበት ጊዜ የሕዝብ ወኪልና ለሕሊናው ታማኝ መሆኑን በነጻነት ማረጋገጥ እንዲችል ለዕጩነት ካቀረበው ፓርቲ ዲስፕሊን እስረኝነት ሊላቀቅና ከማንኛውም ባለስልጣን ተፅዕኖ ነፃ ሊሆን ይገባል። ይኸንን ነፃነቱን ለመጠበቅ በምክር ቤት ውስጥ በሚይዘው አቋም አባል ከሆነበት ፓርቲ አቋም ቢለይና ከፓርቲ አባልነቱ ቢባረር እንኳ የፓርላማው አገልግሎት ጊዜ እስከሚጠናቀቅ የፓርላማ መቀመጫውን እንደያዘ መቆየት የሚያስችለው የሕግ ድንጋጌ መኖር አለበት። አካባቢያዊና ብሔራዊ ጠቀሜታ ያላቸውን የፖሊሲና ሌላም ጉዳዮች እያነሱ ክርክር ማካሄድ፣ በመገናኛ ብዙሃንና በተለያዩ ጆርናሎች ማሰራጨት፣ ለመራጩ ሕዝብ የመረጃ ምንጭ ሆኖ ማገልገልና የሕዝቡን ፖለቲካዊ ግንዛቤ ማሳደግ አንዱና ዋነኛው የሕግ አውጭ አካላት ኃላፊነት በመሆኑ ይኸንኑ ተግባራቸውን በሚገባ እንዲወጡ የሚያስችል ሕጋዊ መብት ሊኖራቸው ይገባል። ከሁሉም በላይ በአስፈፃሚው አካል የሚቀርብላቸውን ሕግ ከማጽደቅ በተጨማሪ በራሳቸው አነሳሽነት ሕግ ማውጣት እንዲሁም የመራጩን ሕዝብ መሰረታዊ ጥቅሞችና ፍላጎቶች እየተከተሉ፣ አዳዲስ ክስተቶችና ለውጦች በሀገር ላይ የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ እየመረመሩና መጪውን ሁኔታ በጥንቃቄ እየገመገሙ የሕገመንግስት ማሻሻያ ሃሳብ ማቅረብና ውሳኔ መስጠት ከሕግ አውጭ ምክር ቤቶች የሚጠበቅ ከፍተኛ ኃላፊነት በመሆኑ ይኸንን ለመፈፀም የሚያስችል መብት ሊኖራቸው ይገባል።

እስካሁን ድረስ የተዘረዘሩትን ኃላፊነቶች ምክር ቤቶች በሚገባ እንዲፈጽሙ ትልቅ ድጋፍ ከሚሰጡት አካላት መካከል የሕግ አውጭ ምክር ቤቶች አፈጉባኤዎች ይገኙበታል። እነዚህ አፈጉባኤዎች በፓርላማው ብዙ መቀመጫ ካገኘው ፓርቲ መመረጥ አለባቸው የሚል ዩኒቨርሳል ሕግ የለም። ትልቁ መመዘኛ የምክር ቤቶቹን ውይይትና ክርክር ከአድሎ በፀዳና ስርዓትን በተከተለ መንገድ ለመምራት የሚያስችል ብቃትና ችሎታ ይዞ መገኘት ነው። አንድ የምክር ቤት አፈጉባኤ ለአንድ

*የተወሰነ ፓርቲ ሀሳብ ደጋፊ ሆኖ በመቆም ራሱ በክርክሩ ውስጥ ወገን ለይቶ የሚሰለፍ ከሆነ የምክር ቤቱን ውይይት ስርዓት ለማስያዝም ይሁን በተወሰነ አጀንዳ ላይ ሚዛናዊ ክርክር እንዲደረግበትና ጠቃሚ ውሳኔ ላይ እንዲደረስበት ለማድረግ አይችልም፡፡ ለዚህ ዓይነቱ ኃላፊነት የሚመረጥ ሰው ከፍተኛ ትዕግስት፣ የማመዛዘን ችሎታና ሀሳቦችን የማሰባሰብ ተሰጥኦ ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ የአፈጉባኤው ገለልተኝነት በፓርላማ ክርክር ወቅት ብቻ ሳይሆን ከፓርላማ ክርክር ውጭም መኖር ያለበት ሲሆን የምክር ቤቱን ጥቅም መጠበቅና ወኪል ሆኖ ማገልገል ይኖርበታል፡፡ እንዲህ አይነት አፈጉባኤ ካለ ምክር ቤቶች ተልዕኳቸውን ለመወጣት አንድ ምቹ ሁኔታ አግኝተዋል ማለት ነው፡፡*

## 3.2.2. **ሕግ ተርጓሚ**

### 3.2.2.1 **ህገ-መንግስታዊ ፍ/ቤት**

*ከመንግስት ስልጣን አካላት መካከል አንዱ ሕግ ተርጓሚው ነው፡፡ በተለያዩ ዴሞክራሲያዊ ስርዓቶች ውስጥ ይኸኛው የመንግስት አካል ከፖለቲካዊ ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ እንዲደራጅና እንዲሰራ ከፍተኛ ትኩረት ይደረጋል፡፡ በአንዳንዶቹ ሀገሮች ሕገመንግስታዊ ጉዳዮችን ጨምሮ ማንኛውም የፍትህ አስተዳደርና አመራር ተግባር ለፍርድ ቤቶች ብቻ የሚሰጥበት ሁኔታ አለ፡፡ ለምሳሌ፤ በአሜሪካ ማንኛውም የዳኝነትና የፍትህ ተግባር ለከፍተኛው ፍርድ ቤት የተሰጠ ነው፡፡ በሌሎች ሀገሮች ደግሞ በአንድ በኩል ሕገመንግስት የሚተረጉምና ሕገመንግስታዊ የሆኑ ጉዳዮችን የሚዳኝ እንደ የሀገሩ ሁኔታ ሕገ መንግስታዊ ፍርድ ቤት ወይንም የሕገመንግስት ምክር ቤት የሚል ራሱን የቻለ አካል ሲኖር የፍትህ አስተዳደርና አመራር ስራ ደግሞ ራሱን በቻለ የዳኝነት አካል ይከናወናል፡፡ ለዚህ አይነቱ የፍትህ አደረጃጀትና አሰራር ጀርመን እንደ አንድ ምሳሌ ልትጠቀስ ትችላለች፡፡*

*በሀገራችን አሁን በስራ ላይ ባለው ሕገመንግስት አንቀጽ* 62 *ንዑስ አንቀጽ* 1 *እንደተደነገገው ሕገመንግስት የመተርጎም ኃላፊነት ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ተሰጥቷል፡፡ እንዲሁም በሕገመንግስቱ አንቀፅ* 79 *ንዑስ አንቀጽ* 1 *በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ መሆኑ ተደንግጓል፡፡ በዚህ ፅሁፍ በተለያዩ ርዕሶች ተደጋግሞ እንደተብራራው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ተሰጠ የሚባለው ሕገመንግስት የመተርጎም ስልጣንም ሆነ ለፍርድ ቤቶች ብቻ የተሰጠ ነው የሚባለው የዳኝነት ስልጣን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ በመንግስት አስፈፃሚው አካል በተለይም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁጥጥርና ተፅዕኖ ስር የወደቀ ነው፡፡ በኢዴፓ አመለካከት ከዚህ ዓይነቱ ፖለቲካዊ ቁጥጥርና ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ የተደራጀና የሚመራ የሕገመንግስት ተርጓሚና የዳኝነት አካላት መኖር ይገባቸዋል፡፡*

*ኢዴፓ በኢትዮጵያ ውስጥ ሊሰራ የሚችል የፌዴራል አደረጃጀት አማራጭ በሚያቀርብበት ጊዜ ባለሁለት ምክር ቤት ሕግ አውጭ አካል መኖር እንዳለበት ከእነምክንያቱ አቅርቧል፡፡ ሕግ አውጭው አካል ሕገመንግስት የመተርጎም ስራ ደርቦ የሚሰራ ከሆነ የመንግስት አካላት የስልጣን ክፍፍል መርህ እንደሚጣስ ግልጽ ነው፡፡ አስፈፃሚው አካል የሕግ አውጭውንና የሕግ ተርጓሚውን ኃላፊነት ደርቦ መስራት እንደማይገባው ሁሉ ሕግ አውጭውም የሕግ ተርጓሚውንና የአስፈፃሚውን አካል ኃላፊነቶች ጠቅልሎ ሊይዝ አይገባውም፡፡ በእነዚህ የመንግስት አካላት መካከል ግልፅና ተመጣጠኝ የሆነ የሥልጣን ክፍፍልና የእርስ በርስ ቁጥጥር ከሌለ ፌዴራላዊ ስርዓት እንዳለ ሊቆጠር አይችልም፡፡ በሕወሓት/ኢህአዴግ ሕገመንግስት የፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚባለው አካል ከተወካዮች ምክር ቤት ጋር በጋራና በተናጠል ሕግ የማውጣት ስልጣን እንደተሰጠው የሚያሳዩ ሕገመንግስታዊ ድንጋጌዎች ሰፍረዋል፡፡ እንደገና ሕግ የማውጣት ስልጣን ተሰጠቶታል የሚባለው የፌዴሬሽን ምክር ቤት ሕገመንግስት የመተርጎምም ኃላፊነት ደርቦ እንዲሰራ የተደረገበት ሁኔታ በሕግ አውጭውና በሕግ ተርጓሚው መካከል ግልፅ የሆነ የሥልጣን ክፍፍልና የእርስ በርስ ቁጥጥር እንዳይኖር የሚከለክል ነው፡፡*

*ስለዚህ ሕግ አውጭው አካል ማለትም ሁለቱም ምክር ቤቶች ሕገመንግስት የመተርጎሙን ኃላፊነት ራሱን ለቻለ ነፃ አካል መተው ይኖርባቸዋል ብሎ ኢዴፓ ያምናል፡፡ በመሆኑም ሕገመንግስቱን የመተርጎም ስራ በኃላፊነት የሚያከናውን ራሱን በቻለ መንገድ የተደራጀና በነፃነት የሚሰራ ሕገመንግስታዊ ፍርድ ቤት መቋቋም ይገባዋል፡፡ የዚህ ሕገመንግስታዊ ፍርድ ቤት ዋነኛ ኃላፊነት*

ሕገመንግስቱን መተርጎም ነው። ሕገመንግስቱን ከመተርጎም ጎን ለጎን ከዚሁ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች የመዳኘት ኃላፊነት ይኖረዋል። በፌዴራሉ መንግስትና የፌዴራሉ አባል በሆኑት የክልል መንግስታት መካከል ወይም በፌዴራል መንግስት የተለያዩ ተቋሞች መካከል አለመግባባት ቢፈጠር ዳኝነት ይሰጣል። ለሕገመንግስታዊው ስርዓት ማለትም ለነፃነትና ለዴሞክራሲ አደጋና ስጋት ነው ብሎ ያመነበትን ፓርቲ ወይም ቡድን ሕገመንግስታዊ አለመሆኑን የመወሰንና የማገድ ስልጣን ይኖረዋል። የፌዴራሉና የክልል መንግስታት የሚያወጧቸው አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን ሕገመንግስት የማይፃረሩ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። ከዚህ በተጨማሪ እያንዳንዱ ዜጋ መሰረታዊ መብቱ በመንግስት እንደተጣሰ በማመን አቤቱታ በሚያቀርብበት ጊዜ የመዳኘት ስልጣን ይኖረዋል። እነዚህን ኃላፊነቶቹን የሚወጣው በፌዴራሉ ወይም በክልል መንግስታት ጥያቄ ሲቀርብለት አልያም በፌዴራልና በክልል መንግስታት ፓርላማዎች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በዜጎችና ወዘተ. በመሳሰሉት ሲጠየቅ ነው።

የሕገመንግስታዊ ፍርድ ቤቱ አባላት ከፍተኛ የሕግ ሞያና ልምድ ያላቸው እንዲሆኑ የሚጠበቅ ሲሆን ለዚህ ስራ የሚመረጡበት ሁኔታ ደግሞ የሕዝቡን የስልጣን ባለቤትነት በሚያረጋግጥ መንገድ መፈፀም ይኖርበታል። ስለሆነም የሕገመንግስታዊ ፍርድ ቤት አባላት ቁጥር ከዘጠኝ የማይበልጥ ሆኖ ሶስቱ በተወካዮች ምክር ቤት፣ ሶስቱ በሴኔቱና ሶስቱ ደግሞ በአስፈፃሚው አካል ተመርጠው ሹመታቸው በኮንግረሱ ማለትም በተወካዮች ምክር ቤትና በሴኔቱ የጋራ ስብሰባ እንዲፀድቅ ማድረግ ይቻላል። እንደዚህ ዓይነት አመራረጥ፣ ውክልናና የሹመት አሰጣጥ ስርዓት መኖሩ በአንድ በኩል የሕገመንግስታዊ ፍርድ ቤቱን ኃላፊነት ከፍተኛነት ከማሳየቱም በላይ በሌላ በኩል ደግሞ የዚህ ፍርድ ቤት አብዛኞቹ አባላት የሕዝቡ ተወካዮች በሚገኙባቸው ሁለት ምክር ቤቶች የሚመረጡና የሚሾሙ መሆናቸው በዚህም አካል አመሰራረት የሕዝብ ስልጣን ባለቤትነት መረጋገጡን ያመለክታል። ከዚህ በተጨማሪ ሕገመንግስት የመተርጎም ኃላፊነት በሕዝቡ ላልተመረጡ የሕግ ሞያተኞች ብቻ መተው የለበትም እየተባለ አልፎ አልፎ የሚቀርበውን ስሞታ መሰረት ያሳጣዋል።

### 3.2.2.2 **ነፃ የፍትህ ስርዓት**

ማንኛውም ዴሞክራሲያዊ መንግስት ውጤታማና ጠንካራ መሆን የሚችለው ሕዝቡ የመረጣቸው ተወካዮች የሚያወጡት ሕግ ተፈፃሚ ሲሆንና ሲከበር ነው። ሕግ እንዲከበርና ተፈጻሚ እንዲሆን የሚያስችል፣ ከወገንተኝነት ነፃ የሆነ ፍትህ ለማዳረስ የሚረዳ ቅልጥፍና፣ ብቃትና ጥንካሬ ያለው፣ በዚህም ምክንያት የሕዝቡን እምነት ያገኘ የዳኝነት አካል መኖር አለበት፣ እንደዚህ አይነት የዳኝነት ተቋም ከሌለ የሕግ መኖር ትርጉም የሚያጣበትና ስርዓት ማስጠበቅ የማይቻልበት ሁኔታ ይፈጠራል። የዳኝነት ተቋሞች ከሚጠበቅባቸው ተግባሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ በዜጎችና በባለስልጣናት መካከል ክርክር ሲኖር ገለልተኛ የሆነና ከማንኛውም ውጫዊ ኃይል ተፅዕኖ የተጠበቀ ነፃ ዳኝነት በመስጠት በመንግስት ሊፈፀም የሚችልን የዘፈቀደ አሰራር መከላከል፣ በአጥፊዎች ለሚፈፀም የሕግ ጥሰት ትክክለኛውን ሕጋዊ ቅጣት መወሰን፣ በዜጎች መካከል ለሚነሱ ግጭቶች ውሳኔ መስጠት፣ በሌሎች መብት ላይ ሕገወጥ ጣልቃገብነት የሚፈፅምን ማንኛውም ሰው መግታት፣ በደል የተፈፀመበት ሰው በተቻለ መጠን ለደረሰበት ጉዳት ማካካሻ የሚያገኝበትን ሕጋዊ ውሳኔ መስጠት ናቸው።

የዳኝነት ተቋሞች እነዚህን ኃላፊነቶች እንዲወጡ ቢያንስ ሶስት መሰረታዊ መርሆዎች መጠበቅ አለባቸው። እነዚህም አንደኛ የፍትህ ስርዓቱ እንደ አንድ ከፍተኛ የመንግስት ተግባር በትኩረት መታየት የሚገባው ብቻ ሳይሆን ፍትህ በራሱ እንደግብ መቆጠር ያለበት መሆኑ ነው። መንግስት ለዜጎች ፍትህ ከማረጋገጥ የበለጠ ቁልፍ ስራ ሊኖረው አይችልም። ከዚህ ሌላ ማን ተፈረደለት ወይም ማን ተፈረደበት የሚለው ከግምት ውስጥ ሳይገባ በሕጉ መሰረት ፍርድ መስጠቱና ፍትህ መገኘቱ በራሱ እንደግብ መታየት ይገባዋል። ሁለተኛው መሰረታዊ መርህ በማንኛውም ሁኔታ የዳኞች ነፃነት የተጠበቀ መሆኑ ሊረጋገጥ የሚችለው ራሳቸውን ከመደበኛ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ገለልተኛ አድርገው መገኘት ሲችሉ ነው የሚለው መርህ ነው። በሶስተኛ ደረጃ ሊጠቀስ የሚችለው ሌላ መርህ ፍትህ ለመንግስት የፖለቲካ ተግባርና ዓላማ ማስፈፀሚያ መሳሪያ መሆን የለበትም የሚለው ነው። ይኸም ማለት የፍትህ አስተዳደር ከፖለቲከኞች ቁጥጥርና ተፅዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ መደራጀትና መስራት አለበት ማለት ነው።

በማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ሀገር ውስጥ የሕግ ተፈፃሚነት ስርዓት በዜጎች ተአማኒነትና ሕጋዊ ተቀባይነት እንዲኖረው ከተፈለገ የፍትህ ተቋሙ በአደረጃጀትም ሆነ በአሰራር ከማንኛውም ውጫዊ ተፅዕኖ ነፃና ገለልተኛ መሆን አለበት፡፡ ይህ ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀላል መንገድ ደግሞ በፍትህ ስራ ላይ የሚሰማሩ ሰዎች በተለይም ሕግ የማስከበር ተግባር የሚያከናውኑ ዳኞች፣ አቃቤ ሕጎችና ፖሊሶች ከፖለቲካ ተፅዕኖና ከአድሎ ነፃ ከሆኑ ሕጉን በሀገሪቱ ውስጥ ለሚገኙ ሁሉም ሰዎች በተመሳሳይ መንገድ ተግባራዊ ያደርጉታል፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ በማንኛውም ስርዓት ውስጥ ከፖለቲካዊ ግፊት ሙሉ በሙሉ ነጻ የሆኑና ከፖለቲካዊ ተሳትፎም በገለልተኝነት የቆሙ ዳኞች ጠበቆች፣ የአቃቤ ሕግ ሠራተኞችና ፖሊሶች ማግኘት ይቻላልን? የሚለው ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ሁልጊዜ ቀላል አይደለም፡፡ ፍትህ በማስከበር ስራ ላይ የሚሰማሩት ዜጎች ሰዎች እንደመሆናቸው መጠን ለብዙ ዓይነት ተፅዕኖዎች የተጋለጡ መሆናቸው ጨርሶ ሊወገድ የሚችል ባይሆንም ችግሩን የሚቀንሱ ስርዓቶችና አሰራሮች እንዳሉ ደግሞ አይካድም፡፡

በፍትህ ስርዓቱ ውስጥ የሚሰማሩ ሰዎች ማህበራዊ መሰረት፣ የሚሰጣቸው የሕግ ስልጠና ዓይነት፣ የግል ፖለቲካዊ አመለካከትና እምነት፣ የሕብረተሰቡ ባህልና የፖለቲካ ስርዓቱ ባህርይ፣ እንዲሁም ሌሎች በርካታ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች በስራቸው ላይ የሚያሳርፉት ተፅዕኖ ይኖራል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህን ተፅዕኖዎች ለመከላከል የሚረዱ በርካታ የመፍትሔ አማራጮችን በስራ ላይ በማዋል በፍትህ ስራ የተሰማሩ ክፍሎችን ነፃነትና ገለልተኝነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ አንደኛው መፍትሔ በፍትህ ስራ ለተሰማሩ ሰዎች የሕግ ችሎታና የሞያ ስነምግባር መጠናከር የሚረዳ ብቁ ስልጠና መስጠት ነው፡፡ ጥልቀት ያለው የሕግ ስልጠና ያገኘ ዳኛ፣ አቃቤ ሕግና ፖሊስ ስራን በሕጉ መሰረት ለማከናወን የሚያስችል ብቃትና የሞያ ሥነምግባር ለመጨበጥ የተሻለ እድል ያገኛል፡፡

ሁለተኛው መፍትሔ በፍትህ ስራ የተሰማሩ ሰዎች ስራቸውን በሚከናውኑበት ጊዜ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መስክ የተሰማሩ  ሰዎች ተግባራቸውን በሚገባ የመግለፅና አሳማኝነቱን የማስረዳት ሕጋዊ ግዴታ አለባቸው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በስራቸው ወቅት ለሚፈጽሙት ጥፋት በሕግ የሚጠየቁበት ስርዓት መኖር አለበት፡፡ ተጠያቂነት ሲባል የፖለቲካ ተጠያቂነት እንዳልሆነ መታወቅ ይኖርበታል፡፡ ዳኞች፣ አቃቤ ሕጎችና ፖሊሶች በሚሰሩት ስራ ከማንኛውም ዓይነት ፖለቲካዊ ተፅዕኖና ፖለቲካዊ ተጠያቂነት ሊጠበቁ ይገባቸዋል፡፡ በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ከባለስልጣኖች የተለየ መሰረታዊ አቋም እንዳላቸው ቢታወቅም እንኳ ከፖለቲካ ተጠያቂነት መጠበቅ አለባቸው፡፡ ነገር ግን በሕግ አግባብ የተቀመጡ መደበኛ የመቆጣጠሪያ ስርዓቶች ሊኖሩ ይገባቸዋል፡፡

በፍትህ ስራ የተሰማሩ ሰዎች የግል አመለካከትና እምነት ምንም ይሁን ምን ስራቸውን በሕጉ መሰረት ማከናወናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ በግል ፍላጎት፣ በውጫዊ ኃይል ግፊትና ተፅዕኖ እየተመሩ እንደማይሰሩ ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ሌላው መቆጣጠሪያ ደግሞ በፍትህ ስራ የሚሰማሩ ሰዎች ከተለያዩ ማህበራዊ ክፍሎች የተውጣጡ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከሚሰጣቸው የሞያ ስልጠና በተጨማሪ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን የሚወክሉ መሆናቸውን ማረጋገጥ ፍትህን ለማስፈን አንድ ጠቃሚ መቆጣጠሪያ ዘዴ ሊሆን ይችላል፡፡ ወንዶችና ሴቶች፣ ወጣቶችና ጎልማሶች፣ ወዘተ. በፍትህ ስራ ውስጥ የጋራ ተሳትፎ እንዲኖራቸው በሚደረግበት ጊዜ ወገንተኝነትና አድሎን ለመከላከል ያግዛል፡፡ በፍትህ ስራ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲኖር የሚያግዝ ሌላው መንገድ የጁሪ አሰራርን መጠቀም ነው፡፡ የተለያዩ ጉዳዮችን መርምረው ውሳኔ እንዲሰጡ በሕዝብ ምርጫ የሚሰየሙ የጁሪ አባላት ከተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚውጣጡ ስለሚሆኑ ከአድሎና ወገንተኝነት የፀዳ ፍትህ ለማስገኘት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይኖራቸዋል፡፡ በጁሪ ተግባር የሚሰማሩ ሰዎች ከሌሎች መመዘኛዎች ጋር የሕግ እውቀት ያላቸው መሆኑን ማረጋገጥ ውሳኔያቸው በሕጉ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያስችላል፡፡

ዳኞች ስራቸውን በሚያካሂዱበት ጊዜ በስራ ላይ ባለው ሕግ ወይም ሕገመንግስታዊ ድንጋጌ በሚገባ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሟቸው ወይንም የሕጉ ትርጉም ከፊታቸው ለቀረበው ጉዳይ በሚስማማ ግልጽነት ያልሰፈረ ሆኖ ሲያገኙት ወይንም አሻሚና ከአንድ በላይ ትርጉም የሚሰጣቸው ሆኖ ሲገኝ ሁለት መንገዶችን ተጠቅመው ሊሰሩ ይችላሉ፡፡ አንደኛው መንገድ በሕገመንግስቱ ድንጋጌ ውስጥ ግልጽ ሆነው ከተቀመጡት ቃላቶች በመነሳት በስራ ላይ ካለው ሕገመንግስትና ሌሎች ሕጎች ተፈፀጻሚነት አንፃር ተገቢ ነው ብለው በሚያምኑበት ሀሳብ መሰረት የቀረበላቸውን ጉዳይ

መርምረው ውሳኔ ይሰጣሉ:: ሁለተኛው መንገድ ደግሞ ሕገመንግስቱን ወይም ሕጉን ያረቀቁት ሰዎች በመጀመሪያ በአዕምሯቸው ውስጥ ምን ታሳቢዎችን ይዘው እንዳረቀቁት ለመረዳት በመሞከር በቀረበላቸው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ:: ይህ አሰራር የዳኞችን ነጻነት ከመጠበቅ አልፎ ሕግን በአግባቡ የመተርጎም ብቃት እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል::

በቲዎሪ ደረጃ የዳኞች ሚና ሕገመንግስትንና ሌሎች ሕጎችን በሚቀርቡላቸው ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው:: የሕገ መንግስትንና የሌሎች ሕጎችን መሰረታዊ ትርጉም በመረዳትና በዳኝነት ስራ ውስጥ ተፈጻሚ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ በዳኞች መካከል የተወሰኑ ልዩነቶች ሊኖሩ ይችላሉ:: አንዳንዶቹ የቀረቡላቸውን ጉዳዮች መርምረው በሚወስኑበት ጊዜ በሕገመንግስቱ ወይም በሕጉ ላይ ያሉትን ቃላቶች እንደመነሻ አድርጎ በመጠቀም ፋንታ አንዳለ በደረቁ እየወሰዱ ስራ ላይ ያውሏቸዋል:: በሕጉ ውስጥ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሟቸው በሕገመንግስት ማሻሻያ ወይንም በሕግ ክለሳ ጉድለቶቹ እስኪሟሉ ድረስ ምንም ጥረት አለማድረግን ይመርጣሉ:: ማንኛውንም የቀረበላቸውን ጉዳይ በሕጉ ውስጥ የተቀመጡትን ቃላቶች በጥብቅ ተከትለው ለመወሰን ይሞክራሉ:: ሌሎች ደግሞ የሕገመንግስቱንና የሕጉን መንፈስ ተከትለው ተገቢ መስሎ የሚታያቸውን ውሳኔ ይሰጣሉ:: በዚህም የተነሳ የሕጉን ይዘት የሚወስኑት ሕጉን ያወጡት አካላት ሳይሆኑ ዳኞች ራሳቸው ናቸው የሚል ክርክር አለ:: በተደጋጋሚ ጊዜ በዳኝነት መድረክ ላይ ለሚነሱ ተመሳሳይ ጉዳዮች መስጠት የሚገባውን ብይን ይዘት በመወሰን ዳኞች የሚጫወቱት ሚና መኖሩ ባይካድም የሕገመንግስትንና የሕግን ይዘት እንደሚወስኑ ተደርጎ የሚቀርበው ክርክር ግን በመጠኑም ቢሆን የተጋነነ ነው:: ምክንያቱም በዳኞች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ለአተረጓጎምና ለአወሳሰን ልዩነቶች መስፋት አስተዋፅኦ የሚያደርግ ሕገመንግስታዊ ወይም ሌላ ሕጋዊ ድንጋጌ መኖሩን ባመኑ ጊዜ ሕግ አውጭው አካል ሕገመንግስታዊ ማሻሽያ የማድረግና ሕጋዊ ክለሳ የማካሄድ በማንም የማይነጠቅ ብቸኛ ስልጣን ስላለው ነው::

ከዚህ አጠቃላይ መሰረተ ሃሳብ በመነሳት በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የፍትህ ስራ ለመገምገም በሚሞከርበት ጊዜ መሰረታዊ የሆኑ በርካታ ችግሮች መኖራቸውን ለመገንዘብ ይቻላል:: በሀገሪቱ ውስጥ ነጻ የፍትህ ስርዓትና ይኸንኑ ተግባራዊ የሚያደርጉ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት የሉም:: የዳኝነትና የፖሊስ ተቋማቱ ቀጥተኛ ፖለቲካዊ ቁጥጥርና ተጽዕኖ የሚደረግባቸው ናቸው:: አሁን በስራ ላይ ያለው ሕገመንግስት በአንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ስልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ እንደሆነ፣ በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም የመንግስት አካል፣ ከማንኛውም ባለሥልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተፅዕኖ ነፃ መሆኑን፣ በንዑስ አንቀጽ 3 ደግሞ ዳኞች ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት እንደሚያከናውኑና ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ እንደማይመሩ፣ በንዑስ አንቀጽ 4 ከፊደል ሀ - ሐ የተዘረዘሩ ሁኔታዎች ካልተሟሉና በሕግ የተወሰነው የጡረታ እድሜ ካልደረሰ በስተቀር ከዳኝነት ስራቸው እንደማይታገዱ ተደንግጓል:: ይሁን እንጂ የዳኝነት ተቋሙ በዚህ ሕገመንግስታዊ ድንጋጌ መሰረት ለመስራት በማያስችለው መዋቅራዊ ችግር የተጠለፈ ነው:: በዳኝነት ስራ የተሰማሩ ሞተኞች ተጨባጭ ባልሆነ ሰበብና ፖለቲካዊ በሆነ መመዘኛ ከዳኝነት ስራቸው እንዲባረሩ ከተደረገ በኋላ በምትካቸው ደግሞ የሞያ ብቃት የሌላቸውን ካድሬዎች በመመደብ የዳኝነትን ስራ ነጻነት የሚያጠፋ እርምጃ አሁን የመንግስት ስልጣን በያዘው ፓርቲ በመወሰዱ በሀገሪቱ ውስጥ ቀጥተኛ የሆነ ፖለቲካዊ ቁጥጥርና ተፅዕኖ የማይደረግበት የሕግ ተቋም የለም:: በዳኝነትና በዓቃቤ ሕግ ስራ የሚሰማሩት በአብዛኛው የገዥው ፓርቲ ካደሬዎች ናቸው:: እነዚህን የአንድ ፓርቲ ካድሬዎች ለማሰልጠን በሀገሪቱ ስም በሚገኝ ብድርና እርዳታ ሲቪል ሰርቪስ የሚል ተቋም የተደራጀ ሲሆን ተቋሙ ራሱ በገዥው ፓርቲ አመራር አባላት የሚመራና ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ፖለቲካዊ ቁጥጥር የሚደረግበት ነው:: እንደማንኛውም የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የአካዳሚ ነፃነት እንዲኖረው በሚያስችል አደረጃጀትና አሰራር መርህ የተቋቋመ ሳይሆን ፖለቲከኞችን በዳኝነትና በሌሎችም ስራዎች ለመመደብ የሚያስችል ዝግጅት የሚደረግበት የፖለቲከኞች ማሰልጠኛ ተቋም ነው ማለት ይቻላል::

በዚህ ተቋም የተዘጋጁ ካድሬዎች ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ የዳኝነትና የዓቃቤ ሕግ ኃላፊነት እየተሰጣቸው የዳኝነት መዋቅሩን እንዲቆጣጠሩት እየተደረገ ነው:: በዚህ መንገድ ፖለቲካና ዳኝነት ተደበላልቀው ቁጭ ብለዋል:: በዳኝነት የተመደቡ ካድሬዎች ለዚህ ደረጃ እንዲበቁ ያደረጋቸው የሞያ ብቃትና ችሎታ ሳይሆን አባል የሆኑበት ፖለቲካ ፓርቲ እንደመሆኑ ተጠሪነታቸውና ተጠ ያቂነታቸው ለፓርቲያቸው ነው:: በፍርድ አሰጣጥ ጊዜ የሚጠነቀቁት ሕጉን በትክክል እየተረጎሙ

ፍትህ እንዲረጋገጥ ለማድረግ ሳይሆን ለዚህ ያዘጋጃቸው ፓርቲና መንግስት በዳኝነት ስም ሕጋዊ ሽፋን እንዲያገኝ ለማድረግ ነው። ብይንና ዳኝነት ለመስጠት ሲነሱ ሕጉን በማገናዘብ ፋንታ የፓርቲያቸው መሪዎች ምን ዓይነት ፍርድና ዳኝነት እንደሚፈልጉ አጣርተው ለመወሰን ይጥራሉ። በአሁኑ ወቅት እየተሰራ ያለው ሕግን መሰረት ያደረገ ፍትህ የማረጋገጥ ጉዳይ ሳይሆን የፖለቲካ ውሳኔን በፍርድ ቤት ዳኞች ብይን የተደገፈ ማድረግና ሕጋዊ ሽፋን የመስጠት ጉዳይ ሆኗል።

ኢዴፓ አሁን በሀገሪቱ ወስጥ ያለው የፍትህ ተቋም ምንም ዓይነት ነፃነት እንደሌለው የሚያረጋግጡ በቂ ማስረጃዎች አሉት። በጠቅላላው ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለው የፍትህ መጓደል እንዳለ ሆኖ ኢዴፓ ራሱ የዚሁ ፍትህ አልባነት ዋነኛ ተጠቂ ነው። የኢዴፓ አባላት ባለተጨባጭ ማስረጃና ሕጋዊ ስርዓትን ባልተከተለ መንገድ ግድያ፣ እስራት፣ መገረፍና መሰደድ በተደጋጋሚ ጊዜ የደረሰባቸው ቢሆንም ይኸንን ሕገወጥ ጥፋት የሚያግድ ፖሊስ፣ ፍርድ ቤት፣ አቃቤ ሕግና ዳኛ ማግኘት አልተቻለም። ከሚሰሩበት መሰሪያ ቤት ካላአንዳች ጥፋት የኢዴፓ አባላት በገዥው ፓርቲ መመሪያ እየተባረሩ ሜዳ ላይ ሲጣሉ ይኸንን ግፍ የሚከላከል የፍትህ ተቋም አልተገኘም። በግብርና፣ በንግድ፣ በአገልግሎትና በሌላም መስክ የተሰማሩ የኢዴፓ አባላት በነፃነት ወጥቶ መግባት፣ ሰርቶ መኖርና እንደዜጋ መታየት ስላልቻሉ በየጊዜው ለፍትህ አካላት አቤቱታ ቢቀርብም ይኸንን ኢሰብአዊና ኢዴሞክራሲያዊ ድርጊት የሚያስቆም ፍትህ ማግኘት አልተቻለም። በተደጋጋሚ ጊዜ በፓርቲው አባላትና አካላት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል ብቻ ሳይሆን የፍትህ ተቋሙን ነፃነት ለመፈተሽ ጭምር ኢዴፓ በተጨባጭ ማስረጃ የተደገፉ ክሶችና አቤቱታዎችን ለፍትህ አካላት ቢያቀርብም ሚዛናዊ ፍርድ ማግኘት ቀርቶ ሰሚ ጆሮም አላገኘም።

በዚህና በሌሎችም ተደጋጋሚ ድርጊቶች የፍትህ ስርዓቱ ወንጀልን ለመከላከልና ወንጀለኞችን ለመቅጣት በሚያስችለው ነፃነት ተደራጅቶ እንደማይሰራ በተጨባጭ ተረጋግጧል። በፍትህ ስራ ከተሰማሩት ዳኞች፣ ዓቃቤ ሕጎችና ፖሊሶች መካከል ለሕጉና ለሞያው ስነምግባር በታማኝነት የቆሙ ግለሰቦች እንዳሉ በሚገባ የታወቀ ቢሆንም ተቋሙ ፖለቲካዊ ተፅዕኖና ቁጥጥር በሚደረግበት ሁኔታ ተደራጅቶ ባለመስራቱ የእነዚህ ሀቀኛ ሞያተኞች ጥረት ውጤት ሊያገኝ የሚችልበት እድል የመነመነ ነው። ነፃና ገለልተኛ የፍትህ ተቋም እስከሌለ ድረስ በግለሰቦች ቅንነትና ጥረት ብቻ ፍትህን ማረጋገጥ እንደማይቻል ከኢትዮጵያ ሁኔታ የተሻለ ማስረጃ ማግኘት ይከብዳል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣ ሌሎች የገዥው ፓርቲ አካላትና አመራር አባላት ዳኞች የሰጡትን ብይን በአደባባይ እያጥላሉ፣ የዳኞቹን ሰብዓዊ ክብር የሚነካና መልካም ስማቸውን የሚያጎድፍ ፕሮፓጋንዳ እየነዙ የዳኝነት ስራቸውን በነፃነት እንዳይሰሩና እንዲሸማቀቁ ያደርጓቸዋል። በሰጡት ብይን ደስተኞች በማይሆኑበት ጊዜ የሌለ ወንጀል እየለጠፉ ቅጣት፣ ዕገዳና ማባረር ይፈፅሙባቸዋል። ዳኞች ዐቃቤ ሕጎችና ፖሊሲች ለሞያቸውና ለሕሊናቸው ታማኝ ሆነው ከተገኙ የስርዓቱ ጠላት ተደርገው ይፈረጃሉ። እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች በወረንጦ እየተለቀሙ ከስራ ውጭ ይደረጉና ለአገዛዙ ፖለቲካ ታማኝ የሆኑ ሰዎች እንዲተኳቸው ይደረጋል። በዚህ መንገድ በመላ ሀገሪቱ ፍትህ አልባላት ከመንገሱም በላይ የዜጎች ደህንነትና ነፃነት ዋስትና በማጣቱ ከሕዝቡ ቀና መንፈስና ከፈጣሪ ጥበቃ በስተቀር ሌላ መተማመኛ የሕግ ስርዓት አለ ለማለት አይቻልም።

የፖሊስ፣ የማረሚያ ቤትና የደህንነት ተቋሙ ደግሞ ከዳኞችና አቃቤ ሕጎች በባሰ መንገድ የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ አጀንዳ ከማስፈፀም በስተቀር ሌላ ተልዕኮና ኃላፊነት እንዳይኖረው ተደርጎ የተቀየሰ ተቋም ነው። የገዥውን ፓርቲ ስልጣን በማስጠበቅና የዚህን ፓርቲ ፖሊሲዎች የማይደግፉ ድርጅቶችንና ግለሰቦችን በማፈን ስራ የተጠመደ ተቋም ነው። የዚህ ተቋም አመራር ሙሉ በሙሉ በሕወሓት/ኢህአዴግ ካድሬዎች እጅ የወደቀ ሲሆን በፖሊስና በደህንነት ስራ ከተሰማሩት ሰዎች መካከል አብዛኞቹ የሕወሓት ታጋዮች ናቸው። ይህ ተቋም ቀጥተኛ የሆነ ፖለቲካዊ ቁጥጥርና ተፅዕኖ የሚደረግበት በመሆኑ ነፃና ገለልተኛ በሆነ መንገድ የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ለማስከበር የሚሰራ ዴሞክራሲያዊ ተቋም አይደለም። ተጠሪነቱና ተጠያቂነቱ ለገዥው ፓርቲ በመሆኑ የፓርቲውን ስልጣን ለመጠበቅ ሲባል በሕዝብ ላይ እጅግ ጨካኝ የሆነ የአፈናና የግድያ ተግባር በተደጋጋሚ ጊዜ በመፈፀም ኃላፊነት የጎደለው መሆኑ በሚገባ ታይቷል። ወንጀልን በመከላከልና ወንጀለኛን በማሳደድ የዜጎችን ደህንነትና ሰላም በማረጋገጥ ፋንታ የአንድ ፓርቲ ተላላኪ ሆኖ እንዲያገለግል በመገደዱ ለዴሞክራሲ ስርዓት ምስረታ አስተዋፅኦ ለማድረግ የማይችል የአፈናና የሽብር መሳሪያ ሆኗል። የዚህ ተቋም መመሪያ በቅድሚያ ግደል ከዚያ በኋላ ጠይቅ የሚል አይነት ነው። በመሆኑም ሰላማዊና ሕጋዊ የመብት ጥያቄ ይዘው አደባባይ የወጡትን ሲቪሎች በጦር መሣሪያ ከመጨፍጨፍ አልፎ

*ዜጎችን ከመኖሪያ ቤታቸው፣ ከስራና መዝናኛ ቦታቸው እያፈሱ መሰወር፣ መግረፍና መግደል የዘወትር ተግባር ነው:: የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ሳይኖር ግለሰቦችን ማሰር፣ የግለሰቦችን ቤት መፈተሽ፣ የፖስታና የስልክ መልዕክቶቻቸውን መጥለፍ፣ በድብደባና በማሰቃየት ግለሰቦች ጥፋተኛ ነን ብለው እንዲያምኑ ማስገደድ፣ በወንጀል የተጠረጠሩ ሰዎችን ለመያዝ አላስፈላጊ ኃይል መጠቀምና የመሳሰለውን ሕገወጥ ድርጊት መፈፀም አሁን በስራ ላይ ባለው የፖሊስና የደህንነት ተቋም ውስጥ የተለመደ ነው::*

*ስለዚህ በሀገራችን የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲመሰረት ከተፈለገ በቅድሚያ የፍትህ ተቋማት አሁን ያጋጠማቸውን መዋቅራዊ ችግር በማስወገድ ከፖለቲካዊ ተፅዕኖና ቁጥጥር ነፃ ሆነው እንዲደራጁና እንዲሰሩ ያስፈልጋል:: በዳኝነት፣ በአቃቤ ሕግና በፖሊስ ተግባር የሚሰማሩ ሰዎች የግል ፖለቲካዊ እምነት የመያዝ መብት ቢኖራቸውም የአንድ ፓርቲ አባል ሆነው ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት ሁኔታ መወገድ ይኖርበታል:: የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆነው የተመዘገቡና የፖለቲካ ትግል ለማድረግ ወስነው ተሳትፎ የሚያደርጉ ግለሰቦች በዳኝነት፣ በአቃቤ ሕግና በፖሊስ ተግባር ተመድበው መስራት አይገባቸውም:: በእነዚህ ተቋሞች ለሚሰማሩ ካደሬዎች ማዘጋጃ የሆነው የሲቪል ሰርቪስ በገዥው ፓርቲ አመራር ስር መውደቁና ለዚህም ፓርቲ ተጠሪና ተጠያቂ መሆኑ ቀርቶ እንደሌሎች ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች በራሱ ቻርተር የሚተዳደር፣ አመራሩን በዴሞክራሲያዊ መንገድ መርጦ የሚመድብና ከፓለቲካ ወገንተኝነት ተላቆ ራሱን በቻለ መንገድ የሚሰራ ነፃ የአካዳሚክ ተቋም ሆኖ መስራት አለበት:: የሲቪል ሰርቪስ ተቋም በሀገር ስም ከፍተኛ የሕዝብ ሀብት የሚፈስበት መሆኑ እየታወቀ የአንድ ፓርቲ ፖለቲከኞች ለዳኝነትና ለሌሎች ኃላፊነቶች የሚዘጋጁበት ማሰልጠኛ እንዲሆን መደረጉ በምንም ዓይነት መንገድ ተቀባይነት የለውም:: ይህ ተቋም የሕዝብ ተቋም እንዲሆን ከተፈለገ ወደተቋሙ የሚገቡት ፖለቲከኞች ብቻ መሆናቸው ቀርቶ እንደማንኛውም ከፍተኛ የትምህርት ተቋም የኮሌጅና ዩኒቨርስቲ መግቢያ መስፈርቶችን ለሚያሟሉ ዜጎች ሁሉ ክፍት መሆን ይኖርበታል:: የዳኞችና አቃቤ ሕጎች አመራረጥና ሹመት የሞያ ብቃትን፣ ሥነ ምግባርና ፈቃደኝነትን መሰረት ባደረገ ግልፅ መስፈርት መፈፀም ይገባዋል:: ስልጠና ለብ ለብ መሆኑ ቀርቶ ጥልቀት ያለው፣ ለሞያ ብቁ የሚያደርግና በጥሩ ስነምግባር የሚያንጽ እንዲሆን በተገቢው ጥንቃቄና ዝግጅት መፈፀም ይኖርበታል:: የዳኝነትና አቃቤ ሕግ ስራ የተከበረ ሞያ እንደመሆኑ ለካድሬዎች፣ ለታማኝ ፖለቲከኞች ውለታ መክፈያ እየተደረገ የሚረክስበት አሰራር ጨርሶ መቅረት ይገባዋል::*

*የሀገሪቱ የፍትህ ተቋም የመንግስት ስልጣን የያዘ ፓርቲ አጀንዳ ማስፈፀሚያ መሣሪያ ከሆነበት አሳፋሪ ሁኔታ ወጥቶ በገለልተኝነትና ከማንኛውም ተፅዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ እንዲደራጅና እንዲሰራ መደረግ አለበት:: የዳኞች አመዳደብ የፖለቲካ ዓላማን እንደሚያሳኩ በሚታመንባቸው ጀማሪዎች ላይ ማተኮሩ ቀርቶ በዚህ መስክ ለመመደብ በሚያበቁ ግልፅ መስፈርቶች ብቻ እንዲመሰረትና ጀማሪዎች ከፍተኛ የሞያ ብቃትና የረጅም ጊዜ የስራ ልምድ ካላቸው ጋር በረዳትነት እየተመደቡ ቀስ በቀስ የተሟላ ብቃት እንዲያገኙ በሚያስችል መንገድ መፈፀም ይገባዋል:: ወደሞያው የሚገቡ አዲስ ዳኞችና አቃቤ ሕጎች በአንዴ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዲይዙ ከመደረጋቸው በፊት ከዝቅተኛ ደረጃ ጀምረው ልምድ እያገኙና ብቃታቸውን እያዳበሩ ወደ ከፍተኛው ደረጃ መሸጋገር ይኖርባቸዋል:: በዳኝነትና በአቃቤ ሕግ የተሰማሩ ሰዎች በተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞች እንዳይዘናጉና ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ከሚያስችላቸው የሞያ ስልጠናና ስነምግባር በተጨማሪ ከኃላፊነታቸው ክብደት ጋር የሚመጣጠንና እንዲሁም ለመተዳደሪያቸው የሚበቃ የማበረታቻ ክፍያና ደመወዝ ሊኖራቸው ይገባል:: የዳኞችን የዲስፐሊን ጉድለት ለማስወገድ፣ የልምድ ልውውጥ ለማድረግና የስራ ተነሳሽነትን ለማጠናከር የሚያግዝ ከመንግስት ፖለቲካዊ ቁጥጥር የፀዳ የሞያ ማህበር በነፃነት እንዲያቋቁሙ መደረግ ይኖርበታል:: ዳኞች በሰጡት ዳኝነት የመንግስትን ፍላጎት አልጠበቁም ተብለው ከስራቸው የሚታገዱበት፣ የሚቀጡበትና የሚባረሩበት ሁኔታ ፈጽሞ መወገድ አለበት:: የዳኝነት ስራቸውን በሙሉ ነፃነት ሊያከናውኑ ይገባል:: ከሕግ በስተቀር በሌላ ማንኛውም ኃይል እየተመሩ ክስ እንዲመሰርቱና ብይን እንዲሰጡ ተጽዕኖም ሆነ ሌላ አስገዳጅ ድርጊት ሊፈፀምባቸው አይገባም:: ጥፋት ፈጽመው ሲገኙ በሕግ ግልፅ ሆኖ ከተደነገገው ስርዓት ውጭ ሊቀጡ አይገባም:: የአገልግሎት እድሜ ዘመናቸው ካልደረሰ፣ በራሳቸው ፍላጎት ጥያቄ ካላቀረቡና በሕግ የሚያስጠይቅ ወንጀል መስራታቸው በፍርድ ቤት ካልተረጋገጠ በስተቀር ከስራቸው ሊሰናበቱ አይገባም::*

የፖሊስና የደህንነት ተቋሙ የሕዝቡን ሰላምና ፀጥታ የማረጋገጥ ተልዕኮ ያለው ሆኖ እንዲደራጅና ፋይዳ ያለው የወንጀል መከላከል ሚና እንዲጫወት ከተፈለገ ከአንድ ፓርቲ ሙሉ ቁጥጥርና ተጽዕኖ ነፃ ሆኖ መደራጀት ይኖርበታል፡፡ የፖሊስና የደህንነት ተቋም መሪዎችና አባላት ተጠሪነትና ተጠ ያቂነት ለአንድ የመንግስት ስልጣን ለጨበጠ ማዕከላዊ መንግስት መሆኑ ቀርቶ ለሕዝብ፣ ለተለያዩ ክልል መንግስታትና ለአካባቢ መንግስታት እንዲሁም ስራውን በተጨባጭ ለሚያከናዉኑት የፖሊስና የደህንነት ከፍተኛ ባለሞያዎች እንዲሆን ተደርጎ መከፋፈል አለበት፡፡

ለሕዝብ ተጠሪነትና ተጠያቂነት ይኑራቸው ሲባል የፖሊስ ዋነኛ ስራ የሕዝቡን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ፣ ወንጀልን መከላከልና ጥፋተኞችን ወደሕግ ማቅረብ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት በቀበሌና በወረዳ የሚመራ የፖሊስ ኃይል ከሕዝብ በተመረጡ ኮሚቴዎች መመራት ይገባዋል ማለት ነው፡፡ ለምሳሌ በአንድ ከተማ ውስጥ የሚደራጅ የፖሊስ ኃይል ከከተማው ምክር ቤትና ከሌሎችም የሕዝብ ተቋሞች የተመረጡ አባላት ያለበት የፖሊስ ጉዳይ ኮሚቴ አቋቁሞ እንዲሰራ ማድረግ ይቻላል፡፡ ይህ ዓይነቱ አደረጃጀት የፖሊስን የዕለት ከዕለት ስራ እንዲመራና እንዲያስተባብር በየደረጃው ባሉት የሕዝብ ምክር ቤቶች ለሚሾመው ኮሚሽነር ያላቸውን ተጠሪነትና ተጠያቂነት የሚያጠፉ ሳይሆን ያንኑ የሚደግፍና የሚያጠናክር ነው፡፡

በክልልና በፌዴራል ደረጃ የሚቋቋም የፖሊስ ኃይል ደግሞ ተጠሪነቱና ተጠያቂነቱ በየደረጃው ለሚገኘው የሕግ አውጭው ምክር ቤት ሆኖ የዚህ ተቋም መሪዎችም በዚሁ ምክር ቤት የሚሾሙበት ሁኔታ መኖር አለበት፡፡ የፖሊስ መሪዎችና አባላት ከፖለቲካ እንቅስቃሴ ውጭ መሆናቸውንና የማንኛውም ፓርቲ አባል አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል፡፡ ለፖሊስ አባልነት የሚመለመሉ ዜጎች ከፍተኛ ስነምግባር ያላቸው እንዲሁም ለሞያው ፍላጎትና ፈቃደኝነት ያላቸው ብቻ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡ ማንኛውም የፖሊስ አባል ወደስራው ከመግባቱ በፊት በቂና ጥልቀት ያለው የሞያ ስልጠና ሊሰጠው ይገባል፡፡ የፖሊስ አባላት ስልጠና፣ እድገት፣ ዝውውር፣ ሹመት፣ ሽልማትና ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች የሚገኙት በመላው አባላት ንቁ ተሳትፎ ግልጽ ሆኖ በተዘጋጀ ደንብና ስርዓት መሰረት መሆን አለበት፡፡ የዲስፕሊን ጥፋት ሲፈፅሙ  የሚቀጡበት ግልጽ አሰራርና ሕጋዊ ስርዓት መኖር ይገባዋል፡፡ በፖሊስ ሞያ ለተሰማሩ ሰዎች ከስራቸው ክብደት ጋር የሚመጣጠንና ለኑሯቸው በቂ የሆነ የደመወዝ ክፍያ፣ አበልና ልዩ ልዩ አገልግሎት እንዲያገኙ መደረግ አለበት፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች በሀገሪቱ ውስጥ የነገሰውን ፍትህ አልባነት ለማስወገድ፣ ከጊዜ ወደጊዜ እየተስፋፋ የመጣውን ወንጀል ለመከላከል፣ ጥፋተኞችን በሕግ ለመቅጣት፣ የዜጎችን ሰላምና ደህንነት በአስተማመኝ ሁኔታ ለመጠበቅ፣ ሰብዓዊ መብታቸውንና ነጻነታቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል ዴሞክራሲያዊ የፍትህ ተቋም ማደራጀት ይቻላል፡፡ በመጨረሻ መነሳት የሚገባው ነጥብ የዜጎችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብት እያፈነ የመንግስትን ስልጣን የሚጠብቅና ለዚህም ተቋም ፍላጎት ማስፈፀሚያ መሳሪያ ብቻ ሆኖ የሚያገለግል የስለላ ተቋም በሀገሪቱ ውስጥ ሊኖር የማይገባው መሆኑ ነው፡፡ በየትኛውም የዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ የሚመሰረት የደህንነት ተቋም ዋነኛ ኃላፊነትና ተግባር የዜጎችንና የሀገርን ሰላምና ፀጥታ የሚያናጉ ሁኔታዎች ተፈጥረው ከቁጥጥር ውጭ እንዳይሆኑ መከታተልና ውሳኔ ለሚሰጡ አካላት አስተማማኝ መረጃ በፍጥነትና በጥራት ማቅረብ ነው፡፡ ይህ ለሕዝብና ለሀገር ሰላምና ፀጥታ ዋስትና ሆኖ መገኘት የሚገባው ተቋም የአፈና መሣሪያና ስልጣን የያዘ ፓርቲ አጀንዳ ማስፈፀሚያ ሆኖ ሕዝብንና ሀገርን በሚጎዳ ጨካኝ ተግባር ከተሰማራ እንዲኖር የሚያስፈልግበት ምንም ዓይነት ምክንያት የለም፡፡ አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ የተደራጀው የስለላ ተቋም ለዜጎች ሰላምና ደህንነት ዋስትና መሆኑ ቀርቶ ትልቅ ስጋት ሆኗል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ረሃብና ኤድስ ከደቀኑት የደህንነትና የሕይወት ስጋት ባላነሰ ደረጃ እንደ አንድ ትልቅ አደጋ የሚታየው አገዛዙ ያደራጀውና የሚመራው የስለላ ተቋም ነው፡፡ የዜጎች ሕይወት ለሰላዮች ነፃ እርምጃ የተጋለጠ ነው፡፡ ማንም ዜጋ ከስለላ ለመጠበቅና ከሰላዮች ነፃ እርምጃ ለማምለጥ ምንም ዓይነት መተማመኛ መንገድ የለውም፡፡

የዚህ አገዛዝ ሰላዮች በግል ጥላቻና ቂም በቀል እንኳ ተነስተው የፈለጉትን ነፃ እርምጃ ለመውሰድ እንደሚችሉ በተጨባጭ የሚታይ ነው፡፡ በእነዚህ የሕግና የሞራል ተጠያቂነት በሌላቸው ሰላዮች እየታፈነ ወህኒ የወረደው፣ የተገረፈው፣ የተገደለውና የደረሰበት የማይታወቀው ቁጥር እጅግ ብዙ ነው፡፡ አሁን በስራ ላይ ያለው የስለላ ተቋም የዜጎች ስጋት ከመሆኑና በአፈና መሳሪያነት ከማገልገል በስተቀር ሕዝቡንና ሀገሪቱን ግልጽ ከሆነ የውጭ ወረራና ጥቃት ወይንም ከአሸባሪዎች ድንገተኛ ጥፋት ለማዳን ብዙም ሲጥር አይታይም፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ትልቅ ኃላፊነት ለመጣት የሚያስችለው

አደረጃጀት፣ ስልጠናና ዝግጅት ያለው ተቋም እንዳልሆነም የታወቀ ነው። በመሰረቱ ከፍተኛ የሞያ ስልጠና፣ ዘመናዊ ቴክኒዎሎጂ፣ የረቀቀ አደረጃጀትና አሰራር የሚጠይቅ የደህንነት ተቋም በጠመንጃ አንጋቾችና በፖለቲካ ካድሬዎች ሙሉ ቁጥጥር ስር ሆኖ ለሕዝብና ለሀገር የሚጠቅም ስራ ይሰራል ተብሎ አይጠበቅም። ስለዚህ ለዜጎች ሕይወትና ለሀገር ሕልውና አጅግ የከፋ ስጋትና አደጋ ሆኖ የተደራጀውና የሚሰራው የስለላ ተቋም ሙሉ በሙሉ መወገድ ይኖርበታል ብሎ ኢዴፓ ያምናል። በዚህ ምትክ የመንግስት ስልጣን የያዘ ፓርቲ ተላላኪ የማይሆን ነገር ግን ከሁሉም በፊት ለዜጎች ሰላምና ደህንነት መጠበቅ በብቃት የተሰለፈ፣ ለሀገር ሕልውና ዋስትና የሚሆን፣ በሚገባ በሰለጠኑና ከፍተኛ የሞያ ብቃት እንዲሁም አስተማመኝ ስነምግባር ባላቸው ሰዎች የሚመራ፣ በረቀቀ ቴክኖዎሎጂ የሚታገዝ፣ ዘመናዊ አደረጃጀት ያለው ፈጣንና ወቅታዊ መረጃዎችን ለማግኘትና ለመተንተን የሚችል የሀገርና የሕዝብ ደህንነት ተቋም መደራጀት አለበት። ይህ ተቋም መንግስት በወረደና በወጣ ቁጥር እየፈረሰ ከዜሮ የሚጀምር እንዳይሆን ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነፃ ሆኖ መደራጀትና መስራት ይኖርበታል። የማንኛውም ዴሞክራሲያዊ ሀገር የደህንነት ተቋም ስልጣን ለወጣ ፓርቲ አጀንዳ ማስፈፀሚያ መሳሪያ ሆኖ እንዲያገለግል አይደረግም። ፓርቲዎች ወደመንግስት ስልጣን በወጡና ከዚህ ስልጣን በወረዱ ቁጥር አዲስ ተቋም የሚመሰርቱበት አሰራር የለም። የአንድ ሀገር የደህንነት ተቋም ከአንድ ፓርቲ ዓላማና ጥቅም በላይ ለሆነ የሕዝብና የሀገር ጥቅም እንዲሰራ ሆኖ መደራጀት ይገባዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲኖር የምንፈልገውም እንዲህ ዓይነት የሕዝብና የሀገር ጥቅም ዋስትና የሆነ የደህንነት ተቋም ብቻ ነው።

## 3.2.3 **ሕግ አስፈጻሚ አካል**

የመንግስት ሕግ አስፈጻሚ አካል ኃላፊነት በሁለት የተለያዩ ክፍሎች አማካይነት የሚከናወን ሲሆን አንደኛው ክፍል በፖለቲከኞች የሚፈፀመውን ይመለከታል። ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በቋሚነት ተቀጥረው በሚሰሩ ኃላፊዎችና ሰራተኞች የሚከናወነውን ይመለከታል።

በቅድሚያ በፖለቲከኞች የሚከናወነውን ማየት ይጠቅማል። ፓርላሜንታሪ የሆነ የመንግስት ስርዓት የመሰረቱ ዴሞክራሲያዊ ሀገሮች የመንግስት አስፈፃሚው አካል በሕዝብ ምርጫ ለተቋቋመው ፓርላማ ተጠሪ የሚሆንበትን አሰራር ይከተላሉ። የዚህም መነሻ አስፈጻሚው አካል ስልጣኑን ስራ ላይ በሚያውልበት ጊዜ በሕዝብ የተወከለውን ፓርላማ አመለካከት መከተል ይኖርበታል፣ ወይንም የፓርላማውን ሀሳብ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ስልጣኑን በዘፈቀደ አሰራር ሊጠቀምበት አይገባም ከሚለው መሰረታዊ ግንዛቤ በመነጨ ነው። በብዙዎቹ የፓርላሜንታሪ መንግስት ስርዓት በገነቡ ሀገሮች ሕግ አውጭውን (ፓርላማውን) ለማቋቋም የሚካሄደው ምርጫ የመንግስታቱን ፖለቲካዊ ይዘትና ባህሪይ ይወስነዋል። በአንዳንዶቹ ሀገሮች ያለው የምርጫ ስርዓት አንድ ፓርቲ አብዛኛውን የፓርላማ መቀመጫ በግልፅ እንዲቆጣጠር ስለሚረዳ የሚመሰረተው የመንግስት አስፈፃሚ አካል ይኸንኑ የአንድ ፓርቲ የበላይነት የሚያንፀባርቅ ይሆናል። በሌሎቹ ሀገሮች ያለው የምርጫ ስርዓት ደግሞ ከአንድ በላይ የሆኑ ፓርቲዎች ተመጣጣኝ ውክልና የሚያገኙበት ስለሚሆን በፓርላማ መቀመጫ አንደኛው ፓርቲ ግልጽ የሆነ የበላይነት እንዲይዝ አያስችልም። ስለዚህ በዚህ ዓይነቱ ፓርላማ አማካይነት የሚመሰረተው የመንግስት አስፈጻሚ አካል የፓርላማውን ጥንቅር የሚያንፀባርቅ ይሆናል። ዋናው ነገር በየትኛውም ፓርላሜንታሪ ስርዓት የሚመሰረት የመንግስት አስፈጻሚ አካል በስልጣን ላይ ለመቆየት የፓርላማውን ትምምን ወይም ድጋፍ ማግኘት የሚገባው መሆኑ ነው። በብዙዎቹ ፓርላሜንታሪ ስርዓቶች የአስፈጻሚው አካል አባላት ወይም ሚኒስትሮች የፓርላማ መቀመጫ ያላቸው ስለሚሆኑ ለፓርላማው ያላቸው ተጠሪነት ቀጥተኛ ነው።

በፓርላማ ውስጥ ግልጽ የሆነ የአንድ ፓርቲ የበላይነት በሚኖርበት ጊዜ አስፈጻሚው አካል ገናና ሆኖ የመውጣት እድል ያገኛል። በአንድ ብቸኛ ፓርቲ ግልጽ የሆነ የፓርላማ መቀመጫ ብልጫ በማይኖረው ጊዜ የሕግ አውጭው አካል ሰፊ መሰረት ያለው፣ ነገር ግን ከተለያዩ ፓርቲ ተወካዮች በተውጣጡ ተወካዮች ጥምረት የሚመሰረት ስለሚሆን አስፈጻሚ አካሉም ገናና ሆኖ ለመውጣት አይችልም። በመሆኑም ከፓርላማው ጋር የሚኖረው ግንኙነት ሀቀኛ በሆነ የመስጠትና የመቀበል አሰራር ላይ የተመሰረተ ይሆናል። ይኸም ማለት ብዙዎቹ ጉዳዮች የሚወሰኑት በውይይት፣ በድርድርና በሚደረስበት የጋራ ስምምነት ነው ማለት ነው።

በፓርላሜንታሪ የመንግስት ሥርዓት ውስጥ የአስፈጻሚው አካል የሚይዘው ጠቅላይ ሚኒስትሩን፣ የካቢኔ አባላቱንና ሌሎች ሚኒስትሮችን ነው። በዚህ አይነቱ ስርዓት ዋነኛው የመንግስት አመራር የሚከናወነው በአስፈጻሚው አካል ሲሆን ይኸም በጠቅላይ ሚኒስትሩ መሪነት በሚቋቋም ካቢኔ ተግባራዊ ይሆናል። ጠቅላይ ሚኒስትሩ በመንግስት አመራር ውስጥ ቀዳሚውን የኃላፊነት ስፍራ ስለሚይዝ የሀገር መሪ ተደርጎ ነው የሚታየው። የፖለቲካ ስልጣን በአስፈጻሚው የመንግስት አካል ከሚያዝበት ሁኔታ እስካሁን ያሉትን ሞዴሎች በሁለት ሰፊ ምድቦች ከፍሎ ማየት ይቻላል። አንደኛው ምደብ የመንግስት አመራር በፕሬዚዳንቱ እጅ የሚያዝበትን ሁኔታና ፕሬዚዳንቱ የአስፈጻሚው አካል ዋነኛው የስልጣን ምንጭ የሆነበትን የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው ምድብ ደግሞ የአስፈፃሚው አካል ጠቅላይ ሚኒስትሩንና ሌሎች ሚኒስትሮችን ባካተተ መንገድ የመንግስት አመራር ስራ የሚካሂድበትን የሚመለከት ነው።

በአብዛኛው የፓርላሜንታሪ የመንግስት ስርዓት ባለባቸው ሀገሮች የሚኖረው በሁለተኛው ምድብ የተገለፀው አይነት የአስፈጻሚ አካል ነው። ይህ አካል ብዙውን ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመረጡ ሚኒስትሮችና ሌሎች ባለሥልጣኖች በአባልነት የሚገኙበትን ካቢኔ አቋቁሞ ስራውን ይሰራል። የካቢኔ መንግስት አመራር እንዲኖር አስፈላጊ የሚሆነው የፖለቲካ ስልጣን በጠቅላይ ሚኒስትሩና በሌሎች የመንግስት አካላት መካከል እንዲከፋፈል ለማድረግ ነው። በሌላ አገላለጽ ዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች በጠቅላይ ሚኒስትሩ ብቻ ሳይሆን በሁሉም የመንግስት አመራር አባላት ውይይት ተደርጎባቸው ይወሰናሉ ማለት ነው። በእርግጥ ፖሊሲ በማመንጨትም ሆነ በዋና ዋና የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ በመወሰን ረገድ የካቢኔ አባላትን ተሳትፎ ለማስፋትም ሆነ ለማጥበብ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የአሰራር ዘይቤና ባህርይ የራሱን ተፅዕኖ ማሳደሩ አይቀርም። ጠቅላይ ሚኒስትሮች በካቢኔ ባልደረቦቻቸው ተፅዕኖ ስር እንወድቃለን ብለው ስለሚሰጉ በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ከካቢኔ አባላት ይልቅ ከቅርብ አማካሪዎቻቸው ጋር እየመከሩ መወሰንን ይመርጣሉ። በዚህም የተነሳ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ለራሳቸው የምክር አገልግሎት የሚያቋቁሙት ቢሮክራሲ እየገዘፈና ለቁጥጥር አስቸጋሪ እየሆነ የመጣበት አጋጣሚ ጥቂት አይደለም። በመሰረቱ ጠቅላይ ሚኒስትሮች ለሚፈጽሙት የመሪነት ተግባር ምክር የሚያገኙበት ቢሮክራሲ ማቋቋማቸው ጨርሶ የሚወገዝ ነገር አይደለም። የጠቅላይ ሚኒስትር ስልጣን ለተወሰነ ጊዜ ብቻ የሚቆይ እንደመሆኑ በሥልጣን ቆይታ ጊዜው ተገቢ ስራ መስራት እንዲችል ውስብስብና ቴክኒካዊ ባህርይ ያላቸውን የፖሊሲ ሁኔታዎች አስመልክቶ ዝርዝር እውቀት ሊኖረው ይገባል። የመንግስትን አስፈጻሚ አካል ለመቆጣጠርና ለመምራት የሚያስችል ብቃት እንዲኖረው ያስፈልጋል።

ይሁን እንጂ ከዚሁ ጋር የተያያዙ ችግሮችም እንደሚኖሩ የታወቀ ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪዎች ለኃላፊነቱ ብቃት እንዲኖረው የሚሰጡት ድጋፍ ቀላል ባይሆንም ብዛታቸው የተመጠነ ካልሆነ ስራውን ለመቆጣር ችግር ይፈጠራል። አንዳንድ ጊዜ አማካሪዎች የሚያከናውኑት ተግባር በካቢኔ አባላትና በሌሎች የመንግስት አስፈጻሚ አመራር አባላት የሚንቀሳቀሱትን ስራዎች የሚተካበት ሁኔታ ስለሚያጋጥም የካቢኔ አባላቱንና የሌሎችን አመራር አባላት ተግባር ጠቃሚነት ያጠፋዋል። እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ሲፈጠር መሪ ፖለቲከኞች ሕዝብ ባልመረጣቸው አማካሪዎች ወደጎን እንደተገፉ ስለሚሰማቸው የመንግስትን መረጋጋት የሚጎዳ ውጤት ሊያስከትል ይችላል። እነዚህን የመሳሰሉ የአሰራር ችግሮች ቢኖሩም በፓርላሜንታሪ የመንግስት ስርዓት የካቢኔ አሰራር አሁንም ጥቅም እንዳለው ይታመናል።

የጠቅላይ ሚኒሰትሩንም ሆነ የካቢኔ አባላትን ስልጣን የሚወስኑና ሚናቸውን የሚገድቡ በርካታ ሁኔታዎች በመኖራቸው የአስፈፃሚው አካል ስራ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነው። ለምሳሌ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በፓርላማው ውስጥ አብዛኛውን መቀመጫ የያዘው ፓርቲ መሪ ቢሆንም በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ የሆነ የመቆጣጠር ችሎታ የሚገኘው ግልጽ የሆነ የፓርላማ መቀመጫ ብልጫ ካለው ብቻ ነው። በፓርላማ ውስጥ ያለው ብልጫ አነስተኛ ከሆነ ወይንም ምንም አይነት ብልጫ ከሌለው በመደበኛ ድምጽ አሰጣጥ ውሳኔዎች እንዲወሰኑለት ለማድረግ ያለው እድል ከሌሎች ፓርቲዎች በመጡ የፓርላማ አባላት ትብብር ላይ የተንጠለጠለ ነው። እንዲህ አይነት ሁኔታ ሲኖር በሌሎች ፓርቲዎች የፓርላማ አባላት ለሚቀርቡ ጥያቄዎች በጎ ፈቃድ ማሳየት ይኖርበታል። ምክንያቱም የአስፈፃሚው አካል ሕልውና የሚቀጥለው የእነዚህ ድጋፍ ሲገኝ በመሆኑ ነው። ሌላው ከሕዝቡ የሚገኝ አስተያየት በጠቅላይ ሚኒሰትሩና በካቢኔ አባላት ሚና ላይ እንደዚሁ የራሱ ተፅዕኖ አለው።

የሕዝብ አስተያየት መለኪያ ውጤቶች የአንድን መንግስት አስፈጻሚ አካል ተቀባይነት ማግኘትና ማጣት የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

በፓርላማ አባላት ማሟያ ምርጫ ወይም በአካባቢ መንግስታት ምርጫ ጊዜ የሚታየው የሕዝብ ድምጽ መጨመር ወይም መቀነስ እንደዚሁ ሥልጣን ላይ ያለውን መንግስት አስፈጻሚ አካል ድጋፍ መኖርና አለመኖር ሊያሳይ ይችላል፡፡ እነዚህንና ሌሎች የአስተያየት መለኪያ ዘዴዎችን እየተጠቀሙ ብዙዎቹ የዴሞክራሲ ሀገሮች ጠቅላይ ሚኒስትሮች የፖሊሲ ለውጥ ወይም የሰው ለውጥ ያደርጋሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ ቀጥተኛ በሆነ መንገድ ሳይሆን በተዘዋዋሪ መንገድ ለሕዝብ አስተያየት መልስ ለመስጠት ይሞክራሉ፡፡ የፖሊሲም ይሁን የሰው ለውጥ በማድረግ ፋንታ የአሰራርና የአፈጻጸም ለውጥ በማድረግ ወይም የሕዝቡን አመለካከት ለማስቀየር በሚያስችል ዘዴ የተቀነባበሩ የሚዲያ እንቅስቃሴዎችን በማካሄድ ያጡትን ድጋፍ ለማግኘት ይሞክራል፡፡

ሌላው ችግር ጠቅላይ ሚኒስትሩም ይሁን የካቢኔ አባላት ለተወሰነ ጊዜ ስልጣን ላይ የሚቆዩ በመሆናቸው አላማቸውን ለማስፈፀም የነደፉትን ፖሊሲና የአፈጻጸም መርሀ ግብር በስራ ላይ ሳያውሉት የምርጫ ጊዜ የሚደርስ መሆኑ ነው፡፡ የዚህ አይነቱ የጊዜ እጥረት አስፈጻሚው አካል በጋራ በሚሰራቸው ስራዎች ለይ ተፅዕኖ አለው፡፡ አብዛኞቹ የካቢኔ አባላት የተመደቡበትን ሚኒስቴር መ/ቤት ወይም የመንግስት ተቋም ስራ ማንቀሳቀስ እንደዋናው ኃላፊነታቸው አድርገው ስለሚወስዱት በፓርላማም ይሁን በካቢኔ ውስጥ ከፍተኛ ተሳትፎ ለማድረግ ይቸገራሉ፡፡ የሚመሩትን መስሪያ ቤት ፍላጎት ለማጥናትና ለማማከር ሰፊ ጊዜ መመደብ ስላለባቸው በሌሎች ጉዳዮች በቂ ተሳትፎ ለማድረግ አይችሉም፡፡ ችግሩ በዚህ ብቻ የተወሰነም አይደለም፡፡ ለተወሰኑ (4 ወይም 5) ዓመታት በስልጣን ላይ የሚቆይ የመንግስት አስፈጻሚ አካል ልዩ ሙያ (ችሎታ) የሚጠይቅ ውስብስብና አስቸጋሪ ተግባር እንዲያከናውን የሚጠበቅበት እንደመሆኑ በሳምንት አንድ ጊዜ በሚካሄድ የካቢኔ ስብሰባ ብቻ የጋራ ውሳኔ በሚጠይቁ ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ እየወሰነ ሊዘልቀው አይችልም፡፡ ከመደበኛው ስራቸውና የካቢኔ ስብሰባቸው በተጨማሪ የአማካሪዎችንና የካቢኔ ኮሚቴዎችን ስራ መምራትና ማስተባበር ያስፈልጋል፡፡ እነዚህና የመሳሰሉ ተፅዕኖዎችን እየተቋቋሙ የሚከናወን ስራ በመሆኑ የመንግስት አስፈጻሚ አካል እጅግ ከፍተኛ ብቃትና ልምድ ባላቸው ሰዎች የሚካሄዱ እንጂ የፖለቲካ ስልጣን ውክልና በማግኘት ብቻ ሊወጡት እንደሚችሉት ቀላል ነገር ተደርጎ የሚታይ አይደለም፡፡

በየትኛውም ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ የሚገኙ የመንግስት አስፈጻሚ አካላት የያዙትን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣት ትልቁ መተማመኛቸው ከሞላ ጎደል የዜጎችን ፈቃድና ምርጫ መሰረት ያደረገ ሕገመንግስታዊ ሥርዓት በየሀገራቸው መኖሩ ነው፡፡ በዚህ ዓይነቱ ስርዓት ውስጥ ሕዝቡ የመንግስትን ስራ በብዙ መንገድ ያግዛል፡፡ በመንግስት ፖሊሲዎች ቀረጻ ሂደት ንቁ ተሳትፎ ያደርጋል፡፡ አፈጻጸማቸውንም በቀጥታና በተወካዮቹ አማካይነት ይገመግማል፡፡ ይቆጣጠራል፡፡ ጉደለቶችን በግልፅ አውጥቶ ይተቻል፣ የመፍትሔ አማራጮችንም ያቀርባል፡፡ ሁሉም አቅሙ በሚያቅደው መጠን የመንግስትን ስራ እየተከታተለ ለማረምና ጥቅሙን የሚያስከብር ጠንካራ የመንግስት አገልግሎት በየመስኩ እንዲኖር ተግቶ ይንቀሳቀሳል፡፡ ይኽንን እንዲያደርግ የሚያስችል ሕጋዊና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በመኖሩ ሕዝቡ የመንግስትን ስራ ለመቆጣጠርና ለማረም ያለውን መብት ሁሉ ከመጠቀም አይቦዝንም፡፡ ጥቅሜን ያስከብርልኛል ብሎ በራሱ ፈቃድና ነጻ ውሳኔ በምርጫ የመሰረተው መንግስት ጥቅሙን በሚያጓድለበት ጊዜ አሁንም ከሥልጣን እንዲወርድ በድምጹ መወሰን ይችላል፡፡ መንግስትም በዚሁ ዴሞክራሲ ማእቀፍ ውስጥ ሆኖ መስራት እንዳለበት ስለሚያምን ኃላፊነቱን በትጋትና በታማኝነት ለመወጣት ብርቱ ጥረት ያደርጋል፡፡ የሕዝቡን ፍላጎትና ጥቅም እስካሟላ ድረስ በስልጣን ላይ እንደሚቆይና ይኽንን ማሟላት በተሳነው ጊዜ ስልጣኑን ለባለቤቱ እንደሚያስረክብ ጠንቅቆ ስለሚረዳ ለሕዝቡ ጥያቄዎች ትኩረት እየሰጠ ይሰራል፡፡ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ የተቋቋመ መንግስት የሕዝቡን አስተያየቶችና ትችቶች በመጥፎ አይመለከታቸውም፡፡ የጉድለቶቹ ማረሚያና ጥንካሬዎቹ ምንጭ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል እንጂ ወደጎን አይገፋቸውም፡፡ ሕዝብና መንግስት ሆድና ጀርባ ሆነው ሳይሆን አንድ አካልና አንድ አምሳል ሆነው ይሰራሉ፡፡

የሥልጣን ክፍፍልና የእርስ በርስ ቁጥጥር የሌለበት አገዛዝ በኢትዮጵያ ውስጥ መንገሱን ለማስረዳት የሚጠቅሙ ጉዳዮችን በዝርዝር ከማቅረብ በፊት በአስፈፃሚው አካል ውስጥ ብቻ የሚታየውን የተዛባ የካቢኔ አባላት ድልድል ማየት ይጠቅማል፡፡ አሁን ስልጣን የያዘው ድርጅት ለስሙ አራት ቡድኖች

የመሰረቱት ግንባር እንደሆነ ይገለጻል። እነዚህም ሕዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ (ሕወሃት)፣ ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅቃቄ (ብአዴን)፣ ኦሮሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ድርጅትና (ኦህዴድ) የደቡብ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ደህዴግ) ናቸው። እነዚህ ድርጅቶች እንወክለዋለን የሚሉት ሕዝብ ቁጥር ሲታይ እንደቅደም ተከተላቸው ኦሮሞ፣ አማራ፣ ደቡብ ሕዝቦችና ትግራይ ከ1ኛ እስከ 4ኛ ደረጃ ያለውን ስፍራ ይይዛሉ። በአሁኑ የመንግስት አስፈጻሚ አካል ውስጥ ያለው የሥልጣን ድልድል ሲታይ እያንዳንዱ ድርጅት እወክለዋለሁ ከሚለው ሕዝብ መጠን ጋር የሚመጣጠን ቀርቶ የሚቀራረብ እንኳ ድርሻ አልተሰጠውም። የአንበሳውን ድርሻ ይዞ የሚገኘው አነስተኛ ቁጥር ያለውን ሕዝብ ይወክላል የሚባለው ሕወሓት ነው። የሕወሀት የሥልጣን ድርሻ በቁጥር መብዛት ብቻ የሚገለፅ አይደለም። እጅግ ቁልፍ የሆኑትን የሥልጣን ቦታዎች ለሌሎቹ ባለማጋራትም የሚገለፅ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር፣ የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትር (ፖሊስን ደህንነትና ኢምግሬሽንን ያካትታል) የገቢዎች ሚኒስትር የሕወሓት ሰዎች ናቸው። የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ፣ የመከላከያ ኤታማዦር ሹም፣ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ሰብሳቢ፣ የአዲስ አበባ ከንቲባ፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካሪዎችና ረዳቶች፣ ሚኒስትር ዴኤታዎችና ምክትል ሚኒስትሮች፣ ኮሚሽነሮች፣ የመምሪያ ኃላፊዎች፣ ማኔጀሮችና የመሳሰሉት ከአስፈፃሚው አካል ጋር ግንኙነት ያላቸው የሥልጣን ቦታዎች ሲጨመሩ የሕወሓት ድርሻ ከሁሉም የበለጠ ነው።

ለኦህዴድ፣ ብአዴንና ደህዴግ የተሰጡ የሥልጣን ቦታዎች ቁጥራቸው ማነሱ ብቻ ሳይሆን ትንሽ ጣል እናድርግላቸው በሚል መንፈስ የተሰጡ የሥልጣን ፍርፋሪዎች ናቸው። እንዲያውም በብአዴንና በኦህዴድ ስም ስልጣን ከተሰጣቸው መካከል ለመንግስት ስልጣን የሚያበቃ ችሎታ የሌላቸውና እንወክለዋለን  የሚሉትን ሕዝብ ባህልና ወግ በሚገባ የማያውቁ እንዳሉበት ይታወቃል። በፌዴራሉና በአዲስ አበባ ሲቪል ሰርቪስና በመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ ያሉትን ቦታዎች ሳይቀር ቁልፍ የሚባሉትን ሕወሓት ልቅም አድርጎ የያዘበትን ሁኔታ ለሚያይ ማንኛውም ሰው በዚህች ሀገር ውስጥ የነገሰውን አምባገነንትና የሥልጣን ብልግና መረዳት አይሳነውም።

የመንግስት አስፈፃሚው አካል በጋራና ጠቅላይ ሚኒስትሩ በተናጠል የያዙት ስልጣን የሕግ አውጭውንና የሕግ ተርጓሚውን ሕልውና እንደሌለ የሚያስቆጥር ነው። ስለዚህ በሀገሪቱ ውስጥ ዴሞክራሲ መመስረት ካለበት አስፈፃሚው የመንግስት ሥልጣን አካል ፍጹም ፈላጭ ቆራጭ የሆነበት ሁኔታ መቀየር ይገባዋል። ሕግ አውጭው ግልጽ ተጠያቂነት ያለውና ሀቀኛ ቁጥጥር ሊደረግበት የሚችል በሕግ ግልጽ ሆኖ የተወሰነ ተመጣጣኝ ስልጣን የተሰጠው መሆን አለበት።

በሕገ መንግስቱ አንቀፅ 49 ንዑስ አንቀጽ 3 የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለፌዴራሉ መንግስት ይሆናል በሚል የተደነገገውን መሰረት በማድረግ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የአዲስ አበባ ከተማ የበላይ ኃላፊ የሆነበት አሰራር መቀየር ይኖርበታል። ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሥልጣን እንዲኖረው በሕገመንግስቱ አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 2 ሕጋዊ መብት የተሰጠውን አንድ ክልል በፌዴራሉ ጠቅላይ ሚኒሰትር ቁጥጥር ስር እንዲወድቅ ማድረግ ተሰጠ የተባለውን መብት መልሶ እንደመቀማት የሚቆጠር ነው።

አዲስ አበባ የፌዴራሉ መንግስት ርዕሰ ከተማ በመሆኗ ምክንያት ካላት የጎላ ብሔራዊ ገጽታ በተያያዘ ለፌዴራል መንግስት ተጠሪነት እንዲኖራት ማድረጉ መጥፎ ባይሆንም የፌደራሉን መንግስት አስፈፃሚ አካል በሚመራው ጠቅላይ ሚኒስትር እጅ ስር እንድትወድቅ ማድረጉ ግን ተገቢ አይደለም። የአዲስ አበባን ተጠሪነት እንደአንድ የፌደራል ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን አድርጎ ከማጥበብ ይልቅ የተሻለ ሊሆን የሚችለው የከተማዋ ተጠሪነት በቀጥታ ለሕግ አውጭው ምክር ቤት እንዲሆን ማስቻል ነው። አዲስ አበባ በፌዴራል መንግስት ርዕሰ ከተማነቷ፣ የራሷ አስተዳደር ያላትና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወከሉ የፓርላማ አባላትን በቀጥታ የምትወክል በመሆኗ የዚህችን ከተማ ጥቅሞች ለመጠበቅም ሆነ ሰፊ የአስተዳደር ነፃነት ያላት መሆኗን ለማረጋገጥ የተሻለ የሚሆነው የከተማዋን ተጠሪነት ለፌዴራሉ ተወካዮች ምክር ቤት ማድረግ ነው። አዲስ አበባ ላይ የተከናወነውን እንዲህ አይነቱን ስልጣንን አማክሎ የመቆጣጠር አሰራር በሌሎች ክልሎችም ላይ ለመፈፀም መንግስት በአሁኑ ወቅት እያደረገው ያለው ዝግጅት ፌዴራላዊ አደረጃጀቱን እንደገና አሃዳዊ አደረጃጀት የሚመልስ በመሆኑ መወገዝ ያለበት ነው።

የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥራ ዘመን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሥራ ዘመን (5 ዓመታት) እንደሚሆን በሕገመንግስቱ አንቀጽ 72 ንዑስ አንቀጽ 3 የተደነገገ ቢሆንም አንድ ጠቅላይ ሚኒስቴር ለስንት ዙር ሊመረጥ እንደሚችል በግልጽ የተቀመጠ ሕጋዊ ወሰን የለም:: የአሁኑ አገዛዝ ስልጣን በኃይል ከጨበጠ ጊዜ አንስቶ ለ12 ተከታታይ ዓመታት ሀገሪቱን የመሩት አንድ ግለሰብ ናቸው:: ወደፊትም ለምን ያህል ጊዜ በጠቅላይ ሚኒስትርነት እንደሚቆዩ ማወቅ አይቻልም:: አንድ ሰው እድሜ ልኩን የሀገር መሪ የሚሆንበት አገዛዝ ዴሞክራሲ በሌለበት ሁኔታ ውስጥ መሆኑ የታወቀ ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ የዴሞክራሲ ስርዓት መመስረት ካለበት በሕግ የተገደበ የጠቅላይ ሚኒስቴር የአገልግሎት ዘመን መኖር አለበት:: በኢዴፓ አመለካከት አንድ ጠቅላይ ሚኒስትር ቢበዛ ከሁለት ዙር የበለጠ ስልጣን ሊኖረው አይገባም:: ይህም በግልፅ በህግ የተወሰነ መሆን አለበት:: አንድ ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ባህርይና አሰራር እንዳለው ከሚመዘንበት መካከል አንዱ ከአባላቱ መካከል ማንኛውንም ለአመራር ኃላፊነት ችሎታ ያለው ሰው በነፃነት መርጦ ማሳተፍ ሲችል ነው:: ይኸንን ማድረግ የማይችል ድርጅት ዴሞክራሲያዊ ተቋም ሳይሆን የሥልጣን ፈላጊዎች መጠለያ ዋሻ ወይንም ጥቂት ግለሰቦች ወደስልጣን የሚንጠላጠሉበት መሰላል ብቻ ነው የሚሆነው::

የመንግስት አስፈፃሚው አካል በባንክ አስተዳደርና አመራር ላይ ያለውን የሥልጣን ሞኖፓሊ ማስቀረት ሌላው የዴሞክራሲ ስርዓት የሚጠይቀው አሰራር ነው:: አሁን በስራ ላይ ያለው ሕገመንግስት አንቀጽ 77 ንዑስ አንቀጽ 4 የመንግስት አስፈፃሚው አካል ብሔራዊ ባንክን የማስተዳደርና የመቆጣጠር ስልጣን እንዲኖረው ያዛል:: በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ ደግሞ ከአስፈፃሚው አካል ቁጥጥርና ተፅዕኖ ነፃ ሆኖ ራሱን ችሎ የሚሰራና የሚተዳደር ብሔራዊ ባንክ እንዲኖር ያስፈልጋል:: ከግለሰብ ነፃነት ጋር የተያያዘ ብቻ ሳይሆን የነፃ ገበያ ኤኮኖሚ መርህ የሚጠይቀው ግዴታም ነው:: በነፃነት የሚሰራ ብሔራዊ ባንክ መኖር በሀገሪቱ የልማት እድል ላይ ገንቢ ውጤት የሚያስከትል ነው:: ነፃ የገበያ ውድድር እንዲጠናከርና ባለሀብቶች ያለስጋት ኢንቨስት እንዲያደርጉ የሚያደፋፍር ነው:: ስለዚህ የአስፈፃሚው አካል የሥልጣን ሞኖፓል መነሳትና ነጻ በሆነ የራስ አስተዳደር የሚሰራ ብሔራዊ ባንክ እንዲኖር በግልጽ የተቀመጠ ሕጋዊ ስርዓት ያስፈልጋል::

የአስፈጻሚው አካል በሕገመንግስቱ አንቀጽ 93 ንዑስ አንቀጽ 4 ፊደል «ለ» መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለማውጣት በሚገደድበት ጊዜ የፖለቲካና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን እስከማገድ የሚደርስ መብት እንዳለው ተደንግጓል:: በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 ፊደል «ሐ» በማናቸውም ሁኔታ ሊገደቡ የማይችሉት መብቶች በሕገመንግስቱ አንቀጽ አንድ፣ አስራ ስምንት፣ ሀያ አምስትና ሰላሳ ዘጠኝ ንዑስ አንቀጽ አንድና ሁለት እንደሆኑ ተደንግጓል:: ማንኛውም ሰው በቅድሚያ ሊከበርለት የሚገባውና በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 15 የተደነገገው በሕይወት የመኖር መብት ገደብ ሊጣልበት ከቻለ ሌሎች መብቶቹ ተከብረውለታል ለማለት አይችልም:: በዚሁ ሕገመንግስት አንቀጽ 16 ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት እንዳለው የተደነገገው ገደብ ሊጣልበት ከቻለ ሌሎች መብቶቹ ይጠበቃሉ ማለት ትርጉም የለውም:: በተመሳሳይ ሁኔታ በሕገመንግስቱ ሌሎችም አንቀጾች የተደነገጉ የፖለቲካና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በማንም ሀይል መልካም ፈቃድ የሚወሰኑ አይደሉም:: ሲፈለግ እየተሰጡ፣ ሳይፈለግ የሚነጠቁ ሳይሆኑ በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሊከበሩ የሚገባቸው ናቸው:: ሕገመንግስቱ ገደብ የማይጣልባቸው እንዲሆኑ ጥበቃ ከሰጣቸው አንዳንድ መብቶች ይልቅ ገደብ እንዲጣልባቸው የተደረጉት መብቶች መሰረታዊ ናቸው:: አንድ ሰው በሕይወት የመኖር መብቱ ካልተጠበቀለት በምን አይነት ዘዴ የእኩልነት መብቱ ወይም የመገንጠል መብቱ እንደሚከበር ማወቅ አይቻልም:: ስለዚህ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የተሰጠውና የሰውን ልጅ በሕይወት የመኖር መብት እስከመገደብ የሚደርሰው ስልጣን መነሳት ይገባዋል:: እንዲህ አይነት ለጭካኔ አገዛዝ የተመቸ ሕጋዊ መብት የተሰጠው የመንግስት አስፈጻሚ አካል እስካለ ድረስ ለዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ዋስትና የሚሆን የዴሞክራሲ ስርዓት ሊገነባ አይችልም::

በሕገመንግስቱ አንቀጽ 101 ስለዋናው ኦዲተር የተቀመጡት ድንጋጌዎች፣ በአንቀጽ 102 ደግሞ ስለምርጫ ቦርድ የሰፈሩት ድንጋጌዎች የዋናው ኦዲተርና የምርጫ ቦርድ ተጠሪነት በቀጥታ ለተወካዮች ምክር ቤት መሆኑን በግልፅ አያመለክቱም:: በመሆኑም እነዚህ ቁልፍ የሕዝብ ተቋሞች በርካታ ስልጣን ባግበሰበሰው በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተፅዕኖ ስር የመውደቅ አደጋ ያጋጥማቸዋል:: በተግባር እየታየ ያለውም ይኸው ነው:: በሀገሪቱ ውስጥ የነገሰውን የስልጣን ብልግና፣ የገንዘብ ብክነትና የንብረት ዘረፋ ማስቀረት ያልተቻለው ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁጥጥር ውጭ በነጻነት የሚሰራ

የዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ባለመፈጠሩ ነው፡፡ በሀገሪቱ ወስጥ ነጻና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ለማካሄድ የማይቻለው ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ቁጥጥርና ተፅዕኖ ነጻ ሆኖ የሚሰራ የምርጫ ቦርድ ባለመቋቋሙ ነው፡፡ ከፖለቲካ ቁጥጥር ነፃ ሆነው በገለልተኝነት መርህ መቋቋምና መስራት ያለባቸው ልዩ ልዩ ተቋሞች የአደረጃጀትና የአሰራር ነፃነት እንዳላቸው የሚያረጋግጥ ሕጋዊ ድንጋጌ መቀመጥ አለበት፡፡ ለምሳሌ ዩኒቨርስቲዎች ከትምህርት ሚኒስቴር፣ የመገናኛ ብዙሃን ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ነጻ ሆነው መደራጀት አለባቸው፡፡ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽንና የመሳሰሉት ተቋሞች በነፃነት መስራት የሚገባቸው ናቸው፡፡ ከተሞች በሕዝብ በሚመረጡ ምክር ቤቶች የሚመራ የራሳቸው አስተዳደር እንዲያቋቁሙ ሕጋዊ ነጻነትና መብት በመስጠት ፋንታ በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስትርም ይሁን በሌላ ፖለቲካዊ ቁጥጥር ሊጭንባቸው በሚችል ግለሰብ ባለስልጣንና ተቋም ስር ሊወድቁ አይገባቸውም፡፡

በአስፈፃሚው አካል ውስጥ በካቢኔ አባልነት፣ በሚኒስትርነት ወይም በሌላ የሥልጣን እርከን ላይ የሚመደቡ ሰዎች መመዘኛ የፖለቲካ ታማኝነት ብቻ መሆን አይገባውም፡፡ የተመደቡበትን ቦታ ለመምራት የሚያስችል የሞያ ብቃት፣ የሥራ ልምድና ሥነምግባር ያላቸው ሰዎች እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒሰትሩ የካቢኔ መወያያ አጀንዳዎችን የመቅረፅ፣ ስብሰባዎችን የመምራት፣ በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ አመራር የመስጠትና በሚኒስትሮች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን የማስወገድ ቁልፍ ሚና ቢኖረውም የካቢኔ አባላትንና ሚኒሰትሮችን እያማከረ ለመስራትና ለመወሰን የሚያስገድዱት ሁኔታዎች በርካታ ናቸው፡፡ ስለሆነም በአስፈጻሚው አካል ውስጥ የሚመደቡ ሹሞች የታዘዙትን ሁሉ ለመፈፀም የማያንገራግሩ ታማኞች ብቻ ከሆኑ ሀገርን የሚመራ ጠቅላይ ሚኒስትር ለማማከርና ውሳኔ ለመስጠት መነሻ የሚሆን እውነተኛ መረጃ ለመስጠት አቅም አይኖራቸውም፡፡ የሾማቸውን ፓርቲና መንግስት ብቻ ሳይሆን የሀገርንና የሕዝብን ጥቅም የሚጎዳ ጥፋት ያደርሳሉ፡፡ የፖለቲካ ተሿሚዎች ብቃት፣ ልምድና ስነምግባር አስተማማኝ ካልሆነ የፖለቲካ ታማኝነትና ታዛዥነት ብቻውን የአስፈጻሚውን አካል ውጤታማ አያደርገውም፡፡

የአስፈፃሚው አካል ውጤታማ እንዲሆን በፓርላማ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ አብላጫ ድምፅ መኖር፣ የፖለቲካ ታማኝነት ያላቸው የካቢኔ አባላት መብዛትና ሁሉንም የሥልጣን ወንበር ጠቅልሎ የያዘ ድርጅት መኖር የግድ አስፈላጊ ነገሮች አይደሉም፡፡ ከዚህ ሁሉ የበለጠ ጠቃሚ የሚሆነው ዴሞክራሲያዊና ሕጋዊ የሆነ ሥርዓት መኖር ነው፡፡ ይኸ ስርዓት ባለበት ሁኔታ የፓርላማ መቀመጫ ብልጫ፣ ታዛዥ የካቢኔ አባልና ወንበር ጠባቂ ሹም በየቦታው ማስቀመጥ የግድ አስፈላጊ አይደለም፡፡ በዴሞክራሲያዊና ሕጋዊ ስርዓት ውስጥ የተለያየ ፖለቲካዊ አመለካከት ካላቸው ሰዎች ጋር ልዩነቶችን እያቻቻሉ፣ ሀቀኛ በሆነ የመስጠትና የመቀበል መርህ እየተስማሙ መስራት ይቻላል፡፡ ችሎታ፣ የስራ ልምድና ከፍተኛ ስነምግባር ያላቸውን ሰዎች የፖለቲካ ሹመት ለመስጠት የፖለቲካ አመለካከት ልዩነት መኖር ብቻውን ትልቅ እንቅፋት ሊሆን አይችልም፡፡

## 3.3 ሲቪል ሰርቪስ

የመንግስት አስፈጻሚ አካል ኃላፊነቱን የሚወጣበት ሌላው አካል የሲቪል ሰርቪስ ነው፡፡ የአንድ ሀገር ሲቪል ሰርቪስ በሕግ አውጭውና ሕግ አስፈጻሚው የሚወጡ ፖሊሲዎችን ለማስፈጸም፣ ሕግና ደንቦችን ተግባራዊ ለማድረግ በመንግስት የተቀጠሩ ሰራተኞች የሚገኙበት የሕዝብ አስተዳደር ተቋም ነው፡፡ ሲቪል ሰርቪስ ብዙውን ጊዜ ለመንግስት መስሪያ ቤቶች ፖለቲካዊ አመራር እንዲሰጡ የሚሾሙ የፖለቲካ መሪዎች የሕግ ረቂቅ በሚያዘጋጁበትና ፖሊሲዎችን ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ቴክኒካዊ ድጋፍና የምክር አገልግሎት የሚሰጡ ከፍተኛ የመንግስት ስራ ኃላፊዎችንም ይጨምራል፡፡ ሁሉም መንግስታት የሲቪል ሰርቪሱን አገልገሎት ይጠቀማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ አስቸጋሪ የሚሆነው የሕዝብ አስተዳደር በሆነው ሲቪል ሰርቪስ የስራ ኃላፊዎችና ፖለቲከኞች መካከል ግልፅ የሆነ ልዩነት ማስቀመጥ ነው፡፡ በምርጫ ወደ መንግስት ስልጣን በሚመጡና እንደማንኛውም ተቀጣሪ የመንግስት ሰራተኛ ለሚሰሩት ስራ ደመወዝ እየተከፈላቸው በቋሚነት በሚሰሩ የሲቪል ሰርቪስ የስራ ኃላፊዎች መካከል ግልጽ ልዩነት እንዲኖር በማድረግ በኩል የተሻለ አሰራር ያለው የዴሞክራሲ ስርዓት በገነቡ ሀገሮች ውስጥ ነው፡፡

ሲቪል ሰርቪስ በራሱ ፖሊሲ የሚያወጣ አካል ሳይሆን ከአንድ ፓርቲ ወገንተኝነት ነፃ በሆነ መንገድ ፖለቲከኞች የሚያወጡትን ፖሊሲና ትዕዛዝ የሚያስፈጽምና ምክር የሚሰጥ ተቋም ሆኖ የሚሰራበት

*ግልፅ አቅጣጫ መቀመጥ አለበት። በእርግጥ ብዙ ጊዜ ፖለቲከኞች ዛሬ መጥተው ነገ የሚሄዱ እንደመሆናቸው ከፍተኛ የጊዜ እጥረትና በቂ የቴክኒክ እውቀት ችግር ስለሚያጋጥማቸው በሲቪል ሰርቪስ ምክር ብቻ የሚተማመኑ ከሆነ ከፍተኛ ችግር ሊገጥማቸው ይችላል። እናም ሲቪል ሰርቪሱ በፖለቲከኞች ላይ በሚያሳድረው ጫና ፖለቲካዊ ሚና የሚጫወትበት ሁኔታ ይፈጠራል። ከፍተኛ በሆነው የሲቪል ሰርቪስ ስራ ኃላፊነት ላይ ያሉት ሰዎች ከፖለቲካ ገለልተኛ መሆናቸውን እርግጠኛ ለመሆን እስኪያስቸግር ድረስ ፖለቲካዊ ተፅዕኖ እስከመፍጠር ይደርሳሉ።*

*በአንዳንድ ሀገሮች ለምሳሌ በአሜሪካ ከፍተኛ የሲቪል ሰርቪስ ስራ ኃላፊዎች ከፖለቲካ ኃላፊዎች የሚበዙበት ሁኔታ አለ። በኢጣሊያ፣ በጀርመንና በሌሎችም ሀገሮች በከፍተኛ የሲቪል ሰርቪስ ኃላፊነቶች ላይ የፖለቲካ ተሿሚዎችን የማስቀመጥ አሰራር ስላለ የመንግስት ለውጥ በተከሰተ ቁጥር አዳዲስ ተሿሚዎችን ማፈላለግ አስፈላጊ ይሆናል። በዚህም ምክንያት ከፖለቲካ ገለልተኛ ሆኖ የፖለቲካ መሪዎችን ውሳኔ የሚያስፈጽም የሲቪል ሰርቪስ ተቋም በፖሊሲ አወጣጥ ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩን ጨርሶ ማስወገድ ያልተቻለ ጥያቄ ሆኗል። በንድፈ ሀሳብ ደረጃ ከፍተኛ የሲቪል ሰርቪስ ስራ ኃላፊዎች ለፖለቲካ መሪዎች ምክር ይሰጣል። የፖለቲካ መሪዎች ደግሞ የመጨረሻውን ውሳኔ በራሳቸው መንገድ ይወስናሉ። የሲቪል ሰርቪስ ዋነኛ ስራ ደግሞ ይኸንን ውሳኔ በስራ ላይ ማዋል ይሆናል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በፖለቲከኞች መሰራት ያለበትን ሁሉ ስራ እየነጠቀ ነው የሚል ስሞታ ጎልቶ መሰማት ጀምሯል። ከዚህም አልፎ የፖለቲካ መሪዎች ሊከተሉት የሚፈልጉትን አቅጣጫ ለማስቀየር ሻጥር ይሰራሉ የሚል ጠንካራ ወቀሳም አለ። የሲቪል ሰርቪሱ ስራ ኃላፊዎች በፖሊሲ ማማከር ክልል ወይም በቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ስራ በቋሚነት የሚሰሩ ሲሆኑ ሚኒስትሮችና ሌሎች የፖለቲካ ተሿሚዎች ደግሞ ዘንድሮ በምርጫ ሥልጣን ይይዙና በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት የያዙትን ስልጣን ሊያጡ ይችላሉ። በተጨማሪ አሁን ለተመደቡበት ስራ ያላቸው እውቀት አነስተኛ ይሆናል። ወይም ምንም አይነት እውቀት ላይኖራቸው ይችላል። እንዲህ ዓይነቶቹን ችግሮች ከሚከላከሉባቸው መንገዶች መካከል የራሳቸውን አማካሪዎች መመደብ አንዱ ነው።*

*ከዚህ በተጨማሪ በመንግስት ሰራተኞች ምደባ እድገት አሰጣጥ ዝውውርና ስንበት ውስጥ እጃቸውን በማስገባት ሁኔታዎችን በሚፈልጉት አቅጣጫ ለማካሄድ ይሞክራሉ። ይሁን እንጂ ይህ ደግሞ የራሱ ጉድለቶችና ችግሮች አሉበት። ከዚህ ጋር የተያያዘው ዋነኛ ችግር የሲቪል ሰርቪሱ ገለልተኛነት የሚጠፋበትና ፖለቲካዊ ገጽታው የሚያመዝንበት ሁኔታ መፈጠሩ ነው። እንዲህ አይነቱ ሁኔታ ሲፈጠር ደግሞ ሲቪል ሰርቪሱ ከአንድ ስልጣን ላይ ከወጣ ፖለቲካ ፓርቲ ጋር ወጥ የሆነ ስራ የሚሰራ ፖለቲካዊ ተቋም ይሆንና ገለልተኛና ነጻ የሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም መሆኑ ይቀራል። በዚህ መንገድ ገለልተኝነትና ነፃነቱን ጨርሶ የተነጠቀ ተቋም ደግሞ ስልጣን ላይ ከነበረው ፓርቲ የተለየ ፖለቲካዊ እምነት ያለው ፓርቲ በምርጫ አሸንፎ የመንግስት ስልጣን በሚመሰርትበት ጊዜ አገልግሎት የማይሰጥና የግድ መፍረስ ያለበት ሆኖ ይገኛል።*

*በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ በሲቪል ሰርቪሱ ላይ የሚደረግ ፖለቲካዊ ቁጥጥር የሲቪል ሰርቪሱን ተጠያቂነትና የአሰራር ነጻነት ሚዛን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ ብርቱ ጥረት ይደረጋል። በየትኛውም የሲቪል ሰርቪስ ውስጥ የሚካሄዱ ስራዎች በመንግስት ገንዘብ የሚከናወኑ በመሆናቸው ለሚሰሩት ስራ ኃላፊነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ ከልክ ያለፈ ተጠያቂነት በሚኖርበት ጊዜ የስራ ተነሳሽነትን ከመጉዳት አልፎ የመንግስት ሰራተኞች ስራቸውን በሚሰሩበት ጊዜ ከጥርጣሬ ነጻ ሆነው እንዳይሰሩና የአሰራር ስርዓቶችን ፈጠራ በተሞላበት ዘዴ ለመጠበቅ በማይችሉት ፍርሃት ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋል። ስለዚህ የተሻለው ዘዴ በአንድ በኩል የሲቪል ሰርቪስ ተቋሞች ለሚያስገኙት ጥሩና መጥፎ ውጤት ተጠያቂነት ያለባቸው መሆኑ እንደተጠበቀ ሆነ በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ውጤት ላይ ለመድረስ የሚያስችላቸውን መንገድ ብልሃት እየፈለጉ የሚወስኑበት ነጻነት እንዲኖራቸው ማድረግ ነው።*

*በአሁኑ ጊዜ በዴሞክራሲ ስርዓቶች ውስጥ የሚካሄዱ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ እርምጃዎች ተጠ ያቂነት፣ ግልጽነትና የአሰራር ነጻነት እንዲጠናከር በማድረግ አላማ ላይ ያተኮሩ ናቸው። በዚህ መሰረት ወደዚህ ግብ ለመድረስ የመጀመሪያው አቅጣጫ የስራ ብቃትን ለማሳደግና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የስራ አመራር ቴክኒኮችን እየቀየሱ ተግባራዊ ማድረግ ነው። ይኸንን እውን ለማድረግ በሲቪል ሰርቪሱ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ መመሪያዎችና ዓላማዎች እየለያዩ ከማስቀመጥ ጀምሮ*

ግልጽ የሆኑ የስራ አፈጻጸም ውጤት መለኪያዎችን ተግባራዊ በማድረግ የአላማዎቹን ተፈጻሚነት እስከመመዘን የሚደርስ ቅንጅት መፍጠር ይቻላል፡፡

ሁለተኛው አቅጣጫ ደግሞ የሲቪል ሰርቪሱን አጠቃላይ አደረጃጀት በፖሊሲ እቅድ አውጭና በአገልግሎት ሰጪ ክፍሎች ለይቶ መመደብ ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ የሲቪል ሰርቪስ አደረጃጀትና የስራ አመዳደብ ከፍተኛ የመንግስት ስራ ኃላፊዎች በረጅም ጊዜ ፕላን ላይ ይበልጥ እንዲያተኩሩና በእቅድ አወጣጥ ላይ ያላቸውን ችሎታ እንዲያሳድጉ ያደርጋል፡፡ በአገልግሎት አሰጣጥ የተሰማሩ ሰራተኞች ደግሞ በራሳቸው ፍላጎት ለመወሰን የሚያስችል የአሰራር ነጻነት ያላቸውን ኤጀንሲዎች እያቋቋሙ ለመስራትና በፖሊሲ አውጭዎች ወይም መምሪያዎች እየተዘጋጀ የሚሰጣቸውን አላማና ማስፈፀሚያ በጀት በሚገባ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ውክልና እንዲያገኙ ይረዳል፡፡

ሶስተኛው አቅጣጫ በግል ክፍለ ኤኮኖሚ ውስጥ የሚሰጠውን አገልግሎት ውጤታማ እንዲሆን ለመርዳት ሲታሰብ ከሕዝቡ ፍላጎት አኳያ የሚቀርብ ማንኛውም አገልግሎት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ የኮንትራት ውል መፈፀምና የውሉን ተግባራዊነት በተከታታይ መገምገም ነው፡፡ ብቁ የኮንትራት ውል አፈጻጸም መኖሩንና አገልግሎቱ የተጠቃሚውን ሕዝብ ፍላጎት ጠብቆ በብቃት እየቀረበ መሆኑን ማረጋገጥ ትኩረት የሚሰጠው ጉዳይ ነው፡፡ ከመንግስት አሰራር በተለየ መንገድ የሚካሄድን የኮሜርሽያል አገልግሎት አሰጣጥ በሲቪል ሰርቪሱ ስታንደርድ መሰረት ለመገምገም ሲሞከር ችግር እንዳይፈጠር በግል ተቋሞች ለሚሰጡ አገልግሎቶችም የብቃት መከታተያ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው፡፡

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻዎች በሚደረጉበት ጊዜ ተቋሞችና ሰራተኞች ሕልውናቸው አደጋ ላይ እንደሚወድቅ ስጋት በማይፈጥርባቸው ግልጽ አሰራር መመራት ይኖርባቸዋል፡፡ ግልጽነት በሌለው መንገድ የሚካሄድ የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ስጋት በሚሰማቸው ተቋሞችና ሰራተኞች ከባድ ተቃውሞ የሚያጋጥመው መሆኑ ብቻ ሳይሆን የታሰበውን ውጤት ሳያስገኝ የሚኮላሽበትም ሁኔታ ያጋጥማል፡፡ ስለዚህ ለሲቪል ሰርቪስ ማሻሽያ አስፈላጊ ተደርገው የሚወሰዱት ጉዳዮች የመንግስት ፖለቲካዊ ፍላጎት መኖር ብቻ ሳይሆን የተቋሞችንና የሰራተኞችን ስጋቶች የሚቀንሱ ግልጽ አሰራሮችም መከተልም ሕጋዊ አግባቦች ናቸው፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የሲቪል ሰርቪስ ችግሮች በአብዛኛው ከመንግስት አስፈጻሚው አካል ተጠያቂነትና ግልፅነት ማጣት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ገዥው ፓርቲ የሲቪል ሰርቪሱን መዋቅር የፓርቲው አንድ ቅርንጫፍ አድርጎ ለመጠቀም ከፍተኛ ጥረት ስለሚያደርግ በፖለቲካና በሲቪል ሰርቪስ መካከል ያለውን ልዩነት ለማየት በማይቻልበት ደረጃ አጥፍቶታል፡፡ በዚህ ምክንያት በሀገሪቱ የሲቪል ሰርቪስ መዋቅሮች ውስጥ ከፍተኛ ስርዓት አልበኝነትና ሙስና እየሰፈነ ነው፡፡ በሀገሪቱ ለስሙ ፀረ-ሙስና ተቋም ተቋቁሟል ይባላል እንጂ ሙሰኞቹን የሚከስና የሚጠይቅ አንድም አሳማኝ ጥረት ሲደረግ አልታየም፡፡ ትላልቁ ሙሰኛ ሁሉ ከእነሙሉ ክብሩና ስልጣኑ በቦታው ላይ እንደተቀመጠ ነው፡፡ የተወሰኑ የስርዓቱ ባለሚሎች ለፓርቲውና ለመንግስት ስልጣን መናጋት ስጋት ሆነው በሚታዩበት ጊዜ ሙሰኛ እየተባለ የሚከሰሱበት ሁኔታ ቢኖርም እስካሁን ድረስ ከሙስና ጋር የተያያዘ ጥፋት ሰርተው ለመገኘታቸው በማያጠራጥር መንገድ መረጃ የሚቀርብባቸው ሹማምንት የፀረ-ሙስና ዘመቻው የሚመለከታቸው ሆኖ አልተገኘም፡፡

ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ሲቪል ሰርቪሱ በብዙ እጅ የፓርቲ መዋቅር ከሆነበት ሁኔታ እንዲላቀቅና አሁን ስልጣን ላይ ካለው ፓርቲ የተለየ ፖለቲካዊ አመለካከት ያለው ሌላ ፓርቲ በምርጫ መንግስት ቢመሰርት የመፍረስ እድል እንዳያጋጥመው ከተፈለገ መሰረታዊ እርምጃዎች መወሰድ አለባቸው፡፡ የፖለቲካ ተሿሚና የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኛ ተግባሮች በግልጽ ተለይተው መቀመጥ አለባቸው፡፡ በሲቪል ሰርቪስ ውስጥ ተቀምጠው የፓርቲ ድርጅታዊ ስራና የስለላ ተግባር የሚያከናውኑ የፓርቲ ሕዋሶች በመንግስት ስራ ጣልቃ እንዳይገቡ ግልጽ የሆነ ሕጋዊ ግዴታ ሊጣልባቸው ያስፈልጋል፡፡ የሲቪል ሰርቪስ ሰራተኞች ቅጥር፣ እድገት፣ ስልጠና፣ ዝውውር፣ ስንብትና ጥቅማ ጥቅሞች የሚመሩበት ሕጋዊ ስርዓት መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ እነዚህን ሁኔታዎች የውለታ መክፈያ፣ የዘመድ ማውጫና መጠቃቀሚያ በማድረግ እስካሁን ሲሰራበት የነበረውን ሁኔታ የሚያስቆምና ሕገወጥ የሚያደርግ ግልፅ ስርዓትና ድንጋጌ መኖር አለበት፡፡ በአሁኑ ወቅት በመካሄድ ላይ የሚገኘው ሲቪል ሰርቪስ ማሻሽያ ፕሮግራም በሲቪል ሰርቪሱ ላይ ከዚህ በፊት የነበረውን ፖለቲካዊ ቁጥጥር ይበልጥ

ለማጥበቅ የታለመ በመሆኑ ከፍተኛ ለውጥ ያስገኛል ተብሎ እምነት የሚጣልበት አይደለም። እንዲያውም የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽኑን ወደጎን ትቶ ሌላ ተጨማሪ መዋቅር የፈጠረ በመሆኑ አላስፈላጊ የሰው ኃይል፣ የገንዘብና የጊዜ ብክነት፣ የስራ መደራረብና መዘበራረቅ ፈጠረ እንጂ ያሻሻለው ነገር የለም። የማሻሻያ ፕሮግራም ሰራተኛውን በሚገባ ያሳተፈና ብቃት ባላቸው ሞያተኞች የተዘጋጀ ሳይሆን በካድሬዎችና የኮር አባሎች የሚመራ ፖለቲካዊ ተጽዕኖ የበዛበት ነው። ይህ ደግሞ በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማና በሌሎችም የክልል ከተሞች በተካሄደ የሰራተኞች ምደባ በተግባር የታየ ነው።

የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያው ትኩረት ሊሰጣቸው ከሚገባው ጉዳዮች ውስጥ የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። የሰራተኞች ቅጥር በሲቪል ሰረቪስ በሚዘጋጅና ደረጃውን በጠበቀ የችሎታ መመዘኛ ብቻ እንዲሆን የሚያስችል አደረጃጀትና አሰራር መፍጠር፣ የሰራተኞች እድገት በሲኒየሪቲ ብቻ ሳይሆን በስራ ብቃት መመዘኛዎች የተደገፈ እንዲሆን ማስቻል፣ የሲቪል ሰርቪሱ አደረጃጀት ሞያተኞችንና ድጋፍ ሰጭዎችን፣ የፖሊሲ እቅድ አውጭዎችንና አገልገሎት ሰጪዎችን፣ በግልጽ ለይቶ በሚያስቀምጥ መንገድ እንዲሆን ማድረግ፣ የሰራተኞች ምደባ በሁሉም ክልሎች ተቀራራቢ በሆነ መመዘኛ እንዲሰራ ማስቻል፣ የሲቪል ሰርቪሱ አሰራር በዘመናዊ ቴክኒዎሎጂ የሚታገዝ፣ ቀልጣፋና ግልፅ እንዲሆን ማድረግ፣ በፌዴራልና በክልል የሚቋቋሙ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽኖች ቀጥተኛ ፖለቲካዊ ቁጥጥርና ተፅዕኖ የማይደረግባቸው የራሳቸው የአስተዳደር ነጻነት ያላቸው ሆነው እንዲደራጁ ማድረግ፣ የሲቪል ሰርቪሱ ኮሚሽነሮች ሹመትና ተጠሪነት በፌዴራልና በክልል ለሚገኙ ሕግ አውጭ አካላት እንዲሆን ማድረግ፣ ሰራተኞች ሊያገኟቸው የሚገቡ የዝውውር፣ የጉርሻ፣ የስራ ላይ ስልጠና፣ የእድገትና የመሳሰሉት ጥቅማ ጥቅሞች የሚፈፀሙበት ግልጽ የአሰራር ደንብና አደረጃጀት እንዲኖር ማድረግ የሚሉት ናቸው። እነዚህን ለውጦች በማምጣት የሲቪል ሰርቪሱን ማሻሻያ በቋሚ መሰረት ላይ መገንባት ካልተቻለ አሁን በተጀመረው መንገድ ይቀጥል ቢባል ማቆሚያ ወደሌለው አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መግባት ይመጣል።